Ambasáid na hÉireann
Embassy of Ireland

GAGE — GENDER & ADOLESCENCE: GLOBAL EVIDENCE



# የሴት ልጅ ግርዛትና የህጻናት ጋብቻ አመለካከት

## ልማድና ተግባር በአፋር እና ሶማሌ የአጋማሽ ጥናት ግኝቶች

ከፍያለው እንዳለ፣ ኤልዛቤት ፕሪስለር ማርሻል፣ ወርቅነህ ያደቴ፣ ኒኮላ ጆንስ፣ ይታገሱ ገበየሁ፣ አብዲላሂ አብዲሰላም፣ ካሳሁን ጥላሁን፣ ፍጹም ወርቅነህ እና ጣሰው ወልደሃና

April 2025

## Acknowledgements

ምስጋና፡ ተመራማሪዎቹ አስመረት ገብረህይወት፣ መቲ ከበደ፣ ሮብሃ ሙርሃ እና ፍፁም ወርቅነህ ለሰጡት ጠቃሚ የመረጃ አሰባሰብ እና የመጀመሪያ ትንተና ግብአቶች እውቅና መስጠት ይወዳሉ። በተጨማሪም ክሪስቲን ክሁሪ ላደረጉት የሕትመት ማስተባበሪያ ድጋፍ፣ ጆጆህ ፋል ሲ ለዲዛይንና ሌይአውት፣ እንዲሁም ለኦታቪያ የኢንፎግራፊክስ ዲዛይን ስራ ማመስገን ይፈልጋሉ። በመጨረሻም ጊዜያቸውንና አመለካከታቸውን በልግስና የሰጡ የምርምር ተሳታፊዎችን በሙሉ ከልብ እናመሰግናለን።

## ይማጣቀሻ ጥቆማ

Endale, Kefyalew., Presler-Marshall, E., Yadete, W., Jones, N., Gebeyehu, Y., Abdiselam, A., Tilahun, K., Workneh, F. and Woldehanna, T. (2025) FGM and child marriage attitudes, norms and practices: Midline findings. Report. London: Gender and Adolescence: Global Evidence.

# ማውጫ

**አጽህሮተ ሪፖርት** **1**
መግቢያ 1
የምርምር ዘዴ 1
ቁልፍ ግኝቶች 1
ቤተሰብ፣ የኑሮ መተዳደሪያ እና ማህበራዊ ጥበቃ 1
ትምህርት 1
የሴት ልጅ ግርዛት 2
የህጻናት ጋብቻ 3
የልጃገረዶችና ሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም 4

**መግቢያ** **6**

**የጥናቱ ዳራ** **7**
የአፋርና የሶማሊ ክልላዊ አውዶች 7

**የጥናቱ ንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፍ** **9**

**ናሙና እና ዘዴዎች** **11**

**ግኝቶች** **13**
ቤተሰብ፣ መተዳደሪያ እና የማህበራዊ ጥበቃ መዳረሻ 13
ሶማሊ 16
ትምህርት 19
የሴት ልጅ ግርዛት 28
የህጻናት ጋብቻ 48
የልጃገረዶችንና የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም ማጎልበት 55

**መደምደሚያ እና ለፕሮግራም እና ፖሊሲ ያለው አንድምታ** **62**

**ዋቢ መጻህፍት** **69**

## Figures

ምስል 1: የጊጅ ንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፍ 10
ምስል 2: የምርምር ቦታዎች 11
ምስል 3: ለከብት ግጦሽ ፍለጋ የቤተሰብ ስደት፣ አፋር 13
ምስል 4: የቤተሰብ ቋሚ ንብረት፣ አፋር 14
ምስል 5: የቤተሰብ ዋና የገቢ ምንጭ፣ አፋር 14
ምስል 6: የምግብ ዋስትና፣ አፋር 14
ምስል 7: ማህበራዊ ጥበቃ የማግኘት ዕድል፣ አፋር 15
ምስል 8: ለከብት ግጦሽ ሳር ፍለጋ የቤተሰብ ስደት፣ ሶማሊ 16
ምስል 9: በሶማሊ የቤተሰብ ንብረቶች 17
ምስል 10: የቤተሰብ ዋና የገቢ ምንጭ፣ ሶማሊ 17
ምስል 11: የምግብ ዋስትና በሶማሊ 17
ምስል 12: የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነት በሶማሊ 18
ምስል 13: የአፋር አሳዳጊዎች ለወንዶች ልጆቻቸው ከሴቶች ልጆቻቸው አንጻር ያላቸው የትምህርት ፍላጎት 20
ምስል 14: በትምህርት ላይ ያሉ የአፋር ወጣቶችና የትምህርት ክትትል 20
ምስል 15: የአፋር ወጣቶች የደረሱበት የክፍል ደረጃ 21
ምስል 16: ለመደበኛ ትምህርት የተመዘገቡ የአፋር ልጆች ድርሻ በአሳዳጊዎች እንደተገለጸው 21
ምስል 17: ለወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ የትምህርት ቤት ድጋፍ፣ ለአፋር ሴት ተማሪዎች ብቻ 21
ምስል 18: የሶማሊ አሳዳጊዎች ለወንዶች ልጆቻቸው ከሴቶች ልጆቻቸው አንጻር ያላቸው የትምህርት ፍላጎት 23
ምስል 19: በትምህርት ላይ ያሉ የሶማሊ ወጣቶችና የትምህርት ክትትል 24
ምስል 20: የሶማሊ ወጣቶች የደረሱበት የክፍል ደረጃ 24
ምስል 21: ለመደበኛ ትምህርት የተመዘገቡ የሶማሊ ልጆች ድርሻ በአሳዳጊዎች እንደተገለጸው 25
ምስል 22: ለወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ የትምህርት ቤት ድጋፍ፣ ለሶማሊ ሴት ተማሪዎች ብቻ 25
ምስል 23: የአፋር ታዳጊ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ 29
ምስል 24: በሴት ቤተሰብ የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ በእድሜ ደረጃ፣ በአፋር አሳዳጊዎች እንደተገለጸው 30
ምስል 25: የአፋር ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳት እና ጥቅም ያላቸው እምነት 30
ምስል 26: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳቶችና ጥቅሞች ያላቸው እምነት 30
ምስል 27: የአፋር ወጣቶች ስለ የሴት ልጅ ግርዛት ሃይማኖታዊ ግዴታ እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት 31
ምስል 28: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ተጠባቂነት፣ ሃይማኖታዊ ግዴታዎች እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት 32
ምስል 29: የአፋር ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት 32
ምስል 31: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት 33
ምስል 32: የአፋር ወጣቶች እና አሳዳጊዎች ስለ ብሄራዊ የሴት ልጅ ግርዛት ህግ የማያውቁ 33
ምስል 33: የአፋር ወጣቶች ወደፊት በሴት ልጆቻቸው ላይ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመተግበር ያላቸው ፍላጎት 34
ምስል 30: የአፋር ወንዶች ልጆችና ወጣት ወንዶች ስለወደፊት ሚስታቸው የግርዛት ሁኔታ ያላቸው ምርጫ 35
ምስል 34: የሶማሊ ታዳጊ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ 39
ምስል 35: በሴት ቤተሰብ የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ በእድሜ ደረጃ፣ በሶማሊ አሳዳጊዎች እንደተገለጸው 40
ምስል 36: የሶማሊ ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳቶችና ጥቅሞች ያላቸው እምነት 40
ምስል 37: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳቶችና ጥቅሞች ያላቸው እምነት 41
ምስል 38: የሶማሊወጣቶች ስለ የሴት ልጅ ግርዛት ሃይማኖታዊ ግዴታ እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት 41
ምስል 39: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ተጠባቂነት፣ ሃይማኖታዊ ግዴታዎች እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት 42
ምስል 40: የሶማሊ ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት 42
ምስል 41: የሶማሊ ወንዶች ልጆችና ወጣት ወንዶች ስለወደፊት ሚስታቸው የግርዛት ሁኔታ ያላቸው ምርጫ 43
ምስል 42: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት 44
ምስል 43: የሶማሊ ወጣቶች ስለ ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ሕግ ያላቸው እውቀት 44
ምስል 44: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ሕግ ያላቸው እውቀት 44
ምስል 45: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ሕግ ያላቸው እውቀት 44
ምስል 46: የአፋር ወጣቶች ምርጫ፣ እምነት እና ስለ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ያላቸው እውቀት 49
ምስል 47: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና እውቀት 49

ምስል 48: የሶማሊ ወጣቶች ስለ የህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና እውቀት 52
ምስል 49: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ የህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና እውቀት 53
ምስል 50: ለአፋር ወጣቶች የማህበራዊ አቅም መጎልበት አመላካቾች 55
ምስል 51: የአፋር ወጣቶች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም መጎልበት ያላቸው እምነት 55
ምስል 52: የአፋር አሳዳጊዎች ወጪ እና ቁጠባ 56
ምስል 53: የአፋር አሳዳጊዎች የገቢና ንብረትን የመቆጣጠር ሁኔታ 56
ምስል 54: የአፋር አሳዳጊዎች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መጎልበት ያላቸው እምነት 57
ምስል 55: ለሶማሊ ወጣቶች የማህበራዊ አቅም መጎልበት አመላካቾች 58
ምስል 56: የሶማሊ ወጣቶች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም መጎልበት ያላቸው እምነት 58
ምስል 57: የሶማሊ አሳዳጊዎች ወጪ እና ቁጠባ 59
ምስል 58: የሶማሊ አሳዳጊዎች የገቢና ንብረትን የመቆጣጠር ሁኔታ 59
ምስል 59: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መጎልበት ያላቸው እምነት 60

## Boxes

ሣጥን1: የሴት ልጅ ግርዛት ምደባ 9
ሣጥን2: የአፋር እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ስለመምጣቱ 31
ሣጥን3: የወደፊት ባለቤታቸውን የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ በሚመለከት የአፋር ወንድ ልጆች እና የወጣት ወንዶች ምርጫዎች 35
ሣጥን4: የሶማሊያ ወላጆች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያላቸው እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ይመስላል 41
ሣጥን5: የሶማሊ ታዳጊና እና ወጣት ወንዶች የወደፊት ባለቤታቸው የግርዛት ሁኔታ ምርጫዎች በተመለከተ 43
ሣጥን6: በአፋር ክልል የህጻናት ጋብቻ በጊዜ ሂደት 50
ሣጥን7: የህጻናት ጋብቻ በሶማሌ በጊዜ ሂደት 51

## Tables

ሠንጠረዥ 1: መጠናዊ ናሙና 12
ሠንጠረዥ 2: አይነታዊ ናሙና 12

# አጽህሮተ ሪፖርት

## መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ለማስቆም በቁርጠኛነት እየሰራ ይገኛል። አገሪቱ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ሁለቱንም አሠራሮች የከለከለ ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ያላት ሲሆን፤ እነዚህን ጎጂ ልማዶች ለማስወገድ የተነደፉ በርካታ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችም አሉ። ምንም እንኳን እነዚህ የቁርጠኝነት ተግባራት እና የመንግስት እና የልማት አጋሮቹ ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶች ቢኖሩም የስራው ግስጋሴ በጣም ያልተመጣጠነ እና የታለመለትን ግብ ለማሳካት በጣም ዝግመት የታየበት ነው። በእርግጥ በቅርቡ የተካሄደው የኢትዮጵያ የስነ-ህዝብ እና ጤና ጥናት እንዳረጋገጠው በአፋር እና በሶማሊ አርብቶ አደር ክልሎች ሁለቱንም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከመፍታት አንፃር ያለው እንቅስቃሴ በጣም አናሳ እንደሆነ፤ የሴት ልጅ ግርዛት መጠንም በነበረበት እንደቀጠለ እና የህጻናት ጋብቻ መጠን እየጨመረ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል።

ይህ የጥናት ሪፖርት ድብልቅ ዘዴዎችን (መጠናዊ እና አይነታዊ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን) በመጠቀም ለበርካታ ዓመታት የተካሄደ የረጅም ጊዜ ጥናት አካል ነው። ሪፖርቱ በ 2024 ከአፋር ሁለት ዞኖች እና ከሶማሊ ሁለት ዞኖች የተሰበሰበ መረጃን መሰረት በማድረግ የታዳጊ እና ጎልማሳ ሴቶችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቀም በተለይም የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻ ችግሮችን ይመለከታል። ህጻናት

## የምርምር ዘዴ

ሥርዓተ-ፆታ እና ታዳጊዎች፡ ዓለም አቀፍ መረጃ ላይ ትኩረቱን ያደረገው የጌጅ (GAGE) ፕሮግራም በ2024 መጀመሪያ ላይ በአፋር እና ሶማሊ ክልሎች የመጠናዊ እና አይነታዊ ቀይጥ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ጥናት አድርጓል። ሴቭ ዘ ችልድረን የተሰኘው ህፃናት አድን ድርጅት ሥራውን የሚያከናውንባቸውን ቦታዎች መሠረት በማድረግ ከሁለቱም ክልሎች ከእያንዳቸው በሁለት ዞኖች ውስጥ ከሚገኙ ከሦስት ወረዳዎች መረጃ ተሰብስቧል። የጌጅ ፕሮግራም የአጋማሽ ጊዜ መጠናዊ ጥናት ናሙና 1,881 እድሜያቸው በ12 እና 21 ዓመት መካከል ያሉ ታዳጊዎች እና ወጣት ጎልማሶች እና 1,912 የወላጆችን አካትቷል። የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲመረጡ ከሁለቱም ክልሎች እኩል በሚባል ደረጃ ብዛት ያላቸው እና በሴቭ ዘ ችልድረን ፕሮግረም ተሳታፊ የሆኑትን እና ያልሆኑትንም ማህበረሰቦች አካቷል።

በተጠያቂዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የተሰበሰቡ የዳሰሳ ጥናት መረጃዎች ሰፊ እና የሴት ልጅ ግርዛትን፣ ህጻናት ጋብቻን፣ ትምህርትን፣ የኑሮ መተዳደሪያን፣ የፆታዊ እና ስነ-ተዋልዶ ጤናን፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ እና የውሳኔ አሰጣጥን፣ የስርዓተ-ፆታ ደንቦች እና በሴቭ ዘ ችልድረን ፕሮግራም ተሳታፊ ለሆኑት ማህበረሰቦች የፕሮግራም ተሳትፎን የሚመለከቱ ሞጁሎችን ያካተተ ነበር። ለአይነታዊ መረጃ የጥናት ናሙና አመራረጥም ከሁለቱም ክልሎች እና በፕሮግራሙ ከሚሳተፉ እና ከማይሳተፉ ማህበረሰቦች ውስጥ እኩል ብዛት ያላቸውን አካቷል። መረጃው 65 ታዳጊ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች፣ 67 ታዳጊ ወንድና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች፣ 102 የወላጆች እና 113 ከቀበሌ (ከማህበረሰብ)፣ ከወረዳና ከክልል የተውጣጡ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎችን ያካተተ ነበር።

## ቁልፍ ግኝቶች

በአጠቃላይ የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ ጥናት ግኝቶቹ ከመነሻ ጊዜ ጥናቱ ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በታዳጊ ዕድሜ ላይ ባሉ ወጣቶች እና በእናቶች ሕይወት ላይ ከፍተኛ ለውጦች መኖራቸውን ያሳያሉ። ምንም እንኳን ከእነዚህ ለውጦች መካከል ጥቂቶቹ (ለምሳሌ፡ ለድርቀ ተጋላጭነት) በክልሎች ተመሳሳይ ቢሆኑም ሌሎቹ ደግሞ በአንድ ክልል ብቻ ተወስነዋል (ለምሳሌ፡ በሶማሊ ክልል የጋብቻ ዕድሜ መቀነስ) ወይም በአንድ ክልል ውስጥ በአንድ ዞን (ለምሳሌ፡ በአፋር የሀሪ ረሱ ዞን [ዞን 5] ) ውስጥ ግጭት ተከስቷል።

## ቤተሰብ፣ የኑሮ መተዳደሪያ እና ማህበራዊ ጥበቃ

በአፋር ክልል (70%) እና በሶማሊ ብዛት ያላቸው (45%) አባወራዎች የእንስሳት እርባታ አሁንም ዋና የገቢ ምንጭ ቢሆንም በሁለቱም ክልሎች ውስጥ ጥቂት አባወራዎች ብቻ በአሁኑ ጊዜ ወቅታዊ ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉና የተለያዩ የገቢ ማግኛ ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙ ይህ የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ የጥናት አረጋግጧል። በተለይም ይህ ጉዳይ የታየው በሶማሊ ክልል ሲሆን ብዙ አባወራዎች (38%) በግብርና ብቻ ሳይሆን በንግድም (14%) ጭምር የሚተዳደሩ ናቸው። ይህ በአካባቢው ያለውን የምግብ ዋስትና እጦት ደረጃንም የሚያሳይ ሲሆን በአፋር (35%) ያለው ከስተተ ከሶማሊ (20%) ሲነጻጸር ወደእጥፍ በሚጠጋ ደረጃ ከፍ ያለ ነው። በሁለቱም ክልሎች የምግብ ዋስትና እጦት በአየር ንብረት ለውጥ፣ በድርቅ፣ በጎርፍ፣ በበሽታ እና የእንስሳት ሀብትን እና የሰብል ምርትን በሚያወድሙ ወራሪ ዝርያዎች ምክንያት ተባብሷል። በከፋ ድርቅ ወቅት አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ቢደረግም (በተለይም በአፋር በሀሪ ረሱ (ዞን 5) የማህበራዊ ጥበቃው ካለው ፍላጎት ጋር የተመጣጠነ አለመሆኑን የጥናቱ ተሳታፊዎች አረጋግጠዋል።

## ትምህርት

የፕሮግራም አጋማሽ ጥናቱ እንዳመለከተው የትምህርት ፍላጎት ከፍ ያለ ቢሆንም በሁለቱም ክልሎች በሁለቱ ፆታዎች መካከል ከፍተኛ የፍላጎት ልዩነት አለ። የልጃገረዶች እና የወጣት ሴቶች ፍላጎት ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ያነሰ ነው። የወላጆች ለሴቶች ልጆቻቸው ያላቸው የትምህርት ፍላጎት ለወንዶች ልጆቻቸው ካላቸው ያነሰ ነው። በተማሪዎች የትምህርት ቅበላም በሁለቱም ክልሎች የፆታ ልዩነት አለ። ከወንድ እኩዮቻቸው



የ15 ዓመቷ ልጅ በደረቅ ወንዝ ውስጥ ካለ ጉድጓድ ውሃ ስትቀዳ፤ አፋር፣ ኢትዮጵያ © ናታሊ በርትራምስ/ጌጅ 2024

ጋር ሲነፃፀር፣ በሁለቱም ክልሎች በአፋር (79% ለ 66%) እና በሶማሊ (47% ለ 58%) ያሉ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ለትምህርት የመመዝገባቸው ዕድላቸው በጣም አናሳ ነው፤ ትምህርት ተመዝግበው እየተከታተሉ ከነበሩት ውስጥም የማቋረጥ እድላቸው በእጥፍ ይበልጣል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በስምምነታቸው እንደገለጡት የዚህ ዋነኛ ምክንያት ወላጆች ልጃገረድ ልጆቻቸው የቤት ውስጥ እና የእንክብካቤ ስራ እንዲያከናውኑ ያላቸው ፍላጎት ቢሆንም የህጻናት ጋብቻ፣ የልጃገረዶች በለጋ ዕድሜያቸው የሚያጋጥማቸው ለከፍተኛ አደጋ ተጋላጭነት እና ህገ-ወጥ ስደትም ብርቱ ሚና አላቸው፡፡

በተጨማሪም በአንጻራዊነት መደበኛ ትምህርት በአፋርና በሶማሊ አዲስ በመሆኑ መካከለኛ ደረጃ (7ኛ እና 8ኛ ክፍል) እና ሁለተኛ ደረጃ (ከ9-12ኛ ክፍል) ትምህርት ቤቶች አሁንም በብዛት በከተማዎች ብቻ (በተለይም በአፋር በሐሪ ራሱ [ዞን 5] ስለሚገኙ ብዙ ታዳጊዎች ትምህርት ለመማር እድሜያቸው ቢደርስም በርቀቱ ምክንያት እንዳይማሩ ይገደባሉ፡፡ እንስሳትን የመጠበቅ የስራ ሃላፊነት ስላለባቸው ብዙ ልጆች በልጅነት እድሚያቸው ወደ ትምህርት ስለማይገቡ፤ አብዛኛዎቹ በትምህርት ላይ ያሉት ተማሪዎችም እድሜያቸው በሚማሩበት የክፍል ደረጃ ከሚጠበቀው በላይ ነው፡፡ ይህ ማለት በጣም ጥቂት ልጆች ብቻ (በተለይም ልጃገረዶች) ናቸው ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በላይ የመማር እድል ያላቸው፡፡ ድርቅ በሁለቱም ክልሎች እና ግጭት (በተለይ በአፋር በሀሪ ረሱ [ዞን 5] የህብረተሰቡ አባላትን እና መምህራንን ከትምህርት ይልቅ ህልውናን እንዲያስቀድሙ ስለሚያስገድዳቸው የወጣቶችን የትምህርት ተደራሽነት የበለጠ ገድቧል፡፡

## የሴት ልጅ ግርዛት

በተደረገው ጥናት ግኝት መሰረት የሴት ልጅ ግርዛት በወጥነት በሁለቱም ክልሎች - በአፋር (99%) እና በሶማሊ (80%) - ሆኖ እንደቀጠለ ተደርሶበታል፡፡ ልጃገረዶች የሚገረዙበት ጊዜ ልዩነት ቢኖርም በጥናቱ በናሙናነት የተካተቱ የሶማሊ ታዳጊ ልጃገረዶች ሁሉም እንዳልተገረዙና ሆኖም ግን ከ 14 ዓመት በላይ ከሆኑት ውስጥ 96% የሚሆኑት ግርዛት ተፈፅሞባቸዋል፡፡ የሴት ልጅ ግርዛት አይነት በሁለቱም ክልሎች በተወሰነ ደረጃ አከራካሪ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ምላሽ ሰጪዎች (በተለይ በከተማ አካባቢዎች) አሁን ያሉ የግርዛት ድርጊቶችን የሚረዱት እንደ ባህላዊ ድርጊቶች አንጂ እንደ ሱና (በሀይማኖት የተፈቀደ) አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ በሁለቱም ክልሎች አብዛኞቹ ታዳጊ ልጃገረዶች እና ሴቶች በአፋር ክልል (78%) እና በሶማሊ (100%) ግርዛት (ብልትን የማጥበብ ድርጊት) ቢፈፀምባቸውም ከማጥበቡ በፊት የሚወገደው የሥጋ መጠን እና የማጥበብ ደረጃው ግን በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ እየተሻሻለ ወይም እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ይህም ሌሎች የእድሜ አቻዎችን በማነፃፀር ላይ የተመሰረተ እና በሃይማኖት መሪዎች መካከል ከብልት ላይ ስለሚወገደው ስጋ አይነት ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች በመኖራቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በክልሉ መንግስታት ተቀባይነት ባያገኝም ማንኛውንም አይነት የሴት ልጅ ግርዛትን ስለሚከለክለው የብሔራዊ ህግ ያለው ግንዛቤ ግን ውስን ነው፡፡

ምንም እንኳን በሁለቱ ክልሎች መካከል ግርዛትን በሚመለከት የተወሰነ ልዩነት ቢኖርም - የአፋር የጥናቱ ተሳታፊዎች ከሶማሊ ኣቻዎቻቸው ሲነጻፀር ባጠቃላይ የሴት ልጅ ግርዛት የሚያደርሰውን ጉዳት የበለጠ ቢገነዘቡም፣ ድርጊቱም እንዲቀጥል ያላቸው ድጋፍ አነስተኛ ቢሆንም እና

“ቀላል” የሚባሉ የሴት ልጅ የግርዛት አይነቶችን ቢቀበሉም፣ በሁለቱም ክልሎች ለድርጊቱ ያለው ድጋፍ አሁንም ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነው። በአፋር 40% ወጣቶች እና የሶማሊ 46% ወጣቶች የወደፊት ሴት ልጆቻቸውን ለማስገረዝ እንዳሰቡ ተናግረዋል። ይሁን እንጂ በአፋር ያሉ ምላሽ ሰጪዎች በሱማሌ ክልል ከነበሩት በተሻለ የሚያስከትለውን አደጋ ተገንዝበዋል፤ በድርጊቱ ለመቀጠል ያሳዩት ድጋፍም በአንጻራዊነት አነስተኛና በታናናሾቻቸው ላይ ለማስቀጠል ያሰቡትም በአይነቱ መለስተኛ የሆነውን የሴት ልጅ ግርዛት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛት በሃይማኖት (በተለይ በሶማሊ ክልል) ያስፈልጋል፣ ባህል ከማስቀጠልም አንፃር አስፈላጊ ነው፣ የሴት ልጆችን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ይቆጣጠራል እና ለትዳርም ተስማሚ ያደርጋቸዋል በሚለው እምነት ነው። የሶማሊ ክልል ጎልማሳ ሴቶች እና ለትዳር ወይም ለመሞሸር የተዘጋጁት ልጃገረዶች የሴት ልጅ ግርዛትን ብቻ ሳይሆን በግርዛት አይነቱ የሴት ብልት ማጥበብን እንደሚደግፉ ገልፀዋል። ይህም ሙሽሪት ከትዳር በፊት ከሚደረገው የወሲብ ግንኙነት ንፁህ መሆኗን ለማረጋገጥ ብቸኛው መንገድ እንደሆነ ገልፀዋል።

በሶማሊ ክልል ጥናቱ በተወሰነ ማስረጃ እንዳረጋገጠው ሁለቱም (ሴትን ልጅ የመግረዝ ሂደቱን እና በግርዛት ምክንያት የጠበበውን ብልት መፍታት/ማስፋት) ድርጊት በህክምና እንደሚደገፍና፤ የሴት ልጅ ግርዛት ሙሉ በሙሉ የሴቶች ጉዳይ እንደሆነ አዋቂዎች እና ወጣቶች ይስማማሉ፤ የመንግስት ባለስልጣናት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞችም አይነት 1 (ቀላል የሚባለውን) የሴት ልጅ ግርዛት ብዙውን ጊዜ ተቀባይነት እንዳለው ስምምነታቸውን ገልጸዋል። በጥናቱ እንደተገኘው፣ በአፋር ክልል የሴት ልጅ ግርዛት አይነት ውሳኔ ላይ አባቶች አንዳንድ አስተያየት እንዲሰጡበት ይበልጥ ተሰሚነት ያላቸው ሲሆን፤ አንዳንድ የጥናቱ ተሳታፊዎችም (በአውሲ ረሱ [በዞን 1] የከተማ አካባቢዎች ብቻ) ድርጊቱን ሙሉ በሙሉ ለመተው ፈቃደኞች መሆናቸው ተረጋግጧል።

## የህጻናት ጋብቻ

የፕሮግራም አጋማሽ ዳሰሳ ጥናቱ በተካሄደነት ወቅት በናሙናነት የተካተቱት ታዳጊዎች አማካይ እድሜ ገና 16 ዓመት ያልሞላቸው ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ (5% የሚጠጉት) የዳሰሳ ጥናቱ በተደረገነት ጊዜ ያገቡ ነበሩ። በሁለቱም ክልሎች (በተለይም ራቅ ባሉ የገጠር ቀበሌዎች) ልጃገረዶች የወር አበባ ማየት እንደ ጀመሩ ወይም 15 ዓመት ሲሞላቸው የመጋባት እድላቸው ከፍተኛ ነው። አብዛኞቹ ወጣቶች በሁለቱም ክልሎች– በአፋር (84%) እና ሶማሊ (83%) አብዛኞቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ከ18 ዓመታቸው በፊት ነው ብለው ያምናሉ። በዋናነት የታዳጊ ሴቶች የህጻናት ጋብቻ በሁለቱም ክልሎች የተለመደ ቢሆንም ለዚህ ድርጊት ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደረጋቸው መስኤዎች ግን በጣም የተለያዩ እንደሆኑ ተረጋግጧል። የአፋር ክልል ምላሽ ሰጪዎች እደገለፁት በወላጆች ምክንያት የህጻናት ጋብቻ የተለመደ እንደሆነና፣ ወላጆች አሁንም በዋነኛነት “አብሱማ” የሚባለዉን የጋብቻ ባህል እንደሚከተሉ፤ በዚህም መሰረት የትዳር አጋሮች በእናቶች በኩል የአጎት ልጆች መሆናቸውን ገልፀዋል። ይሁን እንጂ ታዳጊ ሴቶች (እና አስተማሪዎቻቸው)



የ17 ዓመት ልጃገረዶች በቀሎ እዬፊለፊሉ፣ ሶማሌ፣ ኢትዮጵያ © ናታሊ በርትራምስ/ጌጅ 2024

የተሻለ የመደበኛ ትምህርት ዕድል በማግኘታቸው፤ በአሁኑ ወቅት ጋብቻቸው (18 አመት አስኪሞላቸው) እንዲዘገይ እና የሚፈልጉትን የትዳር አጋር ለመምረጥ የመሞገት አቅማቸው እያደገ እንደመጣ ለመረዳት ተችሏል። በሶማሊ የሃይማኖት መሪዎች ተጋቢዎች ከህግ አንፃር ልጆች (ከ18 ዓመት በታች) ቢሆኑም ጋብቻቸውን የማፅደቅ መብት እንዳላቸው ገልፀው፣ የታዳጊ ሴቶች እና ወንዶች የህጻናት ጋብቻ የበለጠ እየተለመደ መምጣቱን የጋብቻ ዕድሜም እየቀነሰ የመጣ ድርጊት መሆኑን እና ያለድሜ ጋብቻ የሚፈፀመው በራሳቸውን በታዳጊዎቹ ፍላጎት መሆኑን ተስማምተውበታል። ለተጠቀሰው ችግር ዋናው ምክንያት በሞባይል ስልኮች የታዳጊ ሴቶች እና ወንዶች እርስ በርስ መስተጋብር (ግንኙነት) እየጨመረ በመምማቱ እና ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታ የመምጣት ምጣኔቸው እያደገ በመምጣቱ እንደሆነ ተጠኝዎች ተናግረዋል። በሁለቱም ክልሎች ጎልማሶችም ሆኑ ወጣቶች በአገር አቀፍ ህግ መሰረት የህጻናት ጋብቻ ህገ-ወጥ እንደሆነ ያላቸው ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ ነው።

## የልጃገረዶችና ሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም

በአፋር እና በሶማሊ የጥናት ቦታዎች፤ በተለይም በብዙ የገጠር ማህበረሰቦች ዘንድ ስር በሰደደው የወንዶች የበላይነት በሚንፀባረቅበት የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች ምክንያት የልጃገረዶች እና ሴቶች አቅም የተገደበ ነው። ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ከታዳጊና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ያነሰ የመንቀሳቀስ መብት እና በጣም የተገደበ ድምጽ አላቸው። በተመሳሳይ ሴቶች በንብረት ላይ ያላቸው ቁጥጥር እና በገንዘብ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብት በተለይም በአፋር (ሴቶች በከብት ንግድ ላይ አብዛኛውን ጊዜ አለመሳተፋቸው) ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር በጣም ውስን ነው። ምንም እንኳን ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ገቢ የሚያገኙበት እና ለቤት ውስጥ ፍጆታ የራሳቸውን አስተዋጾ የሚያበረክቱነት ሁኔታ እያደገ ቢመጣም፣ በሴት ልጆች እንቅስቀሴ ላይ ከወንድ ልጆች የበለጠ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግባቸው እንደሚገባና ባልም ሚስቱን የመቆጣጠር ስልጣን (በሀይልም ቢሆን) እንዳለው ተቀራራቢ የሆነ ወጥ ስምምነት በአፋርም ሆነ በሶማሊ፣ በወጣቶች እና በወላጆች መካከል አለ።

ወላጆችህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻ ናትየጥናቱ መደምደሚያዎችና እና አንድምታዎች- ለስራ አቅድ እና ፖሊሲ

ከዚህ ሰፊ ጥናት ግኝቶቻችን በመነሳት የህጻናት ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት የወጣው ብሄራዊ ፍኖተ-ካርታ ግቦች እንዲሳኩ ከተፈለገ ለኢትዮጵያ መንግስት እና ለአጋሮቹ (ሴቭ ዘ ችልድረን የተሰኘውን የህጻናት አድን ድርጅትን ጨምሮ) የሚከተሉትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት እንጠቁማለን። በታዳጊ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶችን እና ሴቶችን ለውጦች በፍጥነት ለመከታተል የሚያስፈልጉትን ተዋናዮች እና በሚሰጣቸው ኃላፊነት ውስጥ የሚኖራቸውን ልዩ ተግባራት እናሳያለን፤ ጥረቶቹም በጥሩ ሁኔታ የተቀናጁ እና እርስ በርስ የሚደጋገፉ መሆናቸውን እናስገነዝባለን።

- የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ስለሚከለክለው ህግ ያለው ግንዛቤ ውስን በመሆኑ፣ እንደ አፈጻጸም ሁሉም፣ የፍትህ ሴክተር በጎጂ ልማዶች ላይ ሀገራዊ ህጎችን የማስተዋወቅ እና የማስከበር ጥረቶችን ማጠናከር አለበት።
- ገደብ የለሽ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች የልጃገረዶችን እና የሴቶችን የትምህርት፣ የሥራ እና ውሳኔ የመስጠት እድል ስለሚገድቡ እና በመጨረሻም ሁለቱንም የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ስለሚያበረታቱ - በሁሉም ደረጃዎች የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክተር እነዚህን እምነቶች እና ልምዶች በቀጥታ ለመፍታት ጥረቶችን ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
- አባቶች፣ ወንድሞች፣ ወንድ እኩዮቻቸው፣ ወንድ ጓደኞች እና ባሎች ልጃገረዶችን እና ሴቶችን የሚጎዱ ሰፊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን (የሴት ልጅ ግርዛትን ጨምሮ) ለማስቀጠል የበኩላቸውን ሚና ስለሚጫወቱ መንግስት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የወንዶችን አመለካከት እና ተግባራት ለመቀየር ተባብረው መሥራት አለባቸው።
- የልጃገረዶች እና የሴቶችን ህይወት የሚገድቡ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች የማህበረሰቡን እና የመሪዎችንም እነዚህን ደንቦችን የመለየት እና የመፍታት አቅም ስለሚገድቡ፣ በህፃናት እና ስርአተ-ጾታ ላይ ያተኮሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እነዚህን እምነቶችን እና ልምዶችን ለመቀየር፣ አካባቢያዊ ኃላፊነት የሚወስዱ ፈቃደኛነትና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ለማገዝ እና የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ለማስቀም ከታዳጊ ወጣቶች እና ጎልማሶች ጋር መስራት አስፈላጊ ነው።
- ሴት ልጆች ከወንዶች ይልቅ ከትምህርት የመገለል እድላቸው ከፍተኛ በመሆኑ የትምህርት ሴክተሩ ሁሉም ልጃገረዶች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ቢያንስ እስከ መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጨረሻ ድረስ በተቻለ መጠን ደግሞ እስከ ሁለተኛ ደረጃ እንዲያጠናቅቁ ጥረቶችን ማጠናከር ይኖርበታል።
- ዓለም አቀፍ መረጃ እንደሚጠቁመው የህጻናት ጋብቻን ለመከላከል ከሁሉ የተሻለው መንገድ ልጃገረዶች በተቻለ መጠን ትምህርት ቤት እንዲቆዩ ማድረግ፤ ማህበራዊ ጥበቃ ማድረግ (ለምሳሌ የትምህርት ቤት መመገብ፣ የገንዘብ ድጋፎች) ቤተሰቦች ሴት ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ እና ጋብቻንም እንዲያዘገዩ ለማበረታታት ጥቅም ላይ መዋል አለበት።
- በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች እና ሴቶች የራሳቸውን ገቢ የማግኘት እድሎች እጅግ በጣም ውስን በመሆኑ የግብርና እና የሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፎች ያላገቡ እና ያገቡ ሴቶችን የመተዳደሪያ

አማራጮችን ለማስፋፋትና ለማብዛት ጥረቶችን ከፍ ማድረግ አለባቸው።

- ግርዛት የተፈፀመባቸው ልጃገረዶች እና ሴቶች ብዙውን ጊዜ የዕድሜ ልክ ህመም እና ኢንፌክሽን ስለሚያጋጥማቸው፣ የሴት ልጅ ግርዛትም በህክምና የመታዷግ አዝማሚያ እያደገ በመምጣቱ፤ የህጻናት ጋብቻ እና የወጣቶች እርግዝና ችግሮችን ለመፍታት  በክልል እና በወረዳ ደረጃ ያሉ የጤና ጥበቃ ቢሮዎች የጤና ባለሙያዎች የመፍትሄው አካል እንዲሆኑ ጥረታቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው።
- የአፋር እና ሶማሊ ክልሎች በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን በመቀነሱ ረገድ ያሳዩትን እድገት እስካሁን ባለማረጋገጣቸው የክልል መንግስታት መሪዎች የሴቶችን እና የሴቶችን ህይወት የሚያሻሽል ማህበራዊ ለውጥን እንዲሁም ሰፋ ያለ የእድገት ውጤቶችን በማስተዋወቅ ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው።
- የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ሀይማኖታዊ ትእዛዝ ስለሚታይ እና የህጻናት ጋብቻ በሀይማኖት ተቀባይነት ያለው (እንዲያውም ተመራጭ) ተደርጎ ስለሚታይ የመንግስት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ከኃይማኖት አባቶች ጋር ተቀራርበው የማበረታታት ስራ በመስራት ጉዳቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመቀነስ  አስፈላጊ እንደሆነ፣ ለዚህም የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች ምን እንደሆኑ እና "ሱና" (የሚፈቀድ) በሚለው ስር እንደማይካተቱ፣ በመጨረሻም እነዚህን ጎጂ ልማዶች መተው እንደሚያስፈልግ ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ጎሳ እና ባህል የአፋር እና የሶማሊ ማንነቶች ዋና መሰረት ሲሆኑ፤ ለሴት ልጅ ግርዛት እና የህጻናት ጋብቻ ቀጣይነትም እንዲሁ ዋና ጉዳዮች በመሆናቸው የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች ልጃገረዶችን እና ሴቶችን የሚጎዱ እምነቶችን እና ድርጊቶችን ለመቀየር ከጎሳ መሪዎች ጋር ተቀራርበው መስራት ያስፈልጋል።
- የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ለማስቆም የተቋቋመው ብሄራዊ ጥምረት ይህን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ለማስቆም በልዩ ሁኔታ የተቀመጠ በመሆኑ ጥረቶችን ለማስቀጠል እና ችግሩን ለመቅረፍ የሚደረገውን ጥረት ለማፋጠን አባላት በጋራ በመሆን አዳዲስ የለውጥ መንገዶችን መክፈት እና አዳዲስ የለውጥ አንቀሳቃሽ ሀይቾን በመለየት በየደረጃው የሚደረገውን ችግሩን የመቅረፍ ጥረቶችን መደገፍ አስፈላጊ ነው።
- የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ማስቀረት ሃብትን እና ተከታታይነት ያለው የረጅም ጊዜ ጣልቃገብነት የሚጠይቅ በመሆኑ የልማት አጋሮች በጠንካራ የምርምር ማስረጃዎች በመታገዝ በፕሮግራም ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው።


የ18 ዓመቷ እናት እና ሁለት ልጆቿ፣ ሶማሌ፣ ኢትዮጵያ © ናታሊ በርትራምስ/ጌጅ 2024

# መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ እድሜ ጋብቻን ለማስቆም ቁርጠኛ ነው። አገሪቱ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ሁለቱንም ልማዶች የሚከለክል ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ሲኖራት፣ በተጨማሪም የ2013 በሴቶች እና ህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ብሄራዊ ስትራቴጂ እና የድርጊት መርሃ ግብር እንዲሁም የ2019 ሀገር አቀፍ ወጪ የተደረገበት  በ2025 ያለ ዕድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም የተነደፈ ፍኖተ ካርታ አላት። ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን  እና የዘላቂ ልማት ግቦች ፈራሚ ነች። ስምምነቶቹ የሴት ልጅ ግርዛትና ያለ ዕድሜ ጋብቻ የልጃገረዶችንና የሴቶችን መብት የሚጻረር መሆኑን ተገንዝበው እነዚህ ጎጂ ልማዶች እንዲወገዱ ጥሪ ያቀርባሉ።

ምንም እንኳን ይህ ቁርጠኝነትና የመንግስት እና የልማት አጋሮቹ ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶች ቢኖሩም የለውጥ ሂደቱ ያልተመጣጠነ እና የታለመለትን ግብ ከማሳካት አንጻር በጣም አዝጋሚ ነው። በእርግጥም በአፋርና በሶማሌ አርብቶ አደር ክልሎች (መንግስት በማደግ ላይ ያሉ ክልሎች ብሎ ይፈርጃቸዋል) እነዚህን ጎጂ ልማዶች ከማስቀረት አንጻር መሻሻል የታየበት መሆኑን፣ የሴት ልጅ ግርዛት መጠን ባለበት መሆኑን፣ እና የህጻናት ጋብቻ መጠን እንዲያውም እየጨመረ ሊሆን እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ህጻናትይህ የጥናት ሪፖርት ድብልቅ ዘዴዎችን (መጠናዊ እና አይነታዊ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም) ለበርካታ ዓመታት የተካሄደ የረጅም ጊዜ ጥናት አካል ነው። ሪፖርቱ በ 2024 ከአፋር ሁለት ዞኖች እና ከሶማሊ ሁለት ዞኖች የተሰበሰበ መረጃን መሰረት በማድረግ የታዳጊ እና ጎልማሳ ሴቶችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልበትን በተለይም የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ እድሜ ጋብቻ ችግሮችን ይፍትሻል።  ሪፖርቱ በ 2024 ከአፋር ሁለት ዞኖች እና ከሶማሊ ሁለት ዞኖች የተሰበሰበ መረጃን መሰረት በማድረግ የታዳጊ እና ጎልማሳ ሴቶችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልበትን በተለይም የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ እድሜ ጋብቻ ችግሮችን ይመለከታል።

የጌጅ የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ የጥናት ናሙና በሚመለከት ወደ 4,000 የሚጠጉ ወጣቶች እና የወላጆች (ከየክልሉ 1,000 የሚጠጉ አባወራዎች፣ እያንዳንዳቸው ታዳጊ ወጣት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ ያላቸው) እና ከ150 በላይ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች ከአገራዊና አለም አቀፋዊ ዒላማዎች አንጻር ንድፎችን ለማስቀመጥና እና መሻሻልን ለመከታተል በሚያስችል ሁኔታ በጥንቃቄ ተመርጠዋል።

ሪፖርቱ የአፋርን እና የሶማሊን አውድ ለማስተዋወቅ በጥናቱ ዳራ ክፍል ይጀምራል። ሪፖርቱ የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ ጥናት ንድፈ-ሐሳብ ቅንብርና ናሙና እና ዘዴዎችንም ያቀርባል። ግኝቶቹ በጭብጥ ቀርበዋል። ከእነዚህም መካከል ቤተሰብ፣ መተዳደሪያ እና የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነት፤ ትምህርት፤ የሴት ልጅ ግርዛት፤ የህጻናት ጋብቻ፤ እና የልጃገረዶችና የሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም ማጎልበት ሲሆኑ የክልል ሁኔታ በእያንዳንዱ ጭብጥ ስር ተመላክቷል። ሪፖርቱ የጥናቱን አንድምታዎችን ለስራ እቅድ እና ፖሊሲ በማቅረብ ይደመድማል።


በቅርቡ በተፈጠረው ግጭት ጉዳት ከደረሰበት በኋላ እንደገና እየተገነባ ያለው ጤና ጣቢያ፣ አፋር፣ ኢትዮጵያ © ናታሊ በርትራምስ/ጌጅ 2024

# የጥናቱ ዳራ

## የአፋርና የሶማሊ ክልላዊ አውዶች

ሁለቱም የአፋር እና የሶማሊ ክልሎች በዋነኛነት በረሃማ እና በዝናብ ሰርጭት ምክንያት ከቦታ ቦታ ወቀታዊ እንቅስቃሴ ለሚያደርጉ የአርብቶ አደሮች መኖሪያ ናቸው። በተደጋጋሚ የአየር ንብረት ለውጥ-ተኮር ድርቅ እና ጎርፍ (Oxfam, 2016; Management Entity, 2021; UNOCHA, 2022; UNICEF, n.d.a; n.d. b) በጣም ተጎጂ ናቸው። በዋነኛነት በሀብት እጥረት ምክንያት ሁለቱም ክልሎች በቅርብ አመታት በአስር መቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ያፈናቀሉ ተደጋጋሚ ሁከቶች ተጎድተዋል (Tadesse et al.፣ 2015፣ UNOCHA፣ 2022፣ UNICEF፣ n.d.a; n.d.b; Ethiopia Peace Observatory, n.d. )። ምንም እንኳን በአፋር (24%) እና በሶማሊ (23%) የድህነት መጠን ተመሳሳይ ቢሆንም፣ በድህነት ክስተት ሁኔታ ትልቅ ልዩነቶች አሉ (ብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን፣ 2017፣ የዓለም ባንክ፣ 2020)። በአፋር በከተማ የሚኖሩት በገጠር ካሉት በጣም የተሻሉ ናቸው (ibid.)። በሶማሊ ግን ሁኔታው ይህ አይደለም - ማለትም የከተማ ድህነት ከገጠር ድህነት በመጠኑ ከፍ ያለ ነው (ibid.)። በሁለቱም የአፋር (95%) እና የሶማሊ (98%) ክልሎች እስልምና እጅግ በጣም ብዙ በሆነው ህዝብ ይተገበራል (Østebø, 2023)።

በዋነኛነት በሁለቱም ክልሎች ህዝቡ በየቦታው ተበታትኖ የሚኖርና ከቦታ ቦታ ተንቀሳቀሽ ስለሆነ-ሁለቱም ምክንያቶች የመደበኛ ትምህርት አሰጣጥን የሚያወሳስቡ እና ፍላጎት ላይ ጫና የሚያሳድሩ በመሆናቸው - በአፋር እና በሶማሊ የትምህርት ተደራሽነት ከሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ጋር ሲወዳደር በጣም ዘግይቷል (Jackson, 2011፣ Wodajo, 2014፣ Woldesenbet, 2015; Muhumed, 2017; Alemu and Solomon, 2019)። በአፋር ክልል በ2020 በትግራይ ክልል በተከሰተው ግጭት የትምህርት ተደራሽነት የበለጠ ተገድቧል። ይህም በ2021 ሁለተኛ አጋማሽ ላይ በአፋር ትምህርት ቤቶች በስፋት እንዲዘጉ አድርጓቸዋል፣ ብዙ ቤተሰቦችም በልጆቻቸው ትምህርት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ በማያስችል ድህነት ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል (Presler-Marshall et al., 2024a)። የትምህርት ሚኒስቴር (2023) ሪፖርት እንደሚያመለክተው በአገር አቀፍ ደረጃ 6ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ህጻናት 71% ሲሆኑ፣ በአፋር ግን 29% እና በሶማሊ 54% ህጻናት ብቻ ናቸው። በተጨማሪም በሁለቱም ክልሎች ያሉ ልጃገረዶች የትምህርት ዕድል የማግኘት እድላቸው ከወንዶች አንጻር ሲታይ በጣም ያነሰ ሲሆን፣ ምክንያቱም በባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና መዋቅራዊ ሁኔታዎች መካከል ባለው ውስብስብ መስተጋብር ምክንያት ልጃገረዶች ትምህርት ቤት የመመዝገብ እድላቸው አነስተኛ እና የማቋረጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው (Jackson, 2011; Wodajo, 2014; Muhumed, 2017፤ Dessalegn et al., 2020፤ Goshu et al., 2021)። የትምህርት ሚኒስቴር (2023) እንደዘገበው በአፋር ክልል 26% ልጃገረዶች እና 31% ወንዶች ልጆች 6ኛ ክፍልን ያጠናቅቃሉ። በሶማሊ ክልል የማጠናቀቅ መጠኑ ከፍ ያለ ቢሆንም፣ የፆታ ስብጥር ክፍተቱ የበለጠ ነው - 49% ልጃገረዶች እና 60% ወንዶች ናቸው። በሁለቱም ክልሎች በአፋር (13%) እና በሶማሊ (14%) ሴት ልጆች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመዝገብ ያልተለመደ ጉዳይ ነው (ibid.)።

በአፋር እና በሶማሊ ክልል ያሉ ልጃገረዶች እና ሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በስፋት የተመሰረተው በአርብቶ አደርነት ሲሆን፣ በመንግስት ጥረቶች ህዝቡ በተፋሰሶች ሰፍሮ የመኖር ዘይቤ እንዲከተል በመበረታታቱ በመስኖ ሰብል ማምረት የሚቻል ሲሆን መንግስታዊ አገልግሎት ለመስጠት ቀላል እና ቀልጣፋ ነው (Abebe, 2014; Haji and Legesse, 2017; Mahamoud and Ahmed, 2019)። በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሴቶች የገቢ ተደራሽነት ከቁም እንስሳት ጋር ብቻ የተያያዘ ነው (Inkermann, 2015; Dessalegn et al., 2020; Ridgewell and Flintan, 2007)። በሶማሊ ክልል በብዛት በሚገኙት በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች፣ የሴቶች የኑሮ መተዳደሪያ ዘዴዎች ንግድን ጭምር ያካትታሉ። የሴቶች ገቢ ትንሽ ቢሆንም ከወንዶች የበለጠ አስተማማኝ ሊሆን ይችላል (Oxfam, 2016; Gurmu, 2018; Balehey et al., 2018; Mahamoud and Ahmed, 2019; Teka et al., 2019; United States International Development (USAID), 2021)።

የሴት ልጅ ግርዛት የሚፈጸምበት እድሜ እንደየክልሉ ቢለያይም ድርጊቱ በአፋርም ሆነ በሶማሊ በአብዛኛው የተለመደ ነው። አንዳቸውም የክልል ህጎችን ከሀገራዊ ክልከላዎች ጋር እንዲጣጣሙ አላደረጉም። በቅርቡ በተካሄደው የኢትዮጵያ የስነ-ሕዝብ እና ጤና ዳሰሳ (ኢ.ዲ.ኤች.ኤስ) ጥናት፣ በሴቶች የመራቢያ እድሜ (15-49)- በአፋር (91%) እና በሶማሊ (99%) የሴት ልጅ ግርዛት እንደተፈጸመ አረጋግጧል (CSA and ICF, 2017)። በአፋር እና በሶማሊ ክልል በኢትዮጵያ የስነ-ሕዝብ እና ጤና ዳሰሳ (ኢ.ዲ.ኤች.ኤስ) ጥናት ውስጥ ለናሙና የተወሰዱ ልጃገረዶች ቁጥር አነስተኛ [1] ነው በሚለው ማሳሰበያ መሰረት፣ የወጣት ሴቶች መጠን (ከ15-19 ዓመት ዕድሜ ያላቸው) 91% እና 95%[2] እንደቀደም ተከተላቸው ከፍተኛ ነበር። የሴት ልጅ ግርዛት በአፋር እና በሶማሊ ከሌሎቹ ክልሎች በበለጠ የተለመደ ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም ወደ ጫፍ የሄደ ነው። የኢትዮጵያ የስነ-ሕዝብ እና ጤና ዳሰሳ ጥናት እንደዘገበው አብዛኞቹ ከ15 ዓመት በላይ የሆናቸው ልጃገረዶች እና ሴቶች በአፋር (64%) እና በሶማሊ (73%) ብልታቸውን "የተሰፉ" ናቸው (ሣጥን 1ን ይመልከቱ፣ አራቱን የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች

1 በ 2016 የኢትዮጵያ የስነ-ሕዝብ እና ጤና ዳሰሳ (EDHS) ጥናት ላይ የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ጥያቄዎች የተጠየቁት ከ15-19 አመት የሆናቸው ልጃገረዶች ቁጥር በአፋር 139 እና በሶማሊ 152 ብቻ ነው።

2 እድሜያቸው ከ15-19 የሆነው የልጃገረዶች ክልላዊ አሃዞች የ EDHS መረጃን መሰረት ያላደረገ እና በራሳቸው በአጥኚዎቹ ስሌት የተቀመጠ ነው።

ያብራራል። ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆኑ ልጃገረዶች ተገርዞ የመሰፋት መጠናቸው በቅደም ተከተል 64% እና 33% (ibid.) ነበር። በአፋርም ሆነ በሶማሊ ክልል የሴት ልጅ ግርዛት በሀይማኖትና በባህል ሊከወን የሚገባ ተግባር እንደሆነ ይታመናል።

በርግጥም በርካታ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከግርዛት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የጤና አደጋዎች በአጠቃላይ በደንብ ቢታወቁም ድርጊቱን ማስወገድ ከሚያስከትላቸው ማህበራዊ መዘዞች ወይም መቀጠላቸው ከሚያስገኛቸው ማህበራዊ ጥቅሞች ጋር ሲነፃፀሩ ብዙ ጊዜ ብዙም ትርጉም የሌላቸው እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ (Asmani and Abdi, 2008; Flintan, 2008; Andarge, 2014; Abathun et al., 2016, 2018; Gebremariam et al., 2016; Mohamud et al., 2016; Abdisa et al., 2017; Adinew and Mekete, 2017; Getanehe, 2017; የጎልማሶች መሰረተ ትምህርትbe et al., 2020; Presler-Marshall et al., 2022a)።

አፋር እና ሶማሊ ከኢትዮጵያ ክልሎች መካከል ጎልተው የሚታዩት የቤተሰብ ህጋቸውን በመከለስ የህጻናት ጋብቻን መከልከል እንዳለባቸው ነው (McGavock, 2021)። ይህ ማመንታት በሁለቱም አካባቢዎች ባለው ከፍተኛ የህጻናት ጋብቻ ላይ ይንጸባረቃል። እንደ ዩኒሴፍ ዘገባ፣ በ2016 የኢ.ዲ.ኤች.ኤስ. ከ20-24 ዕድሜ ክልል ውስጥ ከነበሩት ሴቶች መካከል 67 በመቶው በአፋር እና 55% በሶማሊ ክልል 18 ዓመት ሳይሞላቸው ትዳር መሥርተው ነበር። ይህም በአገር አቀፍ ደረጃ 40% (UNICEF, n.d.a; n.d.b.b) በተጨማሪም, Elezaj et al. (2019) የኢ.ዲ.ኤች.ኤስ መረጃን በመጠቀም፣ ከ15-17 ዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ልጃገረዶች መካከል የህጻናት ጋብቻ የመከሰቱ አጋጣሚ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ2000 ቀንሷል ቢልም (9 በመቶ ዝቅ ብሏል) በአፋር በ6 በመቶ ነጥብ እና በሶማሊ በ7 በመቶ ነጥብ እየጨመረ የመጣ ይመስላል። የህጻናት ጋብቻ ውስጥ ያሉት እነዚህ መመሳሰሎች በተለይ የጋብቻ ልማዶች የተለያዩ በመሆናቸው ትኩረት የሚስቡ ናቸው። በአፋር ክልል ልምምዱ እንደየዞኑ ስለሚለያይ ሴት ልጅ በባህላዊ መንገድ አብሱማ (የእናት ወንድም ልጅ) የምታገባ ሲሆን ስለ ጋብቻ ጊዜ ወይም ስለምታገባው ሰው ምንም አይነት ውሳኔ መስጠት አይፈቀድላትም (Jones et al., 2016; Dessalegn et al., 2020; Presler-Marshall et al., 2020)። በሶማሊ አብዛኞቹ ልጃገረዶች በሚፈልጉት ጊዜ እና የመረጠትን ያገባሉ (ምንም እንኳን ቀድመው እንዲያገቡ የቤተሰብ እና ማኅበራዊ ጫና ቢኖርም) (Lelieveld, 2011; Woldesenbet, 2015; CSA and ICF, 2017)። በቅርቡ ከአፋር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በ2021 በሰሜን ኢትዮጵያ የተከሰተው ግጭት የሴቶች ልጆችን የህጻናት ጋብቻ የመጋለጥ እድላቸውን የበለጠ እንዳባባሰው፣ ይህም በሁለቱም የህጻናት ጋብቻ የጨመረ ሲሆን ልጃገረዶችም የሚያገቡበት እድሜ ቀንሷል (Presler-Marshall et al.፣ 2024 a)።



በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምትገኝ ሴት ታዳጊ፣ ሶማሌ፣ ኢትዮጵያ © ናታሊ በርትራምስ/ጌጅ 2024

### ሣጥን1: የሴት ልጅ ግርዛት ምደባ

የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) የሴት ልጅ ግርዛትን በአራት ዓይነት ይመድበዋል (WHO, 2024)፡፡ ዓይነት 1 ክሊቶሬክቶሚ ተብሎ የሚጠራው ቂንጥርን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድን ያካትታል፤ ዓይነት 2፣ ኤክሲሽን ተብሎ የሚጠራው ትንሹን ከንፈር እና/ወይም ከፍተኛ (ብዙውን ጊዜ ከቂንጥር በተጨማሪ) መወገድን ያካትታል፡፡ ዓይነት 3፣ ኢንፌቡሊሽን ተብሎም የሚጠራው፣ የጾታ ብልትን ቀዳዳ መጥበብን የሚያካትት ውጫዊውን የሴት ብልት አካል በማስወገድ እና በመገጣጠም (በተለምዶ በጠባሳ ቲሹ) የተረፈውን ሥጋ ነው፡፡ ዓይነት 4 በልጃገረዶች ብልት ላይ የሚደርሱ ሌሎች ጉዳቶችን ያጠቃልላል፡፡

በኢትዮጵያ የሴት ልጅ ግርዛት ብዙውን ጊዜ "የሴት ግርዛት" እየተባለ የሚጠራው ከወንዶች ግርዛት በተለየ ጉዳት ብቻ እንጅ ምንም የጤና ጥቅሞች የለውም፡፡ የቅርብ ጊዜ የስነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ ጥናት ይህንን የምደባ ዘዴ አይከተልም፡፡ ይልቁንስ "የተቆረጠ፣ ሥጋው ያልተወገደ"፣ "የተቆረጠ፣ ሥጋው የተወገደ" እና "ተሰፍቶ የተዘጋ" (CSA and ICF፣ 2017) መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል፡፡

የጥናት ግኝቶቻችንን ለማብራራት በብዙ ሙስሊም ማህበረሰቦች ውስጥ፣ የሴት ልጅ ግርዛት አይነት በሁለት ምድቦች ብቻ ይከፈላል: ሱና (የተፈቀደ) እና ሃራም (የተከለከለ)፡፡ በ2023 በሙስሊም ምሁራን የወጣው ፈትዋ ኢንፌቡሊሽን /አይነት 3 ሀራም እና ክሊቶሬክቶሚ /አይነት 1 ሱና ተቀባይነት እንዳለው አስቀምጠዋል፡፡


# የጥናቱ ንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፍ

እያደገ የመጣውን የወጣቶችን ደህንነት እና እድገት መረጃ ለይ በመመስረት፤ በጌጅ ንድፈ-ሐሳባዊ ማዕቀፍ (GAGE consortium፣ 2019) ላይ እንደተገለጸው፣ ይህ ጥናት አጠቃላይ እይታን ይከተላል፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረውም በችሎታዎች፣ የለውጥ ስልቶች እና አውዶች የእርስ በርስ ትስስር ሲሆን፣ በዚህም ታዳጊ ልጃገረዶች አሁን እና ወደፊት ሙሉ አቅማቸውን እውን እንድያደርጉ ውጤታማ መንገዶችን በመለየት ለመደገፍና አቅማቸውን ለማጎልበት ነው (ምስል 1 ይመልከቱ)፡፡ ይህ አተያይ ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ማጎልበት በጣም የተሳሰሩ መሆናቸውን እና የተለያዩ ሁኔታዎች ወጣት ልጃገረዶች የሚያጋጥሟቸውን አደጋዎች እና እድሎች እንዲሁም ለውጥን የማስፋፋት ስልቶችን እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይገነዘባል፡፡

የዚህ አተያይ ዋናው ጠቀሜታ ችሎታዎችን ለመግለጽ አቃፊ ሲሆን በመጀመሪያ በ Amartya Sen (1984; 2004) እና Martha Nussbaum (2011) እና Naila Kabeer (2003) የተሻሻለው ውስብስብ የሥርዓት-ፆታ ተለዋዋጭነትን በቤተሰብ እና በህብረተሰብ ደረጃዎች በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት ያስቻለ በመሆኑ ነው ፡፡ ይህ ማዕቀፍ ጠቃሚ ጉዳዮችን (assets)– ኢኮኖሚያዊ ፣ ሰብአዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ውስጣዊ ስሜት እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ለመመርመር በሚያስችል ሁኔታ ሰፊ መደበኛ መዋቅር ሆኖ በማደጉ የግለሰቦችን "የመሥራት እና የመሆን" ትርጉም ያላቸውን መንገዶች የማሳካት ችሎታን ያሳድጋል፡፡ የብቃት ስሜት፣ በድርጊቶች እና በውጤታቸው ላይ ስሜት መቆጣጠር አፅንዖት ይሰጣል፤ በማይለዋወጡ ውጫዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይሆን በግለሰብ ችሎታ፣ እውቀት እና ተሰሚነት ላይ ባሉ አቅሞችን መጨመር ላይ ያተኩራል.

ሁለተኛው የጥናናታችን ንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፍ የጥናቱ አውድ ነው፡፡ የእኛ ሞዴል ወጣት ሴቶች በተለያዩ የህይወት ደረጃዎች ላይ የሚገጥኙና የተለያዩ ፍላጎቶች እና ተግዳሮቶች እንዳሏቸው በመገንዘብ በቤተሰባቸው፣ በማህበረሰቡ፣ በንዑስ ብሄራዊ እና በአገራዊ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር በመገንዘብ ልጃገረዶችን በማህበራዊ-ሥነ-ምህዳር ማዕቀፍ ውስጥ ያስቀምጣል፡፡

የመጨረሻው አካል፣ የለውጥ ስልቶች፣ ልጃገረዶች የሚያጋጥሟቸው እውነታዎች አቅማቸውን ለማጎልበት መንገዶችን እና ሁኔታቸውን ለማሻሻል ያየሚረዱ ስልቶች እንደሚቀርቡ እውቅና ይሰጣል፡፡ የእኛ ማህበራዊ-ስነ-ምህዳራዊ አካሄድ በልጃገረዶች አቅም እና አጠቃላይ ደህንነት ላይ ለውጥን ማበረታታት በበርካታ ደረጃዎች የተቀናጁ የጣልቃ ገብነት ስልቶችን እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡ ይህም ልጃገረዶችን፣ ቤተሰቦቻቸውን እና ማህበረሰባቸውን የሚደግፉ ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን ማመጣጠን እና እንዲሁም ለስርአት ለውጥ መጣርን ያካትታል፡፡


ውጤት፡ ልጃገረዶች እና ሴቶች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቅም እአጎልብተዋል፤ የሴት ልጅ ግርዛትን መቋቋም ችለዋል
ችሎታ
ትምህርትና
ጤና፣ ስነ ምግብ፣ ስርዓተ ጾታና ስነ ተዋልዶ ጤና
አካላዊ ምሉዕነት
ስነ ልቦናዊ ደህንነት
የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት
ድምጽና ውሳኔ ሰጪነት
አውዶች
አለማቀፍ
ብሔራዊና ክልላዊ መንግስታት
ብሔራዊና ክልላዊ መንግስታት
ማህበረሰብ (ገጠርና ከተማ)
ቤተሰብ
ታዳጊ ልጃገረዶች (10-19)
ለውጥ
ልጃገረዶችን ማብቃት
ሴቶችን ማብቃት
ሴቶችን ማብቃት
የማህበረሰብ ማህበራዊ ልማዶች ለውጥ ማበረታታት
ከሃይማኖት መሪዎች ጋር አብሮ መስራት
ሴቶችን ማብቃት
ችግር፡ ልጃገረዶችን ለማብቃት እና የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመቀነስ መደረግ ስላለበት ነገር በቂ እውቀት አለመኖር


# ናሙና እና ዘዴዎች

ይህ ሪፖርት በ2024 መጀመሪያ ላይ በአፋር እና በሶማሊ ክልሎች የተካሄዱ የቅይጥ ዘዴዎችን ጥናት ያሳያል። በሦስት ወረዳዎችና በሁለት ዞኖች በየክልሉ መረጃዎች ተሰብስበዋል (ምሥል 2 ይመልከቱ)። እነዚህም ቦታዎች በአፋር አይሳይታ (አውሲ ረሱ ዞን [ዞን 1]) እና ሰሙሮቢና ሀዴሌላ (ሀሪ ረሱ ዞን [ዞን 5]) ወረዳዎችን ያጠቃልላል። በሶማሊ በዳሮር (ጃራር ዞን) እና በሐርሸንና ጎልጃኖ (ፋፋን ዞን) ወረዳዎች ላይ ጥናትና ምርምር ተካሂዷል።

የእኛ የፕሮግራም አጋማሽ የጥናት መጠናዊ ናሙና 1,881 ወጣቶች እና ወጣት ጎልማሶች (በ12 እና 21 መካከል ያሉ ጥናቱ ሲደረግ) እና 1,912 የወላጆችን ያካትታል[3] (ሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ)። ናሙናው በአፋር 961 ወጣቶች፤ በሶማሊ 920 ወጣቶች እና ማህበረሰቦች 933 ወጣቶች መካከል 933 ወጣቶች የሴቭ ዘ ችልድረን ፕሮግራም ተጠቃምዎች) እና 957 ወጣቶች የሴቭ ዘ ችልድረን ፕሮግራም የማይጠቀሙ በሚል እኩል ተከፋፍሏል ማለት ይቻላል። አብዛኛዎቹ ታዳጊ ወጣቶች (81%) እና አብዛኛዎቹ የወላጆች (90%) ሴቶች ነበሩ። በተጠያቂዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የተካሄዱ ጥናቶች ሰፊ ነበሩ፤ እንዲሁም በሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለ እድሜ ጋብቻ፣ በትምህርት፣ በአኗኗር ዘይቤ፣ በፆታዊ እና ስነ ተዋልዶ ጤና፣ የመንቀሳቀስ እና የውሳኔ አሰጣጥ፣ የስርዓተ-ፆታ ደንቦች እና የፕሮግራም ተሳትፎ (በፕሮግራም ማህበረሰቦች ውስጥ ብቻ) ሞጁሎችን ያካተተ ነበር። (Endale et al.፣ 2024a ይመልከቱ)። ከወላጆች ዳሰሳ ጥናቶች በተጨማሪም ስለ ቤተሰብ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እና በማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ውስጥ ተሳትፎን በተመለከተ ሞጁል አካትተዋል። ይህ ሪፖርት ገላጭ ስታቲስቲክስ ላይ የሚመረኮዝ ሲሆን፣ ለተለያዩ ምላሽ ሰጪዎች ቡድን ያቀርባል (ለምሳሌ ወንዶች ከሴቶች፣ ኢላማ እና ቁጥጥር)። አማካኝ ልዩነቶች በስታቲስቲካዊ ጠቀሜታ ሲገለጹ፣ $p<.05$ ይሆናል።

የእኛ መጠናዊ ናሙና በክልሎች በፕሮግራም ከታቀፉ እና በፕሮግራም ካልታቀፉ ማህበረሰቦች ተወስደዋል (ሠንጠረዥ 2 ይመልከቱ)። 65 ወጣት ልጃገረዶች እና ታዳጊ ሴቶች (ግማሾቹ ያገቡ)፣ 67 ታዳጊ ወንዶችና ወጣት ወንዶች (ግማሾቹ ባለትዳር[4])፣ 102 የወላጆች እና ከቀበሌ፣ ከወረዳና ከክልል የተውጣጡ 113 ቁልፍ መረጃ ሰጪዎችን ያካተተ ነው። በዋናነት በሁለቱም በአውሲ ረሱ [ዞን 1] እና በሀሪ ረሱ [ዞን 5] በአፋር፣ በሶማሊ፣ አይነታዊ ጥናት ሲደረግ፣ መረጃዎችን የሰበሰብነው በፋፋን ዞን ብቻ ሲሰሆን፣ በጃራርን አላካተተም። የአይነታዊ ጥናቱ መሳሪያዎች ከዳሰሳ ጥናቶች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጭብጦችን

ምስል 2: የምርምር ቦታዎች




3 ሁሉም የፕሮግራም አጋማሽ ጥናት ተሳታፊዎች በመነሻ ጥናቱ ላይ ተሳትፈዋል (ስለ መነሻ ጥናቱ ናሙና ዝርዝሮችን ለማግኘት አባሪ 1ን ይመልከቱ)። ከፕሮግራሙ ማቋረጥ በናሙና ውስጥ በመነሻ ደረጃ ላይ ከተገመተው (15%) ጋር ሲነፃፀር ውሱን እና ከተገመተው ያነሰ ነበር። ከጠቅላላው 2,042 የመነሻ ጥናት ዋና ምላሽ ሰጪ ወጣቶች፣ 1,890 የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ ጥናት ውስጥ ተሳትፈዋል። በተመሳሳይ፣ ከ2,042 የመጀመሪያ ደረጃ ምላሽ ሰጪዎች መካከል 1,912 የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች በክትትል እና ቃለ መጠይቅ ተሳትፈዋል። ፕሮግራሙን የማቋረጥ መጠን 7.4% ነበር እና እንደ አካባቢ እና ዕድሜ ትንሽ ይለያያል። በአፋር ክልል፣ አጠቃላይ የታዳጊዎቹ የማቋረጥ መጠን 5.9% (6.8% ከ15 ዓመት በታች ለሆኑት የፕሮግራሙ መነሻ ላይ እና 5.2% ዕድሜያቸው 15 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ነበር። በሶማሊተመሳሳይ አሃዞች በቅደም ተከተል 9.8%፣ 10% እና 9.3% ነበር። የቤትስብ አስተዳዳሪዎች የማቋረጥ መጠን 6.3% (4.5% በአፋር እና 8.2% በሶማሊ) ነበር።

4 የጋብቻ ውሳኔ አሰጣጥን በተሻለ ሁኔታ እንድንመረምር አይነታዊ የጥናት ናሙናው በተለያየ ቡድን ውስጥ ያልተመጣጠነ ቁጥር ያላቸው ያገቡ ወጣቶችን አካትቷል።

ሠንጠረዥ 1: መጠናዊ ናሙና

| | | አፋር | | | ሶማሊ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጠቅላላ | በፕሮግራም የታቀፉ | በፕሮግራም ያልታቀፉ | ጠቅላላ | በፕሮግራም የታቀፉ | በፕሮግራም ያልታቀፉ | ጠቅላላ |
| ታዳጊዎች | ጠቅላላ | 961 | 478 | 483 | 920 | 454 | 466 | 1881 |
| | ሴት | 824 | 413 | 411 | 705 | 346 | 359 | 1529 |
| | ወንድ | 137 | 65 | 72 | 215 | 108 | 107 | 352 |
| የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች | ጠቅላላ | 976 | 476 | 500 | 936 | 462 | 474 | 1912 |
| | ሴት | 897 | 450 | 447 | 833 | 414 | 419 | 1730 |
| | ወንድ | 79 | 26 | 53 | 103 | 48 | 55 | 182 |

አካተዋል፤ ነገር ግን ለበለጠ ጥልቅ ዳሰሳ (እንደገና በተጠኝዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ) የግል አመለካከቶች፣ የማህበረሰብ ደንቦች፣ ልምዶችን መቀየር እና ለውጦችን ለማበረታታት ወይም ለማፈን ስለሚሰሩ ተዋናዮች ምልከታዎች መቃኘት ተችሏል (Presler-Marshall et al., 2024d)።

አይነታዊ መረጃ ትንተና አንጻር ሁሉም ቃለመጠይቆች ተቀርጸው እና ተተርጉመዋል፣ ከዚያም ቀደም ሲል በተብራራው የጥናቱ ንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፍ በመረጃ የተደገፈ የጭብጥ (አቃፊ ሀሳብ) ኮድ መጽሐፍን  በመከተል የሶፍትዌር ፓኬጅ MAXQDA በመጠቀም ኮድ ተደርጓል።

ጥናት ከመጀመሩ በፊት የኢትዮጵያ ሶሺዮሎጂስቶች፣ ማህበራዊ ሰራተኞች እና አንትሮፖሎጂስቶች ማህበር (ESSSWA) የሳይንስና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር እውቅና ካለው አካል የምርምር ስነ-ምግባር ኮሚቴ አገራዊ የምርምር ስነ ምግባር ግምገማዎችን እንዲያካሂድ የስነ-ምግባር ክሊራንስ ተቀብሏል። ሁሉም ቃለ-መጠይቆች እንደ ግርዛት ባሉ ስሜታዊ ጉዳዮች ላይ ጨምሮ ከተጋላጭ ታዳጊ ወጣቶችና እና ጎልማሶች ጋር በአግባቡ እንዲገናኙ የሰለጠኑ ነበሩ። ቃለ መጠይቁ ከመጀመሩ በፊት ተሳታፊዎች የመሳተፍ መብት እንዳላቸው (በቃለ መጠይቁ ወቅት በማንኛውም ጊዜ ፈቃዳቸውን የማቋረጥ መብታቸውን ጨምሮ) እና ስለ ሚስጥራዊነት እና ደህንነቱ ተነግሯቸዋል። በመረጃ የተደገፈ ስምምነት (ከ18 አመት በታች ለሆኑ ህጻናት) እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነት (ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አዋቂዎች) ከሁሉም ተሳታፊዎች ተገኝቷል።

ሠንጠረዥ 2: አይነታዊ ናሙና

| | አፋር | ሶማሊ | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|
| ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች | 33 (ግማሽ ያገቡ) | 32 (ግማሽ ያገቡ) | 65 |
| ታዳጊ ልጆች እና ወጣት ወንዶች | 32 (ግማሽ ያገቡ) | 35 (ግማሽ ያገቡ) | 67 |
| እናቶች | 36 | 34 | 70 |
| አባቶች | 16 | 16 | 32 |
| ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች | 58 | 55 | 113 |
| ጠቅላላ | **175** | **172** | **347** |


የአጎቷን ልጅ ያገባች የ15 ዓመት ልጃገረድ፣ አፋር፣ ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም

# ግኝቶች

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የምርምር ግኝቶቻችን- ለጥናት በታዎች ብቻ የሚተገበር እንጂ ለሁሉም አፋር እና ሶማሌ አይደለም - ቤተሰብ፣ ኑሮ እና የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነት ፣ ትምህርት፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለ እድሜ ጋብቻ፣ እና የልጃ ገረዶችን እና የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም ማጎልበት በሚሉ ጭብጦች የተደራጁ ናቸው። በጭብጦች ውስጥ ግኝቶች በመጀመሪያ ለአፋር ከዚያም ለሶማሊ ቀርበዋል።

## ቤተሰብ፣ መተዳደሪያ እና የማህበራዊ ጥበቃ መዳረሻ

### አፋር

በጥናት በታዎች የመደበኛ ትምህርት በአንፃራዊነት አዲስ በመሆኑ[5]፣ የወላጆች ጥናት እንዳመለከተው የቤተሰብ ኃላፊዎች 4% ብቻ ማንበብና መፃፍ የተማሩ ሲሆኑ፣ ማንበብና መፃፍ በከተሞች በአውሲ ረሱ [ዞን 1] (8%) ከሀሪ ረሱ (ዞን 5) (3%) ይበልጣል። የዳሰሳ ጥናቱ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ጊዜ በአጠቃላይ ቤተሰቦች ለግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት (5%) የተለመደ አይደለም (ምስል 3 ይመልከቱ)። በአውሲ ረሱ [ዞን 1]፣ አብዛኞቹ አባወራዎች (67%) ሙሉ በሙሉ በመኖሪያ ቀዬ ሰፍረዋል። በ27% ከሚሆኑት ቤተሰቦች ውስጥ፣ አንዳንድ አባወራዎች በየወቅቱ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ። በሀሪ ረሱ [ዞን 5]፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ኩነቶች በጣም ተቀራራቢ ናቸው፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (52%) ቤተሰቦች ሙሉ በሙሉ የሰፈሩ እና ከግማሽ በታች (44%) የተወሰኑ አባላት ብቻ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ።


የወላጆች የዳሰሳ ጥናት በዞኖች ውስጥ ያሉ የቤተሰብ ንብረቶች ባለቤትነት ላይ ትልቅ ልዩነቶችን ለይቷል። በአውሲ ረሱ (ዞን 1) (97%) ያሉ የአፋር አባወራዎች/እማዎራዎች ከሀሪ ረሱ (ዞን 5) (67%) የመሬት የባለቤትነት ዕድላቸው ከፍተኛ ነበር (ምስል 4 ይመልከቱ)። በሀሪ ረሱ (ዞን 5) (95%) አባወራዎች በአውሲ ረሱ ካሉት (ዞን 1) (80%) ይልቅ ትናንሽ እንስሳት (በአብዛኛው ፍየሎች) የባለቤትነት ዕድላቸው ከፍተኛ ነበር። የትላልቅ የቁም ከብቶች (በአብዛኛው ላሞች) ባለቤትነት በዞኖች ተመሳሳይ ነበር። በእኛ ናሙና ውስጥ በአማካይ ቤተሰብ 20 ፍየሎች እና 6 ላሞች ነበሩት።

ዋናውን የቤተሰብ ገቢ ምንጩን እንዲለዩ ሲጠየቁ የእንስሳት እርባታ በአፋር ጥናት በታዎች 70% የወላጆች ሪፖርት አድርገዋል። ምላሾቹ እንዲሁ በዞን ተለያዩ ነበሩ (ምስል 5 ይመልከቱ)። በአውሲ ረሱ (ዞን 1) 51% ቤተሰቦች በዘላቂነት የመኖር ዕድላቸው ከፍተኛ የሆነባቸው እና መሬት የማግኘት ዕድላቸው ከፍተኛ የሆነባቸው የወላጆች ከሀሪ ረሱ (ዞን 5) 7% የበለጠ የሰብል ልማት ሪፖርት የማድረግ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በሀሪ ረሱ ያሉ አባወራዎች በከብት እርባታ (86% ከ 38%) የበለጠ የመተማመን ዕድል ነበራቸው።

በሁለቱም ዞኖች - ከድርቅ አንፃር የሚገርም ባይሆንም - አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የአፋር የወላጆች ባለፈው ዓመት በቤተሰቦቻቸው የምግብ ዋስትና እጦት እንደነበረ ተናግረዋል (ምስል 6 ይመልከቱ)። ነገር ግን ባለፈው ሳምንት የምግብ ዋስትና ስጋት በአውሲ ረሱ (ዞን 1) 13% ከፍተኛ ነበር።ይህም እንደ ሀሪ ረሱ [ዞን 5] ከዳሰሳ ጥናቱ ከመካሄዱ ሳምንታት በፊት 2% ድርቅ የመወገድ ሁኔታ አልታየበትም።


በማህበራዊ ጥበቃ ረገድ አብዛኛው የአፋር የወላጆች (87%)፣ በሁለቱም ዞኖች፣ ቤተሰባቸው ከምርታማ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እርዳታ አግኝቶ አያውቅም (ምስል 7 ይመልከቱ)። ከእነዚህ ውስጥ እና በከፊል አሁንም በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ላይ በመረጃ አሰባሰብ ወቅት የተከሰተውን ድርቅ የሚያንፀባርቅ

ምስል 3: ለከብት ግጦሽ ፍለጋ የቤተሰብ ስደት፣ አፋር





5 አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች የተገነቡት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥ ነው።


ምስል 4: የቤተሰብ ቋሚ ንብረት፣ አፋር




ምስል 5: የቤተሰብ ዋና የገቢ ምንጭ፣ አፋር





ምስል 6: የምግብ ዋስትና፣ አፋር




ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአውሲ ረሱ (71%) ከሀሪ ረሱ (ዞን 5) (13%) ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው። በትምህርት ቤት ምገባ በአውሲ ረሱ ከሀሪ ረሱ (74% ከ 56%) የበለጠ የተለመደ ነበር። ለክልሉ ዋና ከተማ ሰመራ ቅርብ በሆነው በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ውስጥ ካሉት 75% ጋር ሲነፃፀር በሀሪ ረሱ (ዞን 5) ውስጥ ምንም አይነት የወላጆች የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን እንዳላገኙ ሪፖርት አድርገዋል።

የአይነታዊ ጥናት ግኝቶች የዳሰሳ ጥናቱን ግኝቶች ለማስፋት እና ብዙ ትርጉም ያላቸውን ጉዳዮች በጥንቃቄ ለመመርመር እና ለመረዳት አስችለዋል። አብዛኞቹ በጥናት ቦታዎች የሚገኙ የወላጆች፣ በአውሲ ረሱም ሆነ በሀሪ ረሱ የሚኖሩት፣ ምንም እንኳን የቁም እንስሳት ይዞታቸው ትንሽ ቢሆንም፣ መደበኛ ኑሯቸውም ስረ-መሰረቱ ግብርና ቢሆንም፣ አርብቶ አደር መሆናቸው ተረጋግጧል። የአውሲ ረሱ [ዞን 1] አንድ አባት

ምስል 7: ማህበራዊ ጥበቃ የማግኘት ዕድል፣ አፋር




"እኔ አርብቶ አደር ነኝ፣ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም ከብት አረባለሁ" ብለዋል፡፡ የሀሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ እናት እንደገለፁት የሰብል እርሻ እየተስፋፋ ባለበት ወቅት መስኖ ለማልማት የሚያስፈልገውን ገንዘብ እና ጥረት ያላቸው ብቻ ገቢን ማባዛት ይችላሉ፡፡ መስኖ ለመስራት ለምፈልጉ ገንዘብ ላላቸው ሰዎች ብዙ ስራ ይጠይቃል፡፡

ሌላዋ የዚሁ ዞን ነዋሪ እናት አክለውም ሰብል የሚያመርቱ እንኳን ከብቶቻቸውን እንደ ሴፍቲኔት ይመለከቷቸዋል፡፡ ምክንያቱም ሰብል ካልተሳካ ፍየል ለምግብነት ሊሸጥ ይችላል፡፡

> የእርሻ ምርቱ ቤተሰብን ለመመገብ በቂ ካልሆነ እንስሳትን እንሸጣለን እና ገንዘቡን ምግብ እና ሌሎች ነገሮችን ለመግዛት እንጠቀምበታለን..

የሁለቱም ዞኖች የወላጆች እና ታዳጊ ወጣቶች በአጽንኦት እንደተናገሩት የአየር ንብረት ለውጥ ሁለቱንም የእርሻ ስራ አይነቶች (የከብት እርባታ እና ሰብል ልማት) በጣም አስተማማኝ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል፤ ምክንያቱም ድርቅና ጎርፍ የከብት እርባታ እና ምርትን ቀንሷል፡፡ ድርቅ እና ጎርፍ ከብቶች ለበሽታ ተጋላጭ እንዲሆኑ እና ወራሪ የእፅዋትና የእንስሳት ዝርያዎች እንዲስፋፋ አድርገዋል፡፡ የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆኑ እናት

> ዋናው መንስኤ በአካባቢው የዝናብ እጥረት ያስከተለው ድርቅ ነው" በማለት አብራርተዋል፡፡ ድርቅ ሲከሰት… ለእንስሳቱ በቂ ምግብ ስለሌላቸው ለበሽታ ይጋለጣሉ፡፡

የዚሁ ዞን ነዋሪ የ20 አመት ወጣት የሚከተለውን ጨምሯል፡፡

> ባለፉት ሁለት አመታት ድርቅ ተከስቶ ነበር፡፡ ቤተሰቤንና በአጠቃላይ ማህበረሰቡን ክፉኛ ጎድቷል፡፡ ከድርቁ በተጨማሪ የእንስሳት በሽታዎችና መቸገሮችም ተከስተዋል፤ ይህም በእንስሳቶቻችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡፡

በግብርና ላይ ያለው ተፅዕኖዎችም ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የአውሲ ረሱ (ዞን 1) ነዋሪ የሆኑት አባት ጎርፍ ሰብሎችን ብቻ ሳይሆን አፈርን አጥቧል ወስዷል ብለዋል፡፡ "አንዳንድ ሰዎች ሰብል ለማልማት ቢሞክሩም የአዋሽ ወንዝ ሞልቶ የጎርፍ መጥለቅለቅ በመከሰቱ የሰዎችን የእርሻ መሬት በመሸርሸር ወስዷል፡፡" ሰብሎች ጤናማ ሆነው ሲጀምሩ እንኳን ብዙ ጊዜ ከመኸር ወቅት በፊት ይወድቃሉ፡፡ የሃሪ ረሱ እናት [ዞን 5] አክለውም፣

> እርሻው ጥሩ ምርት እየሰጠ አይደለም፤ ሰብሎች ማደግ ሲጀምሩ ጥሩ ሆነው ይታያሉ፤ በኋላ ላይ ተባዮች ሰብሎችን ያጠፋሉ እና ወደ ምርት ውድቀት ያመራሉ፡፡

በተለይ በሃሪ ረሱ [ዞን 5]፣ ምላሽ ሰጪዎች እንደገለፁት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተከሰተው ግጭት የእርሻ ስራን ይበልጥ እዳስተጓጎለና በኑሯቸው ላይ ብዙ ጉዳት አድርሷል፡፡ ሰብል የሚያመርቱት በእርሻቸው ለመስራት ፍርሀት ነበረባቸው፡፡ እንስሳት የሚያረቡ ደግሞ ወደ ገበያ ለመውሰድ ፈርተው ነበር፡፡ የሃሪ ረሱ እናት እንዲህ ብለዋል፣

> ከደህንነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች በእርሻ ቦታው መቆየት አልቻልንም፡፡ በእርሻ አካባቢ ሰው ሲያገኙ ሊጎዱ ወይም ሽጉጥ ሊተኩሱ ይችላሉ፡፡ ከደህንነት ስጋት የተነሳ እርሻችንን ሳንጠብቅ ቀርተናል፤ ወፎችም አወደሙት፡፡

የዚሁ ዞን አባት አክለውም፣ "ባለፉት ሁለት ዓመታት ሰዎች ከብቶቻቸውን ወደ ገበያ ለመውሰድ ፈርተው ነበር" ብለዋል፡፡

ከዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች ጋር በተገናኘ፣ ብዙ የአይነታዊ ጥናት ተሳታፊዎች እንደተናገሩት ቤተሰባቸው እና ማህበረሰባቸው ከመነሻው ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከምግብ ዋስትና ጋር ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆኑት አባት የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ጎርፍ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ቀበሌ አብዛኛው ህዝብ በምግብ እጥረት እና በረሃብ ተሠቃይቷል፡፡ ብለዋል፡፡

የሀሪ ረሱ (ዞን 5) አንድ አባት ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡፡፤

> በአካባቢያችን ላለፉት ሁለት ዓመታት የምግብ እጥረት ተከስቷል፤ ይህም የሆነው በድርቅ፣ በግጭት እና በተፈጠረው የመንገድ ምክንያትነው፡፡

እናቶች አክለውም ቤተሰቦች በቂ ምግብ ቢያገኙም እንኳን የአመጋገብ ጥራት ቀንሷል። የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆኑ እናት እንዲህ በማለት አብራርተዋል፣

ከዚህ በፊት ሩዝ እና ዳቦ እያፈራረቅን ልጆቹን እንመግብ ነበር…አሁን የምንሰጠው አንድ ዓይነት ምግብ ብቻ ነው።

ምላሽ ሰጪዎችም ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ለምግብ እጦት የተጋለጡ መሆናቸውን ጠቁመዋል። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የምትኖር የ15 ዓመቷ ልጃገረድ "ወንዶቹ ይብቃቸሁ" ስትል ተናግራለች፤ ምክንያቱም ሴቶች ከወንዶች በፊት እንዲበሉ መፍቀድ ነውር ነው።" በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የሚኖር የ18 ዓመት ወጣት "እናቴ ምግቡን [በቤተሰብ ውስጥ ላሉ] ለታናናሽ ልጆች ስጥታለች" በማለት ተናግሯል።

ምላሽ ሰጪዎች እንደሚሉት፣ የማህበራዊ ጥበቃ (የአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታን እና የሴፍቲኔትን ጨምሮ) ከፍላጎት ጋር እኩል አልሄደም። ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] የመጡ እናት እንዲህ ብለዋል፤

ከጦርነቱ በፊት [በሰሜን ኢትዮጵያ] የገንዘብ ድጋፍ ይደረግልን ነበር። በሴፍቲኔት ፕሮግራም ውስጥ ከተሳተፍንበት ጊዜ ጀምሮ ይከፍሉልናል… ከጁንታ ጦርነት በኋላ ወደ አካባቢያችን ምንም አይነት ድጋፍ አልተደረገም። ጦርነቱ ካበቃ በኋላ የአንድ ጊዜ የምግብ ድጋፍ 50 ኪሎ ግራም ስንዴ ብቻ አገኘን… ከዚያም እርሻውን ሰርተን ህይወታችንን እንድንመራ ነገሩን። ነገር ግን ከዚያ በኋላ የእርሻ መሬቱ በውሃ ተጥለቀልቋል።

በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ ተቋርጧል።
ምላሽ ሰጪዎች የትምህርት ቤት ምገባም ጠቃሚ እንደሆነ ነገር ግን በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ መቋረጡን ተናግረዋል። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የሚኖረው የ18 ዓመት ወጣት የሚከተለውን ብሏል።

በዚህ አመት 2024 (2016) በተጨማሪ በመጀመሪያው ሴሚስተር የትምህርት ቤት ምገባ ነበር፣ ነገር ግን በሁለተኛው ሴሚስተር ቆመ፣ ግን የትምህርት ቤቱ ምገባ ለምን እንደተስተጓጎለ እርግጠኛ አይደለሁም።


## ሶማሊ

የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ ላይ የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው 16 በመቶው የሶማሊ የወላጆች ማንበብና መፃፍ የተማሩ ሲሆኑ በጃራር የማንበብ እና የማንበብ ድግግሞሾች ከፋፋን (14%) ይበልጣል። በተጨማሪም ወቅታዊ ከቦታ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ ያልተለመደ መሆኑን አረጋግጧል። አብዛኛዎቹ የሶማሊ የወላጆች (78%) ምንም የቤተሰባቸው አባላት ለግጦሽ ሳር ፍለጋ ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ እንደማያደርጉ ተናግረዋል (ምስል 8 ይመልከቱ)። በፋፋን ያሉ አባወራዎች (83%) በጃራር ካሉት (66%) የበለጠ በአንድ ቦታ የመስፈር ዕድሉ ነበራቸው። ቤተሰቦች ወቅታዊ ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ለአንዳንድ አባላት ብቻ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ (10%) እና ለሁሉም አባላት (12%) መሰደድ የተለመደ ነበር።


በተጨማሪም የወላጆች ዳሰሳ ጥናት በዞኖች ውስጥ ያሉ የቤተሰብ ንብረቶች ባለቤትነት ላይ ትልቅ ልዩነቶችን ለይቷል። በፋፋን የሚገኙ አባወራዎች (59%)፣ አባወራዎች የበለጠ የሰፈሩበት እና የሰብል እርሻ እየሰፋ ባለበት በጃራር ካሉ አባወራዎች የበለጠ የመሬት ባለቤትነት ዕድላቸው ከፍተኛ ነበር፤ እርሻ ብዙም ያልተለመደ እና መሬት በብቸኝነት የጎሳ ባለቤትነት (14%) የተያዘ ነበር (ምስል 9 ይመልከቱ)። በፋፋን የሚገኙ የወላጆች (55%) በጃራር ካሉት (29%) የበለጠ ቤተሰቦቻቸው ትልቅ ከብቶች (ብዙውን ጊዜ ግመሎች) እንዳላቸው ሪፖርት አድርገዋል። የትናንሽ እንስሳት (ብዙውን ጊዜ ፍየሎች) ባለቤትነት በዞኖች (82%) እኩል የተለመደ ነበር። በሶማሊ ናሙና ውስጥ ያለው አማካይ ቤተሰብ 2 ግመሎች እና 18 ፍየሎች ነበሩት።

ዋናውን የቤተሰብ የገቢ ምንጭ እንዲለዩ ሲጠየቁ፣ የሶማሊ የወላጆች ምላሽ በዞኑ ይለያያል (ምስል 10 ይመልከቱ)። በጃራር የጥናት ቦታዎች የሚገኙ ወላጆች (30%) ከፋፋን (41%) ጋር ሲነጻጸር የሰብል እርሻ አነስተኛ ነበር። እንዲሁም ከፋፋን (18% በተቃራኒ 12%) የንግድ፣ ሽያጭ እና የግል ስራን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን፣ አብዛኛው የንግድ፣ ሽያጭ እና የግል ስራ ከኢትዮጵያ ይልቅ በሶማሊላንድ ከሚገኙ ገበያዎች ጋር የተያያዘ ነው። በሁለቱም ዞኖች የእንስሳት እርባታ የተለመደ ነበር (45%)።


ምስል 8: ለከብት ግጦሽ ሳር ፍለጋ የቤተሰብ ስደት፣ ሶማሊ



ምስል 9: በሶማሊ የቤተሰብ ንብረቶች





ምስል 10: የቤተሰብ ዋና የገቢ ምንጭ፣ ሶማሊ





በቤተሰብ ንብረቶች እና በኑሮዎች ላይ ልዩነቶች ቢኖሩም፣ የሶማሊ የወላጆች የምግብ ዋስትናን በተመለከተ ያላቸው ስጋት በዞኑ የተለየ አልነበረም። በሁለቱም በፋፋን እና በጃራር ካሉት የወላጆች አንድ አምስተኛ (20%) ባለፈው ሳምንት ስለምግብ ማግኘት ተጨንቀው እንደነበር ተናግረዋል (ምስል 11 ይመልከቱ)። ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ መቶኛ የምግብ ዋስትና እጥረት መኖሩን ሪፖርት አድርጓል።

በአጠቃላይ፣ በጃራር የሚገኙ የሶማሊ የወላጆች በፋፋን ካሉት የተሻለ የማህበራዊ ጥበቃ ተጂራሽነት እንዳላቸው ተናግረዋል። በሁለቱም ዞኖች ውስጥ ግማሽ የሚጠጉ (48%) አባወራዎች የሴፍቲኔት ያገኙ ቢሆንም፣ ከእነዚህ ውስጥ፣ በጃራር የወላጆች (64%) በአሁኑ ጊዜ በፋፋን ካሉት (58%) የበለጠ የሴፍቲኔት ተጠቃሚ የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው (ምስል 12 ይመልከቱ)። በሁለቱም ዞኖች ውስንነቶች ያሉበት የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን አቅርቦት እና የትምህርት ቤት ምገባ የተለመደ አይደለም። በፋፋን ከሚገኙት የወላጆች ጋር ሲነፃፀሩ የጃራር የወላጆች የተሻለ የጤና መድህን (4% ከ9 በመቶ በላይ) እና የትምህርት ቤት ምገባ (6% በተቃራኒ 12%) አላቸው።

ምስል 11: የምግብ ዋስትና በሶማሊ



ምስል 12: የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነት በሶማሊ




በሶማሊ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ አይነታዊ የጥናት መረጃ የተሰበሰበው በፋፋን ብቻ ነበር። በዞኑ የሰዎች መተዳደሪያ በጣም ልዩ ልዩ አይነት እንደሆነ ምላሽ ሰጪዎች ተናግረዋል። በዋነኛነት በሃርሽን የሚኖሩ ጥቂት አባወራዎች/እማዎራዎች በከብቶች ላይ ብቻ ጥገኛ ናቸው። ነገር ግን አብዛኛው አባወራ (በተለመደው የአየር ሁኔታ) የእንስሳት እርባታ እና ቢያንስ አንዳንድ ሰብሎች፣ እና ብዙዎቹ ገቢያቸውን (አንዳንድ ጊዜ በዓመት ለጥቂት ወራት ብቻ) ገንዘብ የሚያስገኝ የጉልበት በመስራት፣ በንግድ እና በማዕድን ቁፋሮ ያሟላሉ። አናሳ የሆኑት የሀርሽን ወረዳ የሀይማኖት አባቶች እንደሚሉት፣

> እዚህ ያሉት ሰዎች አርብቶ አደሮች ናቸው… ፍየሎች እና ግመሎች አሉን …በእርሻ ስራ ላይ ብዙም አናተኩርም… እፅዋትን የምንተክለው እንስሳቶቻችንን ለመመገብ ብቻ ነው።

የጎልጃኖ ወረዳ ነዋሪ የሆነ የ19 አመት ወጣት አክሎም በአርብቶ አደርነት ብቻ መተዳዳር ያለፈ ታሪክ ነው ሲል "ቀደም ሲል የህብረተሰቡ አብዛኛው መተዳደሪያ ከብት ማርባት ነበር" ሲል ተናግሯል። አሁን የ15 ዓመት የሀርሽን ነዋሪ ልጅ እንደተናገረው፣

> ይህ ልዩ ልዩ አይነት ነው - አንዳንዶች ከሰል በመሸጥ ኑሯቸውን ይመራሉ፣ አንዳንዶቹ በእንስሳት እርባታ፣ አንዳንዶች እስካሁን ድረስ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተዋል… ዋናው መተዳደሪያ ንግድ ነው፣ እንደ ትናንሽ ሱቆችን በመስራት ላይ ናቸው።

በፋፋን ወጣቶች እና የወላጆች ወደ ሀገር የሚላከው ገንዘብ ለቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ ህልውና ጠቃሚ መሆኑን ሪፖርት አድርገዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በአቅራቢያ ባሉ ከተሞች የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት እና ወደ ውጭ አገራት መካከለኛው ምሥራቅ እና አውሮፓ ጨምሮ ተሰደው የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት ገንዘብ በመላክ ይረዳሉ።የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነ የ12 አመት ልጅ ሪፖርት እንዳደረገው፣

> በከተማዋ ውስጥ አንድ ታላቅ እህት አለችን እና ትደግፈናለች… በሃርጌሳ (ሶማሊ ላንድ) ውስጥ የቤት ሰራተኛ ነች።

የ17 አመት ልጃገረድ ከሃርሽን አክላ እንደተናገረችው፣ "አባቴ ኖርዌይ ውስጥ ለ7 አመታት ኖሯል፣ በየወሩ 100 ዶላር ይልክልን ነበር።"

በመላው ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ የሶማሊ ምላሽ ሰጭዎች 2022 መጨረሻ እና በ2023 መጀመሪያ ላይ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው ድርቅ ከፍተኛ የኑሮ ጉዳትን እንዳስከተለ በመላው ማህበረሰቦች፣ የሶማሊያ ምላሽ ሰጭዎች ተስማምተዋል። ከብቶች ሞተዋል፣ ሰብሎች ደርቀዋል፣ እና አነስተኛ ንግዶች (የማህበረሰቡ አባላት ገንዘብ በማግኘታቸው የተመካው) ከሽፈዋል። የሃርሼን የጎሳ መሪ እንዲህ ሲል ገለጿል።

> አብዛኞቹ እንስሳት ሞተዋል፣ በእናም ያሉንን የምንሸጥበት ቦታ የለንም። በዚህ ክልል አብዛኛው እንስሶቻችን በሶማሊያ ይሸጣሉ እንደ ሞቃዲሾ፣በሳሶ ወይም በርበራ። የምንሸጥባቸው ሌሎች ቦታዎች የለንም። እዚያ ስንሄድ እና ብዙ ሰዎች ሲሸጡ የእንስሳቱ ዋጋ ይቀንሳል።

ከወረዳው የልማት ወኪልም በተመሳሳይ መልኩ ተናግሯል፡-

> ድርቁ ያለንን ሰብል በሙሉ አወደመ። ከዓመት በኋላ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ምንም በቂ ነገር አልነበረም። ቀደም ባሉት ጊዜያት ዘሮች ነበሩ። በችግሩ ምክንያት ህብረተሰቡ ምግብ የሚገዛበት ሌላ ገቢ ስላልነበረው እነዚህን ዘሮች በመቁረጥ ከሰል ወደ ማምረት ተሸጋግሯል።

የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነ የ21 አመቱ ወጣት ድርቁ ቢያበቃም ቤተሰብ የሚመካባቸውን እንስሳት ዳግም ለማቋቋም አመታትን እንደሚወስድ ተናግሯል።

> የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት ከብቶቻቸውን እየሸጡ ለኑሮ መተዳደሪነት ይጠቀማሉ። ነገር ግን በድርቁ ወቅት ሰዎች ከብቶቻቸውን አጥተዋል። በድርቁ ምክንያት የከብቶች

> መጥፋት በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ አሁን የአካባቢው ማህበረሰብ ከብት የለውም፡፡ በርግጥ አሁን ዝናብ ይዘንባል፤ ሰዎች ግን ከብት የላቸውም፡፡

ምንም እንኳን አብዛኞቹ የፋፋን ምላሽ ሰጪዎች አሁ ወቅት በቂ ምግብ እንዳገኙ ቢገልጹም፣ በድርቁ ምክንያት የምግብ ዋስትናቸው በእጅጉ እንደተጎዳ ተስማምተዋል፡፡

የጎልጃኖ የቀበሌው ሰብሳቢ ሪፖርት እንዳደረገው፣ "በከፍተኛ የምግብ እጥረት ተከስቶ ነበር፡፡ በ500 ብር የምንገዛው ዱቄት በ2,500 ተሸጧል፡፡ ድሃ ከሆንክ ምንም መግዛት አትችልም፡፡" የሀርሸን ከተማ ነዋሪ የሆነች የ19 ዓመቷ ወጣት እናት እንደተናገረቸው በተለይ የተለያየ ገቢ ላልነበራቸው አርብቶ አደሮች ድርቁ ከባድ ነበር፡፡ "የምንሸጣቸው ፍየሎች ብቻ አሉን፡፡ ፍየሎቻችንን በመሸጥ ምግብ እንገዛለን፡፡" ብላለች፡፡ የጎልጃኖ ከተማ ነዋሪ የሆነችው ሌላዋ ወጣት እናት እንደገለፀችው በጣም ትንንሽ ልጆች ያሏቸው ሴቶች አካባቢያቸውን ለቀው ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ባለመቻላቸው (የተሻለ የግጦሽ መስክ ፍለጋ፣ የጉልበት ስራ ለመስራት ወይም አስተማማኝ የአደጋ ጊዜ እርዳታ ለማግኘት) እነሱና ልጆቻቸው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ የሚከተለውን ተናግራለች፡፡

> እኔ ልጆች ስላሉኝ ቀየን ትቼ ወደሌላ ቦታ መሄድ አልቻልኩም…የምንበላው ነገር አልነበረንም…ልጆችን ይዞ የምግብ እጥረት በጣም አስቸጋሪው ነገር ነበር… ልጆች ረሃብን መቋቋም ስለማይችሉ እኔ አስቀድሜ እመግባቸዋለሁ፡፡ ከልጆች የተረፈ ካለ እናቴን አበላታለሁ፡፡ ልጆቼን ካበላሁ በኋላ ምንም ምግብ ከሌለ እኔ እና እናቴ ያለ ምግብ እንተኛለን፡፡

በድርቁ ወቅት የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎት ማግኘት የተለመደ እንደነበር ተነግሯል፡፡ አብዛኛዎቹ ምላሽ ሰጪዎች ማህበረሰባቸው ከኢትዮጵያ መንግስት ወይም ከአለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) የምግብ ራሽን እንደተቀበሉ ተናግረዋል፡፡ "የሃርሸን ከተማ የልማት ወኪል "ሴፍቲኔት ፕሮግራም የስንዴ ዱቄት፣ የምግብ ዘይት እና አተር ሰጥቶናል" ሲል አስታውሷል፡፡" የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነ የ20 ዓመት ወጣት፣ "ከዚህ ቀደም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተወሰነ የምግብ ድጋፍ ይሰጡ ነበር" ሲል አክሎ ተናግሯል፡፡ የፕሮግራም አጋማሽ መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ግን ምላሽ ሰጪዎች የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ማብቃቱን እና ከሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑት ጥቂቶች ብቻ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡ አብዛኛዎቹ አባወራዎች/እማዎራዎች የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ያለመ መሠረተ ልማት በመፍጠር በሕዝብ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ነበሩ፡፡ አንድ የ20 አመት ወጣት ከሃርሸን እንደገለጸው ድጋፍ የሚሰጠው በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር፡-

> የሴፍቲኔት ፕሮግራም ድጋፍ የምናገኘው በሕዝብ ሥራዎች ፕሮግራም ውስጥ ከተሳተፍን በኋላ ሲሆን ለሥራ በምላሹ ጥሬ ገንዘብ ይሰጣል፡፡ ሌሎች አካል ጉዳተኞች እና የ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ህዝባዊ ስራ መስራት የማይችሉ፣ ነፃ ድጋፍ ያገኛሉ… የውሃ ኩሬዎችን ለመንከባከብ እንሰራለን እንዲሁም እርከን በመሥራት የአፈር መራቆትን እንጠብቃለን… በዓመት ሁለት ጊዜ ድጋፍ እናገኛለን፡፡

የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ16 ዓመቷ ልጅ አክላ እንደተናገረችው ምንም እንኳን ጥቅማጥቅሞች ትንሽ ቢሆኑ (የዋጋ ግሽበት እንዳለ ሁኖ) እና መደበኛ ባይሆኑም እያንዳንዱ ትንሽ ነገር ይረዳል: - "ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማግኘት ከጀመርን በኋላ በህይወታችን ላይ ትንሽ ለውጥ አለ ማለት እንችላለን፡፡


## ትምህርት

### አፋር


በአፋር የጥናት ቦታዎች ውስጥ የትምህርት ፍላጎት እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ እስካሁን ከተመዘገቡት ወጣቶች መካከል ከሁለት ሶስተኛው በላይ (68%) የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ለማጠናቀቅ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ የታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ምኞት ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (83% ከ 65%) በእጅጉ የላቀ ነበር፡፡ በአውሲ ረሱ (ዞን 1) ዩኒቨርሲቲ የመግባት ምኞት (75%) ከሀሪ ረሱ (ዞን 5) (63%) በከፍተኛ ደረጃ ከፍ ያለ ነበር፡፡ የወላጆች በትምህርት ገበታ ላይ ላሉ ልጆቻቸው ያላቸው ምኞት ዝቅተኛ ነበር፡፡ የወላጆች ወንዶች ልጆቻቸው (57%) ዩኒቨርሲቲ እንዲያጠናቅቁ ከሴት ልጆቻቸው (38%) ይልቅ የመመኘት እድላቸው ከፍተኛ ነው (ምስል 13 ይመልከቱ)፡፡ በከተማ እና የተሻለ አገልግሎት ባላቸው አውሲ ረሱ [ዞን 1] ውስጥ ያሉ የወላጆች ከሀሪ ረሱ [ዞን 5] የበለጠ ለወንዶች እና ለሴቶች ልጆች ከፍተኛ ምኞት ነበራቸው፡፡ የሚያስደስተው ነገር፣ ወንድ የወላጆች ለወንዶች እና ለሴቶች ልጆች (81% እና 71%) ከሴት የወላጆች (55% እና 35%) ከፍተኛ ምኞት እንዳላቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡

በአፋር የጥናት ቦታዎች ከሚገኙ ወጣቶች መካከል ሁለት ሶስተኛው (67%) ብቻ በመደበኛ ትምህርት የተመዘገቡ ናቸው (ምስል 14 ይመልከቱ)፡፡ የታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች (79%) ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (66%) የበለጠ የመመዝገብ እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በከተማ ውስጥ ያሉ ወጣቶች እና ይበልጥ ተረጋግተው በአውሲ ረሱ [ዞን 1] (84%) በሃሪ ረሱ [ዞን 5] (59%) የሚኖሩት የመመዝገብ እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ እስካሁን ከተመዘገቡት መካከል አብዛኞቹ (81%) በፕሮግራም አጋማሽ ጥናት ወቅትም ተመዝግበዋል፡፡ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (20%) ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ይልቅ (10%) የማቋረጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ መጀመሪያ በትግራይ በተቀሰቀሰው እና ከዚያም በመላው ሰሜን ኢትዮጵያ የተስፋፋው ግጭት ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረባቸው በሃሪ ረሱ [ዞን 5] (23%) ወጣቶች በአውሲ ረሱ [ዞን 1] (14%) ካሉ አቻዎቻቸው ይልቅ የማቋረጥ እድላቸው ሰፊ ነበር፡፡ ከዳሰሳ ጥናቱ በፊት በነበሩት ሁለት ሳምንታት ውስጥ የመገኘት ብዛት ከፍተኛ ነበር (95%)፣ ነገር ግን ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች

ምስል 13: የአፋር አሳዳጊዎች ለወንዶች ልጆቻቸው ከሴቶች ልጆቻቸው አንጻር ያላቸው የትምህርት ፍላጎት




ምስል 14: በትምህርት ላይ ያሉ የአፋር ወጣቶችና የትምህርት ክትትል





በዚያ ጊዜ ውስጥ እንደታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ሶስት እጥፍ አልተገኙም (6% በተቃራኒ 2%)፡፡

የአፋር ወጣቶች በትምህርት የመቀጠል ሁኔታ አዝጋሚ ነው፡፡ ምንም እንኳን በናሙናው ውስጥ ያሉት አማካኝ ጎልማሳ ወንዶች 16 አመት የሞላቸው ቢሆንም፣ አማካዩ ተማሪ ገና 4ኛ ክፍል አላጠናቀቀም ነበር (ምስል 15 ይመልከቱ)፡፡ በአውሲ ረሱ (ዞን 1) የሚኖሩ ተማሪዎች፣ ምንም እንኳን (በአማካይ) በ3 ወር ብቻ ቢበልጡም፣ በሃሪ ረሱ (ዞን 5) ካሉ አቻዎቻቸው (5.7 ክፍል ከ 3.9 ክፍሎች) ቀድመው ወደ ሁለት የሚጠጉ የሙሉ ክፍል ደረጃዎች ላይ ነበሩ፡፡ ታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች በትንሹ ቀድመዋል (5 ክፍል በተቃራኒ 4.6)፤ ምክንያቱም በአማካይ ከግማሽ አመት በላይ ይበልጡ ነበር፡፡ በድምሩ የትምህርት ቤት መልቀቂያዎች ውጤት ከተመዘገቡ ተማሪዎች ትንሽ ከፍ ያለ ነበር፡፡ አማካኝ ትምህርት ያቋረጡት ከትምህርት በወጡበት ወቅት 5.1 የትምህርት አመታትን ያጠናቀቁ ነበሩ፡፡ ትምህርት ያቋረጡ ልጃገረዶች (5.2 ክፍል በ15.8) ከወንዶች አቻዎቻቸው (በ15.3 ዓመታቸው 4.5 ክፍል) የበለጠ ክፍል ደረጃዎችን አጠናቀው የነበረ ሲሆን፣ ምክንያቱም ከትምህርት ሲወጡ በእድሜ ትልቅ ስለነበሩ ነው፡፡ በአውሲ ረሱ (ዞን 1) ትምህርት ያቋረጡት በሀሪ ረሱ (ዞን 5) (6.3 ክፍል ከ 4.6) ትምህርት ከአቋረጡ የበለጠ ክፍል ደረጃዎችን አጠናቀዋል፣ ምንም እንኳን በሃሪ ረሱ ትምህርታቸውን ያቋረጡት ትምህርታቸውን ትተው በወጡበት ወቅት በአውሲ ረሱ ካሉት ወደ ግማሽ ዓመት የሚጠጋ የሚበልጡ ነበሩ፡፡


የአፋር ወጣቶች በትምህርት ሂደት ያላቸው አዝጋሚ ግስጋሴ በእድሜ የተቃኘው ብዙዎች ወጣቶች ወደ ትምህርት ቤት ዘግይተው በመመዝገባቸው ነው፡፡ በቤተሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሁሉም ህጻናት የትምህርት ምዝገባ ሁኔታ ሲጠየቁ፣ የቤተሰብ አስታዳዳሪዎች እንደተገገሩት ከ7-12 አመት የሆናቸው 48% ብቻ ተመዝግበው ነበር ፣ ከ13-18 አመት ካሉት 60% ህጻናት ጋር ሲነፃፀር (ምስል 16 ይመልከቱ)፡፡ በአንፃራዊነት በሰዓቱ መመዝገብ ሁኔታ ይበልጥ ሰዎች ተረገግተው በሚኖሩበት እና የተሻለ አገልግሎት በሚሰጥ አውሲ ረሱ [ዞን 1] ከሀሪ ረሱ [ዞን 5] (71% በተቃራኒ 36%) እና የበለጠ የተለመደ ነበር፤ በሚያስደንቅ ሁኔታ (በወጣቶች መካከል ያለው ተመሳስሎዎች እንዳሉ ሁነው) ከወንዶች ይልቅ በሴቶች መካከል የተለመደ ነበር (53% በተቃራኒ 44%)፡፡

በወጣት የጎልምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች ትምህርት አቀባበል ብዙውን ጊዜ የሚቀረጸው ቢያንስ በከፊል፣ ትምህርት ቤቶች የወር አበባን ለመቆጣጠር እንዲረዷቸው በመሆኑ፣ የታዳጊ ወጣቶች ዳሰሳ ጥናት ስለ ትምህርት ቤት ውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ንፅህና (WASH) ተማሪዎችን ጠይቋል፡፡ ከተመዘገቡ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች መካከል 41%

ምስል 15: የአፋር ወጣቶች የደረሱበት የክፍል ደረጃ





ምስል 16: ለመደበኛ ትምህርት የተመዘገቡ የአፋር ልጆች ድርሻ በአሳዳጊዎች እንደተገለጸው




የሚሆኑት በአፋር ክልል የሚገኙት ትምህርቶች ለሴቶችና ለወንዶች የተለየ መጸዳጃ ቤት እንዳላቸው ተናግረዋል (ምስል 17 ይመልከቱ)። ተመሳሳይ መጠን ያለው (37%) ልጃገረዶች በትምህርት ቤት ውስጥ የወር አበባን ለመቆጣጠር የሚረዱ ቁሳቁሶች ወይም አቅርቦቶች እንዳሉ ተናግረዋል። በት/ቤት ላይ የተመሰረተ  አጠባበቅ አስተዳደር ድጋፍ ሪፖርት ካደረጉ ልጃገረዶች መካከል አብዛኞቹ የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ አቅርቦቶችን (83%) እና የመጸዳጃ ቤቶችን (59%) ሪፖርት አድርገዋል።

ምስል 17: ለወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ የትምህርት ቤት ድጋፍ፣ ለአፋር ሴት ተማሪዎች ብቻ




አይነታዊ ጥናቱ የዳሰሳ ጥናት ግኝቶችን እንደገና አስፍቶና አጥርቶ አይቷል። ለምሳሌ ምላሽ ሰጪዎች እንደተናገሩት ለአረጋውያን እና ለወጣቶች በተለይም በአውሲ ረሱ [ዞን 1] እና ከሀሪ ረሱ [ዞን 5] ራቅ ካሉ ማህበረሰቦች ለመጡ መደበኛ ትምህርት በልጅነት አይገኝም ነበር።በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የምትኖር አንዲት ባለትዳር እና ትምህርት ቤት ገብታ የማታውቅ የ23 ዓመት ወጣት እንደገለጸችው፣ "በዚያን ጊዜ ትምህርት ቤት አልነበረም።" ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ማህበረሰቦች ማለት ይቻላል የራሳቸው ትምህርት ቤት ቢኖራቸውም (ቢያንስ እስከ 4ኛ ክፍል)፣ በቂ የሀብት አቅርቦት አለመኖር በተለይ በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የወጣቶችን የትምህርት እድል መገደቡን ቀጥሏል። በአንዳንድ ሁኔታዎች የመማሪያ ክፍሎች ወንበር ወይም መጽሐፍ ስለሌላቸው ነው፣ ወይም መምህራን በጣም ጥቂት ስለሆኑ ወይም መምህራን በጣም ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤት ስለሚቀሩ ነው። በሃሪ ረሱ የሚኖረው የ20 አመት ወጣት እንደገለጸው በእሱ ማህበረሰብ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በአስተማሪዎች እጥረት ምክንያት በጣም ከባድ ነው፤

በመጠጥ ውሃ  እና ሌሎች መገልገያዎች እጥረት ምክንያት መምህራን በመደበኛነት ወደ ትምህርት ቤት አይመጡም፡ ፡ በተጨማሪም በትምህርት ቤታችን በቂ መምህራን እንዳልተሰማሩ እና ወደ አካባቢያችን የሚመጡትም በውሃና ሌሎች መገልገያዎችን  እጦት ምግብን ጨምሮ ትምህርት ቤቱንና አካባቢውን ለቀው ወጥተዋል። አስተማሪዎች

ወደዚህ አካባቢ መምጣት እና በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ መሥራት አይፈልጉም።

የታዳጊ ወጣቶች የመካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የማግኘት እድል የተገደበው የከፍተኛ ደረጃዎች ትምህርት ሚሰጠው በአንፃራዊነት በይበልጥ በከተማ አካባቢዎች በመሆኑ ነው። ይህ ደግሞ በሃሪ ረሱ [ዞን 5] ውስጥ ላሉ ወጣቶች በጣም የሚገድበው ነው፣ ወደ ትምህርት ቤት በእግር መጓዝ ወይም በከተማ ውስጥ ተከራይተው መኖር አለባቸው። አንድ አባት ከሃሪ ረሱ እንደገለጹት፣

"በኩማሜ 9ኛ ክፍል የሚማር ወንድ ልጅ አለኝ…እሩቅ ነው…ለሽማግሌዎች 11 ሰአታት ይወስዳል፣ ለወጣቶች ደግሞ 7 ወይም 8 ሰአታት ይወስዳል።

የ 21 ዓመት ያገባች ታዳጊ ወጣት ሴት ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] በተጨማሪ እንደገለጸችው፣

ትምህርቴን ያቋረጥኩት ባለብን የገንዘብ እጥረት ምክንያት ነው… የገንዘብ አቅም ያላቸው ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ከተማ ሄደዋል፣ ነገር ግን የኔ ወላጆቼ ትምህርቴን እንድቀጥል አልሄዱም።

እንስሳትን የመጠበቅ ሃላፊነት፣ በተለይም በሃሪ ረሱ [ዞን 5]፣ የታዳጊ ወጣቶችን የትምህርት እድል ይገድባል። በዚህ ዞን ነዋሪ የሆነ የ19 አመት ወጣት በዚህ ምክንያት ትምህርት ቤት ሄዶ እንደማያውቅ ተናግሯል - እናም ወንድምና እህቶቹ የሱን ስህተት እንዲያስወግዱ እንደሚያበረታታ በተጨማሪ ገልጿል፡-

ምንም መማር አልጀመርኩም - እረኛ ነኝ። እናቴ መማር እንድጀምር ገፋፋችኝ፣ነገር ግን እምቢ አልኩ…እና ከብቶችን መንከባከብ መረጥኩ። ያኔ መማር የጀመሩት ጓደኞቼ እና የዕድሜ ጓደኞቼ በሙሉ አሁን 12ኛ ክፍል ጨርሰዋል። ከፊሎቹ ስራ ይዘው ደሞዝ የሚከፈላቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብተዋል። በዛን ጊዜ መማር የጀመሩ ጓደኞቼን ሳይ ትምህርት ባለማግኘቴ በጣም ይከፋኛል። በአሁኑ ጊዜ እኔ ከብት እረኛ ነኝ ነገር ግን ሁሉም ወንድሞቼ እና እህቶቼ ትምህርት ቤት ናቸው እና እንዲማሩና አላማቸውን እንዲያሳኩ እመክራቸዋለሁ።

ህጻናት እንስሳትን የመጠበቅ ሃላፊነት እስከ ታዳጊነት እድሜ መጀመሪያ ድረስ ትምህርት ያልጀመሩ እና በዚህም ምክንያት እድሜያቸው ከሚማሩበት ክፍል ደረጃ በላይ በሆኑ አያሌ ቁጥር ባላቸው ታዳጊዎች ላይም ይንጸባረቃል። በሃሪ ረሱ (ዞን 5) የምትኖር እናት ልጅዋ በ12 ዓመቱ ትምህርት መጀመሩን ገልጻለች፤ ምክንያቱም እሱ ለእንስሳት የመንከባከብ ኃላፊነት ነበረበት። "ልጄን ወደ ትምህርት ቤት ሳልክ ያዘገየሁት እንስሳትን የሚንከባከብ ምንም ሰው ስለሌለኝ ነው።" ብላለች። መላሾቹ አክለው እንደተናገሩት በሰአቱ ለሚመዘገቡ ህጻናት እንኳን ሳይቀር እንስሳትን የመጠበቅ ሀላፊነቶች በተማሪዎችን የትምህርት ገበታ መገኘት እና ቀጣይነት ላይ ተጽኖ ያሳድራሉ፡ በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የምትኖር አንዲት ባለትዳር የ22 ዓመት ወጣት እንዲህ ብላለች፦

በቤት ውስጥ ከፍተኛ የሥራ ጫና ስላለብን እነሱ (ልጆቹ) ከብቶቹን ይንከባከባሉ። ልጆቻችን አንዳንድ ቀናት ትምህርት ቤት ይማራሉ እና አንዳንድ ቀናት ይቀራሉ።

ምላሽ ሰጪዎች እንደተናገሩት በአየር ንብረት ለውጥም ሆነ በግጭት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የታዳጊ ወጣቶች የትምህርት ተደራሽነት በእጅጉ ቀንሷል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ይህ የሆነበት ምክንያት ጎርፍ ትምህርት ቤቶችን እና የመማሪያ ቁሳቁሶችን ስለወሰዳቸው ነው። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የሚኖረው የ22 ዓመት ወጣት እንደገለፀው፡

በጎርፍ ምክንያት የትምህርት ቤት ህንጻዎች በውሃ ተውጠዋል፣ እናም ቁሳቁሶች መጽሐፍት፣ መቀመጫዎች፣ ጠረጴዛዎች እና የተማሪዎች መዛግብትንም ጨምሮ በጎርፍ ተጥለቅልቀው ወድመዋል።

በሌሎች ሁኔታዎች ይህ የሆነበት ምክንያት የቤተሰብ መተዳደሪያዎች በጣም ጉዳት ስለደረሰባቸው በትምህርት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ አቅም ስለሌላቸው ነው። አንድ የዞን 1 እናት አክለው "ከምናገኘው የበለጠ ገንዘብ እናጠፋለን፣ ህይወት ውድ ነው" ሲሉም ተናግረዋል።

ወቅታዊ ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ አባወራዎች መካከል፣ ረዘም ያለ ድርቅ ተማሪዎችን ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ገበታ አስወጥቷቸዋል። የሃሪ ረሱ [ዞን 5] የሚኖር የ19 ዓመት ወጣት እንዲህ ሲል ገልጿል፡-

እንደሚታወቀው በአካባቢያችን ሳርና ውሃ ፍለጋ ከከብቶች ጋር ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የተለመደ ነው። በየአመቱ ከቦታ ቦታ እንቀሳቀሳለን ነገርግን በአካባቢያችን የተለመደው ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ ለአጭር ጊዜ ምናልባትም ለአንድ ወር ወይም ለሁለት ወር እና እንዲሁም በአቅራቢያው ወደሚገኙ አካባቢዎች ነበር የምሄደው። ነገር ግን ባለፈው ዓመት የተከሰተው ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ ለረጅም ጊዜ - ከስድስት ወር ለሚበልጥ ጊዜ ነበር።

በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የጥናት ቦታዎች ከድርቅ ጋር ተያይዞ የሚደርሱት ጉዳቶች በግጭቱ የበለጠ ተባብሰዋል፣ ይህም ተማሪዎች እና መምህራን ወደሌላ ቦታ ጥለው እንዲሄዱ በማድረግ ብዙ ትምህርት ቤቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነች እናት የሚከተለውን ብላለች።

የፀጥታ ጉዳዮች በአካባቢያችን ትምህርት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረዋል… መምህራን እዚህ ተጉዘው ተማሪዎችን ለማስተማር ምንም አይነት ደህንነት አይሰማቸውም… በጦርነቱ ወቅት ትምህርት ቤቱ ተጎድቷል።

የአይነታዊ ጥናት ተሳታፊዎች ለልጃገረዶች የበለጠ ውስን የትምህርት ተደራሽነት ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ አያሌ ማብራሪያዎችን ሰጥተዋል። አንዳንዶቹ ልጃገረዶች ወደ

ትምህርት ቤት እንደማይላኩ ተናግረዋል፣ ምክንያቱም ከእናቶቻቸው ጋር አብረው ለመስራት እቤት ውስጥ ስለሚያስፈልጉ። ሀሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነችው የ20 ዓመቷ ባለትዳር ወጣት እንዲህ ስትል ተናግራለች፡- "ልጃገረዶች ውሃ አምጥተው ምግብ ያበስሉልዎታል፣ ነገር ግን ወንዶች ይህን አይከውኑም።" ሌሎች እንደተናገሩት ትምህርት ቤት ለመድረስ ያለው ርቀት፣ ልጃገረዶች እያደጉ ሲሄዱ የጊዚያቸውን የመጠቀም ፍላጎት ስለሚያድግ፣ በህጻናት ጋብቻ ምክንያት እና የአለም አቀፍ የስደት አዝማሚያ እያደገ በመምጣቱ ልጃገረዶች ከታዳጊ ወንድ ልጆች በይበልጥ ብዘውን ጊዜ ትምህርት ያቋርጣሉ። የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነ የ23 አመት ወጣት ሚስቱ ተማሪነቷን እና እናትነቷን ማመጣጠን ባለመቻሏ ከ8ኛ ክፍል በኋላ ትምህርቷን ማቋረጧን ገልጿል።

> ከባለቤቴ ጋር ስገባ 8ኛ ክፍል እየተማረች ነበር፣ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ከወሰደች በኋላ ትምህርቷን አቋርጣለች። ምንም እንኳን ወደ 9ኛ ክፍል ብታልፍም በእርግዝና ምክንያት መማርን መቀጠል አልቻለችም... መማር እንደገና አልጀመረችም፣ የቤት እመቤት ሆነች።

በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የምትኖር አንዲት እናት እንደተናገረችው ታዳጊ ወንዶ ልጆች ሳይሆኑ የልቁንም ልጃገረዶች በመካከለኛው የታዳጊነት እድሜያቸው ወቀት ገቢ የሚያስገኝ ስራ ለማግኘትና የቤተሰባቸውን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ዓላማ አድርገው ትምህርታቸውን በመተው ይሰደዳሉ። "የሚሰደዱት ልጃገረዶች እንጂ ወንዶች አይደሉም። ወንዶች ልጆች በቀላሉ ሥራ ማግኘት አይችሉም።" ከጥቂቶች በስተቀር፣ ትምህርት ቤት ያልተመዘገቡ ወይም አዘውትረው የማይገኙ ልጃገረዶች ምርጫቸው ይህ እንደሆነ ተገንዝበዋል። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የምትኖር የ12 ዓመቷ ልጅ እንዲህ ብላለች።፤

> ወንዶች ጥሩ ሁኔታ ላይ ሲሆኑ ይመጣሉ፣ ካልሆነ ግን ትምህርት ቤቱን ለቀው ይሄዳሉ... ልጃገረዶች እናታቸው ስትሰራ ሁልጊዜ ያያሉ... ይህን ህይወት ላለመድገም [የነርሱ አመለካከት] ያለን ብቸኛ አማራጭ መማር ነው።

በተለይም በአውሲ ረሱ [ዞን 1] አብዛኞቹ ተማሪዎች እንደተናገሩት የትምህርት ቤት መጸዳጃ ቤቶች ንጽህና የጎደላቸው እና በአብዛኛው ጥቅም ላይ ያልዋሉ ናቸው፤ በተለይም በድርቁ ምክንያት ውሃ ሙሉ በሙሉ አያገኙም። የሃሪ ረሱ [ዞን 5] የሚኖር የ18 ዓመት ወጣት እንዲህ ሲል ገልጿል፤

> አብዛኞቹ ተማሪዎች መጸዳጃ ቤት አይጠቀሙም፣ በጫካ ውስጥ ነው የሚጠቀሙት። መጸዳጃ ቤቱ ውሃ ስለሌለው በቆሻሻ የተሞላ እና መጥፎ ጠረን አለበት።


ልጃገረዶች በትምህርት ቤት ውስጥ የወር አበባን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ ሲጠየቁ በአብዛኛው ወደ ቤት እስኪመለሱ ድረስ እንደሚጠብቁ ተናግረዋል። አንዲት የ18 ዓመት ወጣት ሴት እንዲህ በማለት ገለጸች፡-

> ትምህርት ቤት ከመሄዳችን በፊት ማንኛውንም ለወር አበባ የሚያስፈልገውን ነገር በቤት ውስጥ ጥንቃቄ እናደርጋለን፣ ምክንያቱም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጁ ቦታዎች ስለሌሉ እና ከዚያ በኋላ የትምህርት ቀን ያበቃል፣ በኋላም ወደ ቤት ስንመለስ የንፅህና መጠበቂያ እቃዎቻችንን በዛን ጊዜ መለወጥ እንችላለን ።

## ሶማሊ

በሶማሌ ክልል ውስጥ በተመዘገቡ ወጣቶች መካከል የትምህርት ፍላጎት እጅግ ከፍተኛ ነው። ወደ ሶስት አራተኛ የሚጠጉ (74%) ከመቼውም ጊዜ በላይ፣ የተመዘገቡ ወጣቶች ዩኒቨርሲቲ ለመጨረስ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል። አካባቢያዊ ልዩነቶች በጣም ትንሽ ሲሆኑ፣ የታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ይልቅ ዩኒቨርሲቲን የማጠናቀቅ ምኞታቸው ከፍተኛ ነበር (82 በመቶው ከ71%)። የወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት ያላቸው ምኞቶች ተመሳሳይነት ነበራቸው። ምንም እንኳን አካባቢያዊ ልዩነቶች በጣም ትንሽ ቢሆኑም፣ የወላጆች ከሴቶች ልጆቻቸው (75%) ይልቅ ወንድ ልጆቻቸው (84%) (ምስል 18 ይመልከቱ) ዩኒቨርሲቲ እንዲጨርሱ ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ምስል 18: የሶማሊ አሳዳጊዎች ለወንዶች ልጆቻቸው ከሴቶች ልጆቻቸው አንጻር ያላቸው የትምህርት ፍላጎት




በተጨማሪም ሴት እና ወንድ የወላጆች ለወንዶች ልጆቻቸው ተመሳሳይ ምኞት የነበራቸው ቢሆንም፣ ወንድ የወላጆች ከሴት የወላጆች ይልቅ (82% በተቃራኒ 74%) ሴት ልጆቻቸው ዩኒቨርሲቲ እንዲያጠናቅቁ ይፈልጋሉ።

በሶማሊ ከሚገኙ ወጣት ታዳጊዎች መካከል 50% ብቻ በመደበኛ ትምህርት ተመዝግበዋል (ምስል 19 ይመልከቱ)። ታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች (58%) ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (47%) የበለጠ የመመዝገብ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በፋፋን የሚገኙ ወጣቶች (51%)፣ አንዳንዶቹ በአይነታዊ ጥናቱ መሰረት ከኢትዮጵያ ይልቅ በጎረቤት ሶማሌላንድ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ፣ በጃራር ካሉት (46%) የበለጠ የመመዝገብ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። እስካሁን ከተመዘገቡት መካከል አብዛኞቹ (89%) የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ ጥናቱ ወቅትም ተመዝግበዋል። ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (13%) ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች (6%) የበለጠ የማቋረጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በየአካባቢው ትምህርት የማቋረጥ መጠን ተመሳሳይ ነበር። አማካኝ የተመዘገቡ ተማሪዎች፣ ጾታ እና ቦታ ከግምት ውስጥ ሳይገቡ፣ ከዳሰሳ ጥናቱ በፊት ባሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ 10% የትምህርት ቀናት አምልጠዋቸው ነበር።


በሶማሊ የጥናት ቦታዎች የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች በትምህርታቸው የመግፋት ሁኔታ ወደ ኋላ የቀረ ነው። ምንም እንኳን በናሙናው ውስጥ ያለው አማካኝ ታዳጊ ወጣት ጥናቱ በተደረገበት ወቅት 15.7 አመት የነበረ ቢሆንም አማካኙ የተማሪ መጠን 7ና 4ኛ ክፍል አላጠናቀቀም ነበር (ምስል 20 ይመልከቱ)። ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ትንሽ ቀድመዋል (5.1 ክፍል ከ 4.6 ክፍሎች) ምክንያቱም በእድሚያቸው ትንሽ ከፍ ያሉ ስለነበሩ (15.9 ዓመት ከ 15.3 ዓመታት ጋር ሲነጻጸር)። በጃራር ያሉ ወጣቶች (5.2 ክፍል) ከፋፋን (4.9 ክፍል) ትንሽ ቀድመው ነበር፣ ምክንያቱም በእድሚያቸው ትንሽ ከፍ ያሉ ስለነበሩ (16.2 ዓመት ከ15.5 ዓመታት ጋር ሲነጻጸር)። የት/ቤት ለቃቂ ተማሪዎች የክፍል ደረጃን የማጠናቀቅ ስኬት ከተመዘገቡ ተማሪዎች በትንሹ ያነሰ ነበር። 4.7 አመት ብቻ ትምህርቱን አጠናቆ በ14.9 አመት ትምህርቱን ያቋረጠ አማካይ ታዳጊ ወጣት፣ በጃራር ካሉት ት/ቤት ለቀው የወጡት በጣም ታዳጊዎች (14.4 ዓመታት) እና አነስተኛ ትምህርት ያላቸው (4.3 ክፍሎች) ነበሩ።

አሁንም እንደ አፋር አቻዎቻቸው፣ የሶማሊ ተዳጊ ወጣቶች በትምህርታቸው የመግፋት ሁኔታ ወደኋላ የመቅረት ሁኔታ በጣም ትልቅ ተጽኖ ያረፈበት ብዙ ተማሪዎች ወደ ትምህርት

ምስል 19: በትምህርት ላይ ያሉ የሶማሊ ወጣቶችና የትምህርት ክትትል




ምስል 20: የሶማሊ ወጣቶች የደረሱበት የክፍል ደረጃ



ቤት ዘግይተው በመግባታቸው ነው። እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በታች ስለሆኑ ሁሉም ህጻናት የመመዝገብ ሁኔታ ሲጠየቁ፣ የወላጆች እንደተናገሩት ከ7-12 አመት የሆናቸው ህጻናት 37% ብቻ ዕድሜያቸው ከ13-18 የሆኑ ሕፃናት 50% ጋር ሲነጻጸር ተመዝግበው ነበር (ምስል 21 ይመልከቱ)። በአንፃራዊነት በጊዜ መመዝገብ ሁኔታ በጃረር ከፋፋን (38% በተቃራኒ 26%) ምንም የፆታ ልዩነት ሳይታይበት የተለመደ ነበር፣

ምክንያቱም በታዳጊ ወጣትነት ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች ትምህርት የመቀበል ሁኔታ የሚወሰነው ትምህርት ቤቶች ልጃገረዶች የወር አበባቸውን መቆጣጠር እንዲችሉ ቁሳቁሶችን አሟልተው በመያዛቸው ሲሆን፣ የታዳጊ ወጣቶች ዳሰሳ ጥናት ተማሪዎችን ስለ ትምህርት ቤት የንጽህና አገልግሎት ጠይቋል። ከተመዘገቡት የሶማሊ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች 60% የሚሆኑት ትምህርት ቤታቸው ለሴቶች እና ለወንዶች የተለየ መጸዳጃ ቤት እንዳለው ተናግረዋል (ምስል 22 ይመልከቱ)። ብዙ ልጃገረዶች የወር አበባን ለመቆጣጠር የትምህርት ቤት መጸዳጃ ቤት ተቀባይነት እዳለው እንደማይሰማቸው በማስረዳት፣ ትንሽ ቁጥር ያላቸው ምላሽ ሰጪዎች (36%)፣ ትምህርት ቤታቸው ውስጥ የወር አበባን ለመቆጣጠር የሚረዱ ቁሳቁሶች ወይም አቅርቦቶች እንዳሉት ተናግረዋል። ማንኛውም ትምህርት ቤት ላይ የተመሰረተ ያደረገ የMHM ድጋፍ ሪፖርት ካደረጉ 36% ልጃገረዶች፣ አብዛኛዎቹ የመጸዳጃ ቤት (73%) እና የMHM አቅርቦቶች (38%) እንዳሉ ተናግረዋል።


በፋፋን ዞን፣ በሁለቱም የሀርሽን እና ጎልጃኖ ወረዳዎች የተካሄደው የአይነታዊ ጥናት፣ የሶማሌ ታዳጊ ወጣቶች ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ እና በትምህርት የመቀጠል ሁኔታ ወደኋላ መቅረት በርካታ ምክንያቶችን ግልጽ አድርጓል። በመጀመሪያ በብዙ የገጠር ማህበረሰቦች፣ መደበኛ ትምህርት አሁንም በአንፃራዊነት አዲስ ነው፣ አቅርቦቱም አሁንም በጣም ውስን ነው። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ22 ዓመቷ ወጣት ለምን ትምህርት ቤት እንዳልገባች ስትጠየቅ

> ቀደም ሲል ትምህርት ቤት አልነበረም። በቅርቡ እዚህ ትምህርት ቤት ተጀመረ። በእርግጥም መምህራን እንደገለፁት አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች በተለይም በጣም ርቀት ባላቸው አካባቢዎች የሚገኙት በርግጥም ትምህርት ቤቶች አይደሉም ብለዋል፤ እነሱ በምትኩ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት (የጎልማሶች መሰረተ ትምህርት) ማዕከላት "እስከ 3ኛ ክፍል ደረጃ" ብቻ የሚሰጡ ናቸው።


በሃርሸን የትምህርት ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደተናገረው በወረዳው ከሚገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእጥፍ የሚበልጡ የአቢኢ ማዕከላት አሉ (35 በተቃራኒ 18)።

በተጨማሪም እና በዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች መሰረት፣ ምንም እንኳን አብዛኛው ማህበረሰቦች አሁን የተወሰነ የትምህርት እድል ቢያገኙም፣ ልጆችን ለትምህርት በወቅቱ የማስመዝገብ ሁኔታ የተለመደ አይደለም፣ ምክንያቱም አብዛኛው የወላጆች (በተለይ ራቅ ባሉ አካባቢዎች የሚኖሩት) የህጻናትን ጊዜ ለትምህርት ከማዋል ይልቅ ለእንስሳት ጥበቃ ስለሚጠቀሙበት ነው። በእኛ አይነታዊ ጥናት ናሙና ውስጥ የተካተቱ ብዙ ወጣቶች 1ኛ ክፍልን በ7 መጀመር የነበረባቸው ቢሆንም፣ የጀመሩት በንፅፅር በ12 ዓመታቸው ነው። የሃርሺን የ15 ዓመት ወጣት ልጅ እንደተናገረው፣ "በአብዛኛው ታናናሾቼ ከብቶቼን እንዲጠብቁ ይደረጋል"። የማህበረሰቡ አባል የሆነች የ18 ዓመት

ምስል 22: ለወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ የትምህርት ቤት ድጋፍ፣ ለሶማሊ ሴት ተማሪዎች ብቻ




ምስል 21: ለመደበኛ ትምህርት የተመዘገቡ የሶማሊ ልጆች ድርሻ በአሳዳጊዎች እንደተገለጸው



ወጣት ሴት እንደተናገረችው “የገጠሩ ማህበረሰብ ከትምህርት ይልቅ የእንስሳት እንክብካቤን ይፈልጋል።” በተለይም ምንም እንኳን ታዳጊ ወጣቶች ከመደበኛ ትምህርት ይልቅ እንስሳትን ለመንከባከብ ቅድሚያ እንዲሰጡ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ለሃይማኖታዊ ትምህርት ግን ይህ አይደለም። ምላሽ ሰጪዎች እንደተናገሩት አብዛኞቹ ልጆች ቁርአንን በ6 ወይም 7 አመታቸው እና ብዙ ጊዜ በቀን ለአምስት ወይም ለስድስት ሰአታት መማር ይጀምራሉ። የፋፋን ነዋሪ የሆነች አንዲት እናት እንደገለጸችው፣

> ልጆቼ የሃይማኖት ትምህርት የጀመሩት ገና በ7 ዓመታቸው ነው። አንድ ልጅ ለዓመታት የሃይማኖት ትምህርት መከታተልና በ20 ዓመቱ ትምህርቱን ማጠናቀቅ ይችላል።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ብዙውን ጊዜ በመካከለኛ ወይም በታዳጊ ዕድሜያቸው መገባደጃ ለሚያጠናቅቁ በቁጥር አነስተኛ ለሆኑት የገጠር ታዳጊ ወጣቶች ወደ 7ኛ ክፍል መድረስ ትልቅ እንቅፋት አለበት፣ ምክንያቱም መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት ማእከላዊ በታዎች ላይ ብቻ ነው፣ ይህም በእያንዳንዱ መንገድ ለብዙ ሰዓታት የእግር ጉዞ ይፈልጋል። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነ የ12 አመት ልጅና የ 2ኛ ክፍል ተማሪ እንደገለጸው ታላቅ እህቱ (እንደ ሁሉም የቀበሌው ታዳጊ ወጣቶች) ከ6ኛ ክፍል በኋላ ትምህርቷን አቋርጣለች፤

> እህቴ እስከ 6ኛ ክፍል ተምራለች አሁን ግን በትምህርት ገበታ ላይ አይደለችም። እሷ ባለፈው አመት ስድስተኛ ክፍል ነበረች እና እዚህ ከ6ኛ ክፍል በላይ የለም።

በተጨማሪም በአብዛኛዎቹ የገጠር አካባቢዎች የትምህርት ጥራት ዝቅተኛ ነው። በከፊል ይህ የሆነበት ምክንያት የጎልማሶች መሰረተ ትምህርት የሚሰጠው በዋነኛነት እስከ 8ኛ ክፍል ብቻ በተማሩ መምህራን ነው። አንድ አስተማሪ እንዲህ ሲል ገልጿል፡-

> የጎልማሶች መሰረተ ትምህርት መደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አይደሉም…የ የጎልማሶች መሰረተ ትምህርት ትምህርት ቤቶች መምህራን በአብዛኛው የ8ኛ ክፍል ምሩቃን ሲሆኑ አንዳንዶቹ ስልጠና እየተሰጣቸው ነው…መምህራኑ ጀማሪዎች ናቸው፤ ለአርብቶ አደር ማህበረሰቦች መሰረታዊ የፅሁፍ እና የንባብ ትምህርት እንዲጡ የታሰቡ ናቸው።

አንዳንድ ጎልማሶች የ የጎልማሶች መሰረተ ትምህርት ጥራት በጣም ውስን በመሆኑ በምትኩ ልጆቻቸውን ወደ ቁርዓን ትምህርት ቤት መላክ እንደሚመርጡ ተናግረዋል። የሃርሽን የጎሳ መሪ እንደገለጹት፣

> የትምህርት ቤታችን መሠረተ ልማት አለ፣ነገር ግን ጥራት ያላቸው መምህራን የሉትም…በዚያ የሚማሩት ጥቂት ተማሪዎች ብቻ ናቸው…ከዚህ በቀር የቁርዓን መምህራችን ጎልተው ይታያሉ።

በፋፋን የትምህርት ጥራት እንዲጓደል ምክንያት የሆነው ግን የየጎልማሶች መሰረተ ትምህርት ቅድመ ሁኔታ ብቻ አይደለም። በጣም ከተማ ከሆኑ አካባቢዎች ውጭ አንዳንድ ልጆች በጊዜ ተመዝግበው በዓመት አንድ ክፍል ከሚያጠናቅቁበት አካባቢ ታዳጊ ወጣቶች እና የወላጆች ተጨማሪ እንደተናገሩት የመምህራን መቅረት ሁኔታ ከፍተኛ ነው፣ የትምህርት ቤት መገልገያዎች የተበላሹ ናቸው (በሁለቱም ቸልተኛነት እና ሆን ተብሎ በመጥፋቱ) እና የመማሪያ ክፍሎች በቂ እጥረት አለባቸው። በጎልጃኖ የገጠር ቀበሌ ነዋሪ የሆነች የ15 አመት ታዳጊ እንዲህ ብላለች፡-

> እዚህ ያሉት መምህራን የሚኖሩት በወረዳ ከተማ ነው፤ በጠዋት መጥተው እዚህ አስተምረው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። አዘውትረው ወደ ት/ቤቱ ለማስተማር አይመጡም። በትምህርት ቀናት ወደዚህ ሲመጡ በደንብ አያስተምሩም… አስተማሪዎቹ በሳምንት 2 ወይም 3 ቀናት ሊመጡ ይችላሉ።

የሃርሼን ቁልፍ መረጃ ሰጭ እንደተናገረው፣ “ትምህርት ቤቱ በመንግስት የተዘነጋ እና የተረሳ ሲሆን መምህራኑ ትምህርት ለመስጠት እንኳን አይገኙም”። ምንም እንኳን አንዳንድ መምህራን ከፍተኛ የመምህራን ከስራ መቅረት ሁኔታ ለትምህርት ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን ምክንያት እንደሆነ በያነሱም፣ የመማሪያ ክፍሎች ጥራት ያለው ትምህርት ለማዳረስ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እጥረት እንዳለባቸው ከህብረተሰቡ ጋር ተስማምተዋል። አንድ መምህር ከሀርሼን እንዲህ ሲል ገልጿል፡-

> መምህራን ከሥራ እንዲለቁ ካደረጉት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በአግባቡ ባለመከታተላቸው ነው። ተማሪዎቹ መምህራኑ በሚያስተምሩበት ርዕስ ጉዳይ ላይ በትክክል ካልተሳተፉ የመምህራንን የስራ ሞራል ይነካል… በቂ የመማሪያ መጽሐፍት አቅርቦት የለም። ያሉት የመማሪያ መጽሃፍት ለሁሉም ተማሪዎች ለማሰራጨት በቂ አይደሉም፣ ስለዚህ ለአስተማሪዎች ብቻ አቅርበናል።

በ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ (ወይም የተማሩ) ጥቂት ታዳጊ ወጣቶች አክለውም እንደተናገሩት ሌላው ወሳኝ የትምህርት ጥራት ክፍተት በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጠው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት እጥረት ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሶማሊኛ ነው፤ ሁለተኛ ደረጃ ግን በእንግሊዝኛ ስለሚሰጥ ተማሪዎች የ8ኛ ክፍል ፈተናን ቢያልፉም ለሁለተኛ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ አይደሉም። 9ኛ ክፍል የተመዘገበ የሀርሽን ከተማ ነዋሪ የ16 አመት ታዳጊ ወጣት ልጅ እንደተናገረው ይህ ለተማሪዎች የት/ቤት መልቀቂያ ፈተናን ለማለፍ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

> በታችኛዎቹ የክፍል ደረጃዎች ሁሉንም ትምህርቶቻችንን በሶማሊኛ እንማር ነበር፤ የእንግሊዘኛ ኮርስ አልነበረንም አሁን ግን ወደ ከፍተኛ የክፍል ደረጃዎች ስንሸጋገር እያንዳንዱ ትምህርት በእንግሊዝኛ እየተሰጠ ስለሆና

> እንግሊዝኛ ስለማናውቅ በጣም ለማመን በሚቸግር ደረጃ ከባድ እና ፈታኝ... ባለፉት ሁለት ዓመታት በላንከደርታ (ሀርሸን ካሉት ቀበሌዎች አንዱ) ውስጥ በሚገኙ ከሁሉም ትምህርት ቤቶች ማንም ወደ ዩኒቨርሲቲ ያለፈ የለም።

በመላው ወረዳዎች ድርቁ ከትምህርት ገበታ የመቂረት ሁኔታን ይበልጥ እንዳባባሰው ምላሽ ሰጪዎች ተስማምተዋል። ብዙ አባወራዎች በተለይም በሃርሸን ለራሳቸው እና ለከብቶቻቸው ውሃ እና ምግብ ለማግኘት አካባቢያቸውን ለቀው ሄደዋል። ትምህርት ቤቶች ባዶ ሆነው ቀርተዋል። የሀርሸን የትምህርት ባለሞያ እንደተናገረው፣

> ድርቁ በትምህርት ቤትም ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። የውሃ እጥረት ሲፈጠር አባወራዎች ግጦሽ እና ውሃ መፈለግ ይጀምራሉ እና ወደ ደጋህቡር አካባቢ (50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ) ሊዛወሩ ይችላሉ፣ ይህም ማለት ከልጆቻቸው ጋር አብረው ይሄዳሉ ማለት ነው

የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነ የ17 አመት ታዳጊ በተጨማሪ እግጸገለጸው፣ "መምህራንም ከአካባቢው ለቀው ሄደዋል፣ በድርቁ ምክንያት አካባቢውን ለቀው ወጥተዋል።"

በመላው የድርቁ በወቅ በከተሞች ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶች ክፍት ሆነው ቢቆዩም፣ ብዙ ቤተሰቦች የህልውና ፍላጎቶችን ለማሟላት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለመቀየር ተገድደዋል። ለትምህርት ወጪ የሚደረግ ገንዘብ ለምግብ ይውል ነበር፣ እናም የአዋቂዎች ጊዜ ወደ ማንኛውም ገንዘብ የሚያስገኝ ስራ ስለዞረ ልጆች ለከብት እንክብካቤ የበለጠ ሀላፊነት ነበረባቸው። የሃርሸን ቁልፍ መረጃ ሰጭ እንደተናገረው፣ "ወላጆች ከብቶቻቸውን ባጡ ጊዜ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክ አቆሙ... ወላጆች የትምህርት ቁሳቁሶችን መግዛት አልቻሉም።" የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነችው የ21 ዓመቷ ወጣት እንደገለጸችው፣

> ከድርቁ በኋላ ህጻናትን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ አላሰብንም ነበር... ቤት ውስጥ እያሳለፉ ነው። ከድርቁ የተረፉትን ጥቂት ፍየሎች ይንከባከባሉ።

ምላሽ ሰጪዎች ድርቁ ቢቆምም በትምህርት ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት አሁንም እያገረሸ መሄዱን ተናግረዋል። በድርቁ ወቅት ያቋረጡ ብዙ ወጣቶች ወደ ትምህርት ቤት አልተመለሱም፣ ምክንያቱም የጉልምስና ህይወታቸውን ቀጥለዋል። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተዘግተው ቆይተዋል፤ ብዙ መምህራንም ወደ ስራቸው አልተመለሱም። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ15 ዓመቷ ታዳጊ ወጣት ልጅ እንደገለጸችው፣ "ድርቁ ትምህርቴን እንዳቋርጥ አድርጎኛል። አሁን ቤት ውስጥ ነው የማሳልፈው፣ ቤት ውስጥ እየሠራሁ ነው።" ብላለች። አንድ የቀበሌ ደረጃ የሴቶች ጉዳይ ዋና መረጃ ሰጭ እንደዘገበው፣

> ቀደም ሲል እዚህ ቀበሌ ውስጥ ብዙ መምህራን ነበሩ፣ አንዳንዴም ከጅግጅጋ (ከሶማሊ ክልል ዋና ከተማ) ለማስተማር ይመጡ ነበር። በአንድ ወቅት 10 አስተማሪዎች ነበሩን አሁን ግን የቀሩት 4 ብቻ ነው።

ወጣቶች እና የወላጆች በተመሳሳይ እንደተናገሩት፣ የልጃገረዶች ችግር በዋነኝነት የሚፈጠረው ልጃገረዶች ለቤት ውስጥ እና ለእንክብካቤ ስራ በወላጆች ስለሚፈለጉ ነው። እነዚህ ፍላጎቶች ልጃገረዶች ለትምህርት ጨርሶ እንዳይመዘገቡ ይገታሉ፣ ምዝገባቸውን ያዘገያሉ፣ ከትምህርት ቤት መቅረትን ይጨምራሉ፣ እና ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ያደርጋሉ። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ22 ዓመቷ ታዳጊ ወጣት እንደተናገረችው፣ "ብዙውን ጊዜ ልጃገረዶች ከትምህርት ቤት የሚቀሩት የቤት ውስጥ ሥራዎችን ስለሚሠሩ ነው። የሀርሼን ነዋሪ የሆነ አንድ መምህር የሚከተለውን ገልጿል፦

> አንዲት እናት ከሦስት ሴት ልጆቿ አንዷን ብቻ ወደ ትምህርት ቤት ትልካለች። አንደኛዋ በቤቱ ውስጥ እንድትሰራ የተመደበች ሲሆን ሦስተኛዋ ደግሞ ገቢ ለማግኘት በአንዳንድ የንግድ ሥራዎች ውስጥ መሥራት አለበት። ልጃገረዶች ወላጆችን በተለይም እናታቸውን በመርዳት ረገድ ብዙ መሥራት አለባቸው። ወንዶቹ በቤቱ ውስጥ ምንም ነገር ማድረግ የለባቸውም። ወደ ትምህርት ቤት ብቻ ይመጣሉ። ስለዚህ ብዙ ልጃገረዶች እቤት ውስጥ ይቆያሉ፣ እና አንዷ ብቻ ወደ ትምህርት ቤት እንድትመጣ ይፈቀድላታል። ነገር ግን በቤቱ ውስጥ አራት ወንዶች ልጆች ካሉ ሁሉም ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ይፈቀድላቸዋል።

የዚሁ ወረዳ ነዋሪ የሆነ የ12 አመት ታዳጊ ወጣት እና የ5ኛ ክፍል ተማሪ እንደገለፀው ከ11 አመት እህቱ በስተቀር ሁሉም ወንድሞቹና እህቶቹ በእድሜያቸው ተገቢውን ክፍል ይማራሉ፣ እና የ13 አመት ወንድሙ መደበኛ ትምህርት በጠዋት እና የሃይማኖት ትምህርት ከሰዓት በኋላ ይማር ነበር። ለምን የ11 አመት እህቱ ትምህርት እንድትማር እንዳልተፈቀደላት ነገር ግን ወንድሙ ሁለት አይነት ትምህርት አግኝቷል ተብሎ ሲጠየቅ፣

> ሌሎች ወንድሞቼ እና እህቶቼ ትምህርት ቤት ስለሚማሩ ከብቶቹን የሚጠብቅ ሰው ስለሌለ ነው መለሰ። ... እንስሳትን ለመንከባከብ ጊዜ የለውም።

መምህራን አክለውም የስርዓተ-ፆታ ልዩነት እየጠበበ አይደለም ምክንያቱም ሴት ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት የሚስቡ ፕሮግራሞች ለምሳሌ የትምህርት ቤት ምገባ እና የመገኘት ሽልማት ተቋርጠዋል። የሃርሸን ትምህርት ቢሮ ኃላፊ እንዳስታወሰው፣

> ቀደም ሲል ልጃገረዶች ለ18 ቀናት ያለማቋረጥ ለማበረታታት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ዘይትና ሌሎች ቁሳቁሶችን ይቀበሉ ነበር... አሁን እነዚህ ነገሮች በሙሉ ቆመዋል።

የልጃገረዶች የትምህርት ተጠቃሚ አለመሆን ከወንዶች ጋር ሲወዳደር ህጻናት ጋብቻን እና በስደት ተጽዕኖዎች ስር የወደቀ ነው። በፋፋን የምትኖር አንዲት መምህርት እንደተናገረችው

ሴት ልጆች ከጋብቻ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት “ክልክል” ነው። የዚሁ ዞን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> አብዛኞቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ቀደም ብለው ነው። በዚህ አመት አምስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው ጋብቻ ፈጸሙ። አብዛኞቹ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብሔራዊ ፈተና ማለፍ ተስኗቸዋል፤ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀች ጓደኛዋ ወድቃ ስታገባ ጓደኞቿ የትምህርት ፍላጎታቸውን በማጣታቸው በምትኩ ማግባትን ይመርጣሉ።

ታዳጊ ወጣቶች ከጋብቻ ይልቅ ስደት የልጃገረዶች ትምህርት የማያቋረጥ ቁልፍ ምክንያት እንደሆነ ለይተው አስቀምጠዋል፡ ፡ የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ14 ዓመት ልጅ እንደተናገረችው፣ “ማንም ሰው ስለ ትዳር አያስብም… ስለ ገቢ ያስባል”።

በተሻሉ በከተሞች በሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች እንደተናገሩት ትምህርት ቤቶች የመጸዳጃ ቤት እና የውሃ አቅርቦት (ሁለቱም ልጃገረዶች በትምህርት ቤት ውስጥ የወር አበባን ለመቆጣጠር አስፈላጊ ናቸው) በደንብ የተሟላ ነበረ ቢሆንም፣ በገጠር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የ WASH የንጽህና መጠበቂያ መገልገያዎች እንደሌሉ ወይም ጥቅም ላይ የማይውሉ ነበሩ። የ13 ዓመቷ የሀርሸን ነዋሪ ከሁለቱም ወረዳዎች ሴት እና ወንድ እኩዮቿ የተሰጡ አስተያየቶችን ደግፋ እንደተናገረችው፣ “ሶስት መጸዳጃ ቤቶች አሉ ነገር ግን ውሃ የላቸውም፣ ጽዳት ያስፈልጋቸዋል፣ በርም የላቸውም። ማንም አይጠቀምባቸውም።”

## የሴት ልጅ ግርዛት


### አፋር

ከሞላ ጎደል (99%) በጥናት ናሙናነት የተካቱት ወጣት ልጃገረዶች እና ሴቶች ግርዛት እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል (ምስል 23 ይመልከቱ)። አብዛኛዎቹ (78%) ለአይነት 3/የሴት ልጅ ብልትን ተልትሎ ማጥበብ፣በተለምዶ የጠባሳ ቲሹ (65%) በማጣበቂያዎች (13%) ግርዛት ተፈጽሞባቸዋል። ዞናዊ የሆኑ ከፍተኛ ልዩነቶች ነበሩ፣ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ከሀሪ ረሱ [ዞን 5] (91% በተቃራኒ 71%) በብዛት ይፈጸማሉ። ዓይነት 2/ ኤክሴሽን በሃሪ ረሱ [ዞን 5] ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] (23% ከ 5%) የበለጠ የተለመደ ነበር። ዓይነት 1/የክሊቶሬክቶሚ በሁለቱም ዞኖች ብዘም የተለመደ አልነበረም። ሁሉም በወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት በባህላዊ ገራዦች መፈጸሙን ተናግረዋል።

ምክንያቱም የአፋር ታዳጊ ልጃገረዶች ስለ የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች ያላቸው እውቀት – በራሳቸው አካል ላይ የሚደረጉትንም ጭምር – ከቤተሰብ አስተዳዳሪወች በስፋት ያነሰ ነው (ብዙዎቹ ገና በለጋ እድሜያቸው ግርዛት ይደረጉ ስለነበር፣ እና የመነሻ አይነታዊ ጥናቱ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የግርዛት ድርጊቶች እየተቀያየሩ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመረጋገጡ)፣ የፕሮግራም አጋማሽ የወላጆች የዳሰሳ ጥናት ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ እና የሁሉም ሴት የቤተሰብ አባላት ዓይነት ጥያቄዎችን አቅርቧል። ምስል 24 የግርዛት ልማዶችን በእድሜ ክልል መቀየርን ያሳያል፣ ምንም እንኳን የአፋር ናሙና በአጠቃላይ ውስብስብነትን ለመቀነስ (በዞን ባይቀርብም)።


በ14 ዓመቷ ያገባች የ20 አመት እናት፣ አፋር፣ ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

ምስል 23: የአፋር ታዳጊ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ





በርካታ የሚስቡ አስደናቂ ምሳሌዎች አሉ። በመጀመሪያ በእድሜ ምድብ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ አዝጋሚ ነገር ግን ያለማቋረጥ የመቀነስ ሁኔታ አለ። ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሴቶች (99%) እና ከ12-17 (97%) ለሆኑ ልጃገረዶች፣ የግርዛት ድርጊት የተለመደ ወጥ ድርጊት ነው። ከ9-11 (91%) ወይም 6-8 (86%) ለሆኑ ልጃገረዶች አሁንም በጣም ከፍተኛ ቢሆንም ዝቅተኛ ነው። የሴት ልጅ ግርዛት በትናንሽ ልጃገረዶች ላይ እንኳን በጣም ያነሰ ነው። ይህ አዝማሚያ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ አይደለም እና በጊዜ ሂደት ግልጽ ይሆናል። ወይ የግርዛት ድርጊቶች እየተቀያየሩ ነው– በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ያልተገረዙ ወጣት ልጃገረዶች እያደጉ ሲሄዱ ይገረዛሉ፤ ወይም የግርዛት የስርጭት መጠኑ እየቀነሰ ነው። የብልት አጥብቦ መስፋት ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። የብልት ማጥበብ በሁሉም የልጃገረዶች ቡድን (ከአዋቂ ሴቶች ጋር ሲወዳደር) ብዙም ያልተለመደ ነው፣ ነገር ግን በትናንሽ ልጃገረዶች (ከ0-5 አመት እድሜ ያላቸው) (73%) ከትልልቅ ልጃገረዶች (ከ12-17 አመት እድሜ ያላቸው) (78%) የተለመደ ነው። በድጋሚ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ያልሆነ እና በጊዜ ሂደት፣ ግልጽ የሚሆን ጉዳይ ነው። ምክንያቱም በአዋቂ ሴቶች እና ልጃገረዶች መካከል የግርዛት አይነት ልዩነቶች በግልጽ የሚታዩ ቢሆኑም፣ ስለ ብልት መጥበብ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በወላጆች ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት በጣም ጥቂት ወጣት ልጃገረዶች አሉ። ስሌቶች በናሙና በተመረጡ የወላጆች ዝርዝር ውስጥ የተመረኮዘ ሲሆን ይህም ዕድሜያቸው 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ 1,241 አዋቂ ሴቶች እና 898 ዕድሜያቸው ከ12-17 የሆኑ 898 ልጃገረዶች ብቻ ናቸው፣ ነገር ግን ከ0–2 የሆኑ 112 ልጃገረዶች ብቻ፣ ከ3–5 የሆኑ 193 ልጃገረዶች፣ 264 ሴቶች 6–8፣ እና 211 ሴት ልጆች ከ9–11 እድሜ ያላቸው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በግርዛት ጊዜ ብልት ከመዘጋቱ በፊት ምን ያህል ሥጋ እንደሚወድ የወላጆች ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ ድርጊቶች ከብዷታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንደሚሄድ፣ ብልትን ማጥበብንም ጨምሮ። ዕድሜያቸው ከ12-17 የሆኑ ልጃገረዶች 48% የሚሆኑት ሁሉም የውጭ ብልቶቻቸው ተወግደዋል። ከ9-11 አመት እድሜ ያላቸው ልጃገረዶች መካከል መጠኑ ወደ 40% ዝቅ ብሏል፤ ከ6-8 አመት እድሜ ያላቸው ልጃገረዶች ወደ 36% ዝቅ ብሏል።

የወላጆች እንደገለፁት የሴት ልጃገረድ ልጆቻቸው ግርዛት የሚፈጸምበት ዕድሜ ልክ ዋናዎቹ ታዳጊ ልጃገረዶች እንደሚገረዙበት እድሜ በዞንና በወረዳው ይለያያል። በአይሳይታ አውሲ ረሱ [ዞን 1]፣ እና ሃዲሌላ፣ ሃሪ ረሱ [ዞን 5] ፣ ሴት ልጆች ገና በጨቅላነታቸው ጥቂት ሳምንታት እንደሞላቸው ተገርዘዋል። በሰሙሮቢ፣ ሃሪ ረሱ [ዞን 5] ሴት ልጅ ግርዛት የሚፈጸምባት አማካይ ዕድሜ 4.5 ዓመት ነበር። ግርዛት ከተፈጸመባቸው ልጃገረዶች መካከል፣ ሁሉም ማለት ይቻላል (95%) በባህላዊ ገራዥ እንደተቆረጡ የወላጆች ተናግረዋል። በጤና አጠባበቅ ሰራተኛ የተገረዙ አምስት ልጃገረዶች ብቻ ናቸው ተብሏል።


በአፋር ጥናት ቦታዎች የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች እንደተናገሩት የሴት ልጅ ግርዛት ከጥቅሞች ይልቅ የሚያስከትላቸው አደጋዎች ያመዝናሉ (72% በተቃራኒ 44%) (ምስል 25 ይመልከቱ)። በልጃገረዶችና በታዳጊ ወንድ ልጆች መካከል ወይም በታዳጊ ወጣቶች መካከል በአውሲ ረሱ [ዞን 1] እና በሃሪ ረሱ [ዞን 5] ጉልህ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አልነበረም። የግርዛት አደጋን ከገለጹት ውስጥ፣ ሁሉም ማለት ይቻላል (98%)፣ የሴት ልጅ ግርዛት ልጅ መውለድን አስቸጋሪ እንደሚያደርገው አምነዋል። አብዛኞቹ (56%) የሴት ልጅ ግርዛት በግብረ ሥጋ ግንኙነት ጊዜ የህመም ስሜት እንደሚፈጥር ተስማምተዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ንዑሳን ታዳጊ ወጣቶች እንደተናገሩት የሴት ልጅ ግርዛት ኢንፌክሽን (37%) እና ደም መፍሰስ (25%) ያስከትላል። የግርዛት ጥቅሞችን ከተናገሩት ውስጥ፣ 82% የሚሆኑት የሴቶችን የወሲብ ፍላጎት ይቀንሳል፣ 30% ልጃገረዶችን ከአስገድዶ መድፈር እንደሚከላከል እና 29% ልጃገረዶች ባልን እንዲስቡ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በአፋር ጥናት ቦታዎች የሚገኙ ወላጆችወላጆች እንደተናገሩትም የሴት ልጅ ግርዛት ከጥቅሞች(73%) የበለጠ የምያስከትላቸው አደጋዎች (52%) አሉት (ምስል 26 ይመልከቱ)። ነገር ግን ከታዳጊ ከወጣቶች በተለየ፣ ትልቅ የፆታ ልዩነቶች ነበሩ። ወንድ የወላጆች (85%) ከሴት የወላጆች (71%) የበለጠ ግርዛት የሚያስከትለውን አደጋዎች ተናግረዋል፡ ፡ በዚህ መሰረት ሴት የወላጆች ከወንድ የወላጆች የበለጠ የግርዛት ጥቅሞችን (53% በተቀራኒ 43%) ተናግረዋል።


ምስል 24: በሴት ቤተሰብ የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ በእድሜ ደረጃ፣ በአፋር አሳዳጊዎች እንደተገለጸው




ምስል 25: የአፋር ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳት እና ጥቅም ያላቸው እምነት




ምስል 26: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳቶችና ጥቅሞች ያላቸው እምነት




የአካባቢ ልዩነቶች በጣም አናሳ ነበሩ። ግርዛት የሚያስከትለውን አደጋዎች ከገለጹት የወላጆች ውስጥ፣ ሁሉም (99%) ማለት ይቻላል ግርዛት ልጅ መውለድን አስቸጋሪ እንደሚያደርግ አምነዋል። አብዛኞቹ (66%) በግብረ ሥጋ ግንኙነት ገዜ ህመም እንደሚፈጥር ተስማምተዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ንዑሳን ወላጆች የሴት ልጅ ግርዛት ወደ ኢንፌክሽን (39%) እና ህመም (31%) እንደሚያስከትል ተናግረዋል። የግርዛት ጥቅሞችን ከተናገሩት ውስጥ 85% የሚሆኑት የሴቶችን የወሲብ ፍላጎት እንደሚቀንስ፣ 30% የሴቶችን ባህሪ እንደሚያሻሽል (ከወሲብ ጋር ያልተገናኘ)፣ 26% ልጃገረዶችን ከአስገድዶ መድፈር እንደሚከላከል እና 24% ልጃገረዶችን ባልን ለመሳብ እንደሚረዳቸው ተናግረዋል።

2/3ኛው (66%) የአፋር ታዳጊ ወጣቶች፣ ያለፆታ ልዩነት፣ የሴት ልጅ ግርዛት የሃይማኖት ገዴታ መሆኑን ተስማምተዋል (ምስል 27 ይመልከቱ)። በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የሚኖሩ ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] (70% በተቃራኒ 58%) የበለጠ ስምምነታቸውን ገልጸዋል። ነገር ግን በጣም ጥቂት ተሳታፊዎች የሴት ልጅ ግርዛት መቀጠል እንዳለበት ተስማምተዋል። በዚህ መግለጫ የተስማሙት 30% ብቻ ናቸው። በሃሪ ረሱ ያሉ (33%) ታዳጊ ወጠቶች ከአውሲ ረሱ (25%) የበለጠ ስምምነታቸውን ገልጸዋል። ታዳጊ እና ወጣት ወንዶች ልጆች ከታዳጊ እና ወጣት ሴቶች (35% በተቃራኒ 30%) የበለጠ ስምምነታቸውን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ አብዛኛው ወላጆችበአፋር የጥናት ቦታዎች የሚገኙ ወላጆች (88%) እንደገለፁት፣ በአካባቢያቸው ያሉ ልጃገረዶች ከጋብቻ በፊት እንዲገረዙ ይጠበቃል (ምስል 28 ይመልከቱ)። ከሞላ ጎደል፣ ብዙዎች (86%) እንደተናገሩት ልጃገረዶች ከጋብቻ በፊት ተቀዶ መሰፋት ይጠበቅባቸዋል። ምንም እንኳን የቦታ ልዩነት አነስተኛ ቢሆንም እናቶች ከአባቶች በበለጠ ሁኔታ (89% በተቃራኒ 73%) የሴት ልጅ ግርዛት እና ብልት አጥብቦ መስፋት (97% በተቃራኒ 74%) እንደሚጠበቅ ተናግረዋል። የወላጆች ልክ እንደ ታዳጊ ጎልማሳ

ምስል 27: የአፋር ወጣቶች ስለ የሴት ልጅ ግርዛት ሃይማኖታዊ ግዴታ እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት




### ሣጥን2: የአፋር እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ስለመምጣቱ


የረጅም ጊዜ ጥናት እንደሚያሳየው በጥናት ቦታዎች ላይ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያለው አመለካከት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ነው። ከመነሻ ይልቅ አጋማሽ ጥናት ላይ ወላጆች የሴት ልጅ ግርዛት አደጋዎች እንዳሉት (43 ከ73 በመቶ) ሪፖርት የማድረግ ዕድል አላቸው። የሴት ልጅ ግርዛት መቀጠል እንዳለበት ሪፖርት የማድረግ እድላቸውም አነስተኛ ነበር (38 ከ63 በመቶ)። የሚገርመው ነገር፣ ወላጆች በአጋማሽ ጥናት ላይ የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅሞች እንዳሉት ከመነሻ ጥናት (52% ከ 45%) የበለጠ ሪፖርት የማድረግ እድል አላቸው። ወላጆች የሴት ልጅ ግርዛት ሃይማኖታዊ ነው ብለው ማመን ላይ ምንም ለውጦች አላሳዩም።

በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች* እምነትም በመነሻና አጋማሽ ጥናት ጊዜ ለውጥ አሳይቷል። አጋማሽ ጥናት ጊዜ ልጃገረዶች ከመነሻ መስመር (71% ከ 6%) የበለጠ የሴት ልጅ ግርዛት አደጋዎችን ያውቃሉ። አጋማሽ ጥናት ጊዜ ልጃገረዶች የሴት ልጅ ግርዛት መቀጠል አለበት ብለው የማመን እድላቸው ከመነሻ ጊዜው ያነሰ ነበር (30% ከ 59%)። የሚገርመው ነገር፣ ልጃገረዶች - ልክ እንደ ወላጆች - በአጋማሽ ጥናት ጊዜ የግርዛት ጥቅሞችን ሪፖርት የማድረግ እድላቸው ከመነሻ አኳያ ከፈተኛ (45% በተቃራኒ 25%) ነበር። የሴት ልጅ ግርዛት ሀይማኖታዊ ስለመሆኑ በሴቶች እምነት ላይ ምንም ለውጦች አልነበሩም። በአውሲ ራሱ [ዞን 1] አሳይታ የምትገኝ አንዲት የ23 ዓመቷ ወጣት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃም እውቅና ያለው መሆኑን ተናግራለች።

> ውይይቶችን የምታመቻች ታዋቂ ባህላዊ አዋላጅ አለች… በዚህ ቀበሌ የሴት ልጅ ግርዛትን በመቀነስ ረገድ የተሳካላት ሴት ነበረች። በኋላ፣ ለስኬቷ መጽሃፍ ተጽፎ ሽልማት ተሰጣት… ወደ ማህበረሰቡ ለቃለ መጠይቅ ሲመጡ፣ ፎቶዋ ያለበት መጽሃፍ በእጃቸው ይዘው ነበር።

*በመነሻ ደረጃ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጥያቄዎች የተጠየቁት ልጃገረዶች ብቻ ነበሩ።

ምስል 28: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ተጠባቂነት፣ ሃይማኖታዊ ግዴታዎች እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት





ልጆች የሴት ልጅ ግርዛት በሀይማኖት (76%) እንደሚፈለግ ተስማምተዋል። እናቶች ከአባቶች የበለጠ (77 % በተቃራኒ 67%) ስምምነታቸውን ገልጸዋል። የሴት ልጅ ግርዛት እንዲቀጥል የሚደረገው ድጋፍ በሁሉም ቡድኖች (በአጠቃላይ 38%) ተመሳሳይ ነበር ።

የአፋር ወጣቶች የሴት ልጅ ግርዛትን[6] ዋና ምክንያት[7] እንዲገልጹ ሲጠየቁ፤ ባህል (39%) እና ሀይማኖት (28%) በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ግፊት (21%) እና የሴቶችን መልካም ባህሪ ማረጋገጥ (11%) የጋራ መልሶች ነበሩ (ምስል 29 ይመልከቱ)። የሥርዓተ-ፆታ እና የቦታ ልዩነቶች ጉልህ ነበሩ፡ ፡ ታዳጊ እና ወጣት ወንድ ልጆች (63%) እና ወጣቶች በአውሲ ረሱ (ዞን 1) (50%) ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (35%) እና ወጣቶች ከሃሪ ረሱ (ዞን 5) ወጣቶች (33%) የበለጠ ባህልን በምክንያትነት ለይተው አስቀምጠዋል። ምንም እንኳን ወንዶች ግርዛት የተፈፀመባትን ሚስት ለማግባት የሚመርጡባቸው ምክንያቶች ቢኖሩም፣ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች (30%) ታዳጊ እና ወጣት ወንድ ልጆች ይልቅ ሀይማኖትን (12%) በምክንያትነት ለይተዋል (ሣጥን 2 ይመልከቱ)። በሃሪ ረሱ (ዞን 5) ሴቶች (12%) እና ታዳጊ ወጣቶች (13%) በአውሲ ረሱ (ዞን 1) ከሚኖሩ አቻዎቻቸው ከታዳጊ ወንድ ልጆች (4%) ወይም ከኩዮቻቸው (7%) የበለጠ ለሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት የሴት ልጆችን መልካም ባህሪ ለማረጋገጥ እንደሆነ ተናግረዋል፡ ፡ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ጫና በሁሉም ቡድኖች ላይ ተመሳሳይ ነበር። ምንም እንኳን የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ከሀሪ ረሱ (ዞን 5) የበለጠ ጠንካራ ቢሆኑም፣ ታዳጊ ወጣቶች ሃይማኖትን እንደዋና የሴት ልጅ ግርዛት ዘዋሪ ኃይል በመጥቀስ ረገድ ዘናዊ ልዩነቶች አልነበሩም።

ልክ እንደ ታዳጊ ልጆቻቸው፣ የሴት ልጅ ግርዛትን ዋና ምክንያት እንዲገልጹ ሲጠየቁ፣ የአፋር የወላጆች በዋናነት ባህልን (38%) እና ሀይማኖትን (24%) አስቀምጠዋል። ሆኖም ግን አንዳንዶች የሴቶችን የወሲብ ፍላጎት መቀነስ (12%) እና ሌሎች ምክንያቶችን (26%) ጠቅሰዋል (ምስል 31 ይመልከቱ)። ወንድ የወላጆች (43%) እና በአውሲ ረሱ (ዞን 1) የወላጆች (48%) ከሴቶች የወላጆች (38%) እና በሃሪ


ምስል 29: የአፋር ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት




6 ግርዛት የተፈፀመባቸው ልጃገረዶች ግርዛት ያደረጉበት ዋና ምክንያት ተጠይቀው ነበር። ግርዛት ያልተፈጸመባቸው ታዳጊ ወንዶች እና ልጃገረዶች በአካባቢያቸው ስላለው የግርዛት ዋና ምክንያት ተጠይቀዋል።

7 ምላሽ ሰጪዎች በራሳቸው አንደበት እንዲመልሱ ተጠይቀዋል። ከዚያም ቃለ-መጠይቅ ጠያቂው መላሾቹ በማያውቁት መልኩ ምድቦችን መሰረተ። እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- የሀይማኖት ትዕዛዛት፣ ለማግባት ተመራጭነት፣ የወሲብ ፍላጎት መቀነስ፣ ከፆታዊ ግንኙነት ጋር ያልተገናኘ ባህሪን ማሻሻል፣ የማህበረሰብ ጫና፣ የቤተሰብ ጫና፣ ከአስገድዶ መድፈር መከላከል እና ሌሎችም።

ምስል 31: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት




ረሱ (ዞን 5) ከሚገኙ የወላጆች (33%) የበለጠ ባህልን እንደ ዋና ምክንያት ጠቅሰዋል፡፡ ሴት የወላጆች ከወንድ የወላጆች ሃይማኖትን በበለጠ መቅሰዋል (24% በተቃራኒ 18%)፡፡ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ውስጥ የሸሪአ ፍርድ ቤቶች ጠንካራ ቢሆንም ሃይማኖትን በሚጠቅሱ ሰዎች ላይ ምንም ዓይነት የቦታ ልዩነቶች አልነበሩም፡፡ ሴት የወላጆች (13%) እና በሃሪ ረሱ (ዞን 5) (15%) ከሚገኙ የወላጆች የሴቶችን የወሲብ ፍላጎት መቀነስ እንደ ወንድ የወላጆች (6%) እና በአውሲ ረሱ [ዞን 1] (8%) ከሚገኙ የወላጆች በእጥፍ ይበልጣል፡፡


በአፋር ክልል የጥናት ቦታዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ (48%) ታዳጊ ወጣቶች እና ከአንድ ሶስተኛ በላይ (39%) የአፋር የወላጆች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ምንም አይነት ህግ እንደማያውቁ ተናግረዋል (ምስል32 ይመልከቱ)፡፡ ታዳጊ እና ጎልማሳ ወንድ ልጆች ከልጃገረዶችና እና ወጣት ሴቶች የበለጠ አያውቁም ነበር፤ እና ወንድ የወላጆች ከሴት የወላጆች የበለጠ አያውቁም ነበር፡፡ ከቦታ አንጻር ልዩነቶች አልነበሩም፡፡ የታዳጊ ወጣቶች እና የወላጆች  ህጉ ምን እንደሚል ያላቸው ግንዛቤ ግን እጅግ በጣም ውስን ነበር፡፡ ብዙዎች በተመሳሳይ፣ "ህጉ ሁሉንም ዓይነት የሴት ልጅ ግርዛትን ይከለክላል" እና "ህጉ ከሱና በስተቀር ማንኛውንም አይነት ይከለክላል" በሚለው ተስማምተዋል፡፡

በአፋር የጥናት ቦታዎች ሁለት አምስተኛው (40%) የአፋር ወጣቶች፣ በሴት እና በወንድ መካከል ልዩነት ሳይኖር፣ በወደፊት ሴት ልጆቻቸው ላይ ግርዛትን ለመፈጸም እንዳሰቡ ተናግረዋል (ምስል 33 ይመልከቱ)፡፡ በሃሪ ረሱ [ዞን 5] (46%) ያህሉ ታዳጊ ወጣቶች በአውሲ ረሱ [ዞን 1] (28%) ካሉ አቻዎቻቸው የበለጠ ይህንን ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡ በሁሉም ቡድኖች፣ ወጣቶች ከአይነት 2 ወይም 3 ይልቅ ዓይነት 1 እንደሚመርጡ ተናግረዋል፡፡ ይህ የተባለው ቢኖርም፣ ዓይነት 2 በአውሲ ረሱ ይልቅ (8% በተቃራኒ 3%) በሀሪ ረሱ በብዛት ይመረጣል፡፡


በጥልቅ ቃለ-መጠይቆች ወቅት፣ ታዳጊዎችና ወጣት ወንዶች ስለወደፊት ሚስታቸው ግርዛት ሁኔታ የተለያዩ ምርጫዎችን ሪፖርት አድርገዋል፡፡ የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ ሆነው ባለትዳር የ22 ዓመት ታዳጊ ወጣት እንደገለጸው፣ ዓይነት 3 ግርዛት ከአሁን በኋላ ተመራጭ ባይሆንም ያልተገረዘችን ሴት ማግባት የማይታሰብ ነገር ነው፡-

> በአሁኑ ወቅት በአካባቢያችን ያሉ ታዳጊ ልጆች/ወንዶች ቀደም ሲል የነበረውን የሴት ልጅ ግርዛትን መተግበር የሚያስከትለውን ውጤት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የብልታቸው ጫፍ የተቆረጠባቸውን ልጃገረዶች ማግባት ይችላሉ፡፡ ያልተገረዘች ሴት ግን ማንም ሊያገባ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የልጃገረዶች የብልታቸው ጫፍ

ምስል 32: የአፋር ወጣቶች እና አሳዳጊዎች  ስለ ብሄራዊ የሴት ልጅ ግርዛት ህግ የማያውቁ



ምስል 33: የአፋር ወጣቶች ወደፊት በሴት ልጆቻቸው ላይ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመተግበር ያላቸው ፍላጎት




መቁረጥ ልጃገረዶች የወሲብ ፍላጎታቸው እንዲቀንሱ ይጠቅማቸዋል።

ነገር ግን የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነ ያላገባ የ18 አመት ታዳጊ ወጣት በዚህ ሃሳብ አይስማማም። ስለሆነም ጭራሽ ያልተገረዘችን ሚስት ለማግባት ያለው የሀሳብ ምህዳር እያደገ መምጣቱን ገልጿል።

በአካባቢያችን ብዙ አፋር ያልሆኑ ያልተገረዙ ልጃገረዶች አሉ፣ ነገር ግን መጥፎ ጠባይ የላቸውም ፣ ገር ናቸው፣ የዋህ ናቸው። ስለዚህ ያልተገረዙ ልጃገረዶች ከፍ ያለ የፆታ ፍላጎት እንደሌላቸው ተረድቻሁ፤ እናም ጾታዊ ግንኙነትን በመፈለግ በወንዶች ላይ አይዛለሉም።

የአውሲ ረሱ (ዞን 1) ነዋሪ የሆነ ያላገባ የ20 አመት ታዳጊ ወጣት አክሎ እንደገለጸው፣ ለመወሰን እንደሚቸገርና ሁለት ሚስቶችን በማግባት የራሱን ሀሳብ መወሰን እንደሚመርጥ እና እንደሚያወዳድራቸው ተናግሯል። “በእኔ ፍላጎት የተገረዙትን እና ያልተገረዙን ሴት ልጆች ማግባት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ስለምፈልግ ነው።” ብሏል።

ምንም እንኳን የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ታዳጊ ወጣት ወንዶች ለወደፊት ሚስታቸው የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ ምርጫቸው በዋነኛነት የተቀረፀው በሃይማኖታዊ እምነታቸው እንጂ ስለ ሴት ጾታ ባላቸው እምነት ባየሆንም፣ የአይነታዊ ጥናቱ ግኝት ግን የዚህ ተቃራኒ ነበር። ይህ የሚያመለክተው ታዳጊ ወጣት ወንዶች ላይ ያተኮሩ መልእክቶች በጥንቃቄ የተቀረጹ እና የልጃገረዶችን የወሲብ ፍላጎት ለማሻሻል ሳይሆን በወሲብ መስማማትን በሚያሸል መንገድ ነው። የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነ ያላገባ የ18 ዓመት ታዳጊ ወጣት እንደዚህ ያሉ መልዕክቶች እንዴት ሊሳሳቱ እንደሚችሉ ጎላ አድርጎ ገልጿል፡-

ሰዎች ልጃገረዶች ጥሩ ባህሪ እንዲኖራቸው ለማድረግ ግርዛትን ድርጊት ይፈጽማሉ። ሰዎች ልጃገረዶች ካልተገረዙ በስተቀር ከፍተኛ የፆታ ፍላጎት እንደሚኖራቸውና ከጋብቻ በፊት ወሲብ እንደሚጀምሩ ይገነዘባሉ። ያልተገረዙ ልጃገረዶች ከገቡ በኋላም ማመንዘር እንደሚፈጽሙ ሰዎች ይገነዘባሉ። በህይወቴ ያጋጠመኝ ይህ ነው። ከተገረዘች ልጃገረድ እና ካልተገረዘች ልጃገረድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜአለሁ፣ እናም ትልቅ ልዩነት አየሁ... የተገረዘችው የወሲብ ፍላጎቷ ዝቅተኛ ሲሆን ያልተገረዘው በአልጋ ላይ ስሚቷ የተነቃቃ ነበር።

የአይነታዊ ጥናቱ ተሳታፊዎች የዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶችን አረጋግጠዋል። በዚህም ሁሉም ማለት ይቻላል የሴት ልጅ ግርዛት አለም አቀፋዊ ተግባር መሆኑን ተስማምተዋል። አንድ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆኑ አባት ጠቅለል አድርገው ሲናገሩ፣ “በእኛ ማህበረሰብ ውስጥ ያልተገረዘች አንድም ልታገኝ አትችልም።” ብለዋል።የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነች የ18 ዓመት ታዳጊ ወጣት ሴት ስምምነቷን ስትገልጽ፣ “ከመገረዝ ነፃ የሆነ ማንም የለም።” ይህ የተባለው ቢኖርም፣ ሁሉም ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] የመጡ ጥቂት ምላሽ ሰጪዎች እንደተናገሩት፣ ትንሽ ቁጥር ያላቸው ነገር ግን ቁጥራቸው በማደግ ያለ ያልተገረዙ በጣም ወጣት ልጃገረዶች አሉ። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነ የ24 ዓመት አባት እንዲህ ብሏል፡-

ባለፉት ሦስት እና አራት ዓመታት ውስጥ የተወለዱ ብዙ ያልተገረዙ ልጃገረዶች አሉ። ልጄ ጨርሶ ካልተገረዙት ልጃገረዶች አንዷ ነች።


የአውሲ ረሱ (ዞን 1) ነዋሪ የሆነችው በወጣትነት ዕድሜ ላይ የምትገኝ ልጅ እናት አክለው እንደተናገሩት፣ ይህ ለውጥ የመጣው ሁሉንም ዓይነት የሴት ልጅ ግርዛቶች ለማስወገድ ብቸኛው መንገድ ሴት ልጆች የብልት ተልትሎ ማጥነብ ድርጊት እንዳይፈጸምባቸው ሀሳብ በሚያራምዱ የሀይማኖት አባቶች ጥረት መሆኑን ገልጸች።

የሃይማኖት መሪዎቹ የሱና ግርዛትን መተግበራችን ከቀጠልን የአፋር ባህላዊ ግርዛት ከሁለቱም የአካል ክፍሎች ላይ ያሉትን ሁሉንም ስጋዎች ማስወገድ የሚቻልበት እድል እንዳለ ነግረውናል። በዚህ ምክንያት ህዝቡ የሱና አይነት የሴት ልጅ ግርዛት እንዲቀጥል ምክር ተቀብሏል።

## ሣጥን3: የወደፊት ባለቤታቸውን የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ በሚመለከት የአፋር ወንድ ልጆች እና የወጣት ወንዶች ምርጫዎች

ጥናቱ ታዳጊዎችና ወጣት ወንዶችን ስለወደፊት ሚስታቸው የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ምርጫቸውን ጠይቋል፡፡ ምንም እንኳን 30% ታዳጊዎችና ወጣት ወንዶች ግርዛት መቀጠል እንዳለበት እና 57% የሚሆኑት የእህቶቻቸውን ግርዛት እንደሚደግፉ ቢናገሩም 72% የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛት የተፈጸመባትን ሚስት ማግባት እንደሚመርጡ ተናግረዋል (ምስል 31 ይመልከቱ)፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ (75%) ዓይነት 1 ግርዛት የተፈጸመባትን ሚስት ይመርጣሉ፡፡ ለዓይነት 3 ያለው ምርጫ እምብዛም ነው (6%)፡፡ ግርዛት የተፈጸመባት ሚስት ምርጫቸውን የገለጹ ታዳጊ እና ወጣት ወንድ ልጆች የመረጡበትን ዋና ምክንያት እንዲገልጹ ተጠይቀዋል፡፡ የሃይማኖት ግዴታ (83%) ይበልጡን የጋራ ምላሽ ነበር፡፡ የሚገርመው ነገር 63% የሚሆኑት ታዳጊ እና ወጣት ወንድ ልጆች ባህል ለግርዛት ዋና ምክንያት እንደሆነ ሲገልጹ፣ አንድም ታዳጊ እና ወጣት ወንድ ልጆች ግርዛት የተፈጸመባትን ሚስት በግላቸው የሚመርጡበት ዋና ምክንያት ባህልን አድርገው አልመረጡም፡፡

ምስል 30: የአፋር ወንዶች ልጆችና ወጣት ወንዶች ስለወደፊት ሚስታቸው የግርዛት ሁኔታ ያላቸው ምርጫ




በጥልቅ ቃለ-መጠይቆች ወቅት፣ ታዳጊዎችና ወጣት ወንዶች ስለወደፊት ሚስታቸው ግርዛት ሁኔታ የተለያዩ ምርጫዎችን ሪፖርት አድርገዋል፡፡ የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ ሆነው ባለትዳር የ22 ዓመት ታዳጊ ወጣት እንደገለጸው፣ ዓይነት 3 ግርዛት ከአሁን በኋላ ተመራጭ ባይሆንም ያልተገረዘችን ሴት ማግባት የማይታሰብ ነገር ነው፡-

> በአሁኑ ወቅት በአካባቢያችን ያሉ ታዳጊ ልጆች/ወንዶች ቀደም ሲል የነበረውን የሴት ልጅ ግርዛትን መተግበር የሚያስከትለውን ውጤት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የብልታቸው ጫፍ የተቆረጠባቸውን ልጃገረዶች ማግባት ይችላሉ፡፡ ያልተገረዘች ሴት ግን ማንም ሊያገባ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የልጃገረዶች የብልታቸው ጫፍ መቁረጥ ልጃገረዶች የወሲብ ፍላጎታቸው እንዲቀንሱ ይጠቅማቸዋል፡፡

ነገር ግን የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነ ያላገባ የ18 አመት ታዳጊ ወጣት በዚህ ሃሳብ አይስማማም፡፡ ስለሆነም ጭራሽ ያልተገረዘችን ሚስት ለማግባት ያለው የሀሳብ ምህዳር እያደገ መምጣቱን ገልጿል፡፡

> በአካባቢያችን ብዙ አፋር ያልሆኑ ያልተገረዙ ልጃገረዶች አሉ፣ ነገር ግን መጥፎ ጠባይ የላቸውም ፤ ገር ናቸው፣ የዋህ ናቸው፡፡ ስለዚህ ያልተገረዙ ልጃገረዶች ከፍ ያለ የፆታ ፍላጎት እንደሌላቸው ተረድቻሁ፤ እናም ጾታዊ ግንኙነትን በመፈለግ በወንዶች ላይ አይዛለሉም፡፡

የአውሲ ረሱ (ዞን 1) ነዋሪ የሆነ ያላገባ የ20 አመት ታዳጊ ወጣት አክሎ እንደገለጸው፣ ለመወሰን እንደሚቸገርና ሁለት ሚስቶችን በማግባት የራሱን ሀሳብ መወሰን እንደሚመርጥ እና እንደሚያወዳድራቸው ተናግሯል፡፡ “በእኔ ፍላጎት የተገረዙትን እና ያልተገረዙን ሴት ልጆች ማግባት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ስለምፈልግ ነው፡፡” ብሏል፡፡

ምንም እንኳን የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ታደጊ ወጣት ወንዶች ለወደፊት ሚስታቸው የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ ምርጫቸው በዋነኛነት የተቀረፀው በሃይማኖታዊ እምነታቸው እንጂ ስለ ሴት ጾታ ባላቸው እምነት ባየሆንም፣ የአይነታዊ ጥናቱ ግኝት ግን የዚህ ተቃራኒ ነበር፡፡ ይህ የሚያመለክተው ታዳጊ ወጣት ወንዶች ላይ ያተኮሩ መልእክቶች በጥንቃቄ የተቀረጹ እና የልጃገረዶችን የወሲብ ፍላጎት ለማሻሻል ሳይሆን በወሲብ መስማማትን በሚያሸል መንገድ ነው፡፡ የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነ ያላገባ የ18 ዓመት ታዳጊ ወጣት እንደዚህ ያሉ መልዕክቶች እንዴት ሊሳሳቱ እንደሚችሉ ኃሳ አድርጎ ገልጿል፡-

> ሰዎች ልጃገረዶች ጥሩ ባህሪ እንዲኖራቸው ለማድረግ ግርዛትን ድርጊት ይፈጽማሉ፡፡ ሰዎች ልጃገረዶች ካልተገረዙ በስተቀር ከፍተኛ የፆታ ፍላጎት እንደሚኖራቸውና ከጋብቻ በፊት ወሲብ እንደሚጀምሩ ይገነዘባሉ፡፡ ያልተገረዙ ልጃገረዶች ካገቡ በኋላም ማመንዘር እንደሚፈጽሙ ሰዎች ይገነዘባሉ፡፡ በህይወቴ ያጋጠመኝ ይህ ነው፡፡ ከተገረዘች ልጃገረድ እና ካልተገረዘች ልጃገረድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሜአለሁ፣ እናም ትልቅ ልዩነት አየሁ… የተገረዘቸው የወሲብ ፍላጎቷ ዝቅተኛ ሲሆን ያልተገረዘው በአልጋ ላይ ስሚቷ የተነቃቃ ነበር፡፡

ድርጊቱን በማስወገድ ወይም በመቀነስ ረገድ መሻሻል ቢታይም ሰፋ ያሉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ማንኛውም ሴት ልጅ ከግርዛት ነፃ ልትሆን ትችላለች ብሎ መገመት አይቻልም፡፡የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነች የ17 ዓመቷ ታዳጊ ልጃገረድ እንደገለጸችው፣ የሴት ልጅ ግርዛት በተለምዶ በህፃንነት ጊዜ ሲካሄድ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን "ልጁቷ ካደገች በኋላ እስከ ዘጠኝ አመቷ ድረስ" እንደሚደረግ ተናግራለች፡፡ የዚሁ ዞን ነዋሪ የሆነ  የ15 ዓመት ታዳጊ ልጅ እንዲህ ሲል አብራርቷል፡-

> ያልተገረዘች የ7 አመት እህት አለችኝ፡፡ ብዙ ያልተገረዙ ጓደኞቿም አሏት… ሴት ልጃቸውን እንዲገረዙ የፈቀዱ ወላጆች እና ቆራጮች ቢያደርጉት ይቀጣሉ…ስለዚህ የእህቴን የብልት ጫፍ አላነሳንም፡፡ ወደፊትም ይህን አናደርገውም፡፡

በአፋር ስለ ልማዳዊ የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች ከባድነትም ዓለም አቀፋዊ ስምምነት ነበር፡፡ ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] የመጡ አባት እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል፡-

> ነፍሰ ጡር እናቶችን በወሊድ ጊዜ የሚረዱ ሴቶች ልጃገረዶችን ይገርዛሉ፤ እናም መጀመሪያ የሴት ልጅን የብልት ጫፍ ከስር-መሰረቱ በማውጣት ግራ እና ቀኝ ያለውን ሥጋ ይቆርጣሉ፡፡ የብልት ጫፍ እና መላውን ሥጋ ካስወገዱ በኋላ የተቆረጠው አካል በደም እንዲጣበቅ እና የብልት ቀዳዳቸውን ለመዝጋት ወይም ለማጥበብ የሴት ልጅን ጭን በገመድ ያስራሉ፡፡

በጥናት ቦታዎች የሚገኙ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ከሞላ ጎደል ሁሉም ማለት ይቻላል ዓይነት 3 ግርዛት እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል፡፡ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የምትኖር የ15 ዓመቷ ልጅ እንደገለጸችው፣ "ትንሽ እያለን ለአራት ቀናት እግሮቻችንን ታስረን ተገረዝን፡፡" ብላለች፡፡ የተራክቦ-ብልቷ ምን ያህል እንደተወገደ ዝርዝር መረጃ መስጠት አልቻለችም፡ "ከሕፃንነቴ ጀምሮ ስለ ተገረዝሁ፣ ስለ አሠራሩ አላውቅም፡፡" ብላለች፡፡

በቅርብ ዓመታት ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች እንዴት እየተለዋወጡ እንደመጡ ብዙ መግባባት አልነበረም፡፡ አንዳንድ ምላሽ ሰጪዎች፣ በዋናነት ከሀሪ ረሱ [ዞን 5] ፣ ነገር ግን በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ራቅ ካሉ ማህበረሰቦች የመጡ እንደተናገሩት ፣ ባህላዊ ዓይነት 3 በስፋት መተግበሩን ቀጥሏል፡፡ የሃሪ ረሱ ነዋሪ የሆነች የ14 ዓመቷ ልጅ እንዲህ በማለት ታስታውሳለች፣

> አንዲት ሴት የተገረዘች በቅርቡ አይቻለሁ፣ እሷ ዘመዴ ነች፡፡ ከተቆረጠች በኋላ እግሮቿ ታስረው ነበር… ብዙ ሥጋ ቆርጠዋል፡፡

የአውሲ ረሱ (ዞን 1) ነዋሪ የሆኑ አባት ያክላሉ፣

> እንደ ቀድሞው ጊዜ ግርዛትን የሚፈጽሙ ሰዎችም አሉ እነሱም ራቅ ባሉ ገጠራማ አካባቢዎች የሚኖሩ ናቸው፡፡

ይህ የተባለው ቢኖርም፣ ብዙ ወጣቶች - ብዙ ጊዜ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የሚኖሩ - ታናሽ እህቶቻቸው ወይም ሴት ልጆቻቸው ብልታቸውን ተልትሎ የማጥበብ ድርጊት እንዳልተፈጸመባቸው እና የብልታቸውን ጫፍ "ብቻ" እንዲቆረጠ ተናግረዋል፡ ፡ በአውሲ ረሱ የምትኖር የ18 ዓመቷ ታዳጊ ወጣት እንደተናገረችው፣

> የእኔና የቅርብ እህቴ የብልት አቆራረጥ አንድ ነው፡፡ በአጠቃላይ መወገድ እና የተሰፋ ነው፡፡ ሌሎቹ ሦስቱ እህቶቼ ሱና የነበራቸው ሲሆን፣ የላይኛው ክፍል ብቻተወግዷል፡፡

የ19 ዓመቷ የሃሪ ራሱ ሴት ወጣት 'ቀደም ሲል እግራቸውን ያስሩ ነበር አሁን ግን ሱና እየተለማመዱ ነው' ስትል ትናገራለች፡፡

የግርዛት ድርጊቶች ተለዋዋጭነታቸው በምላሽ ሰጪዎች "ሱና" (የተፈቀደ) በሚለው ቃል የተሸፈኑ(የተጋረዱ) ናቸው፡፡ በአፋር የሚገኙ የሀይማኖት አባቶች የሴት ልጅ ብልት ተልትሎ የማጥበብ ድርጊት እንዲወገድ የሴት ልጅ ብልት ጫፍ  "ሀራም" (የተከለከለ) የሚል ሀሳብ በማበጀት እና የሴት ልጅ የተራክቦ-ብልት ጫፍ  ብቻ መቁረጥን በማበረታታት የድጋፍ ስራ ሰርተዋል፡፡ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የምትኖር አንዲት የ21 ዓመት ታዳጊ በለትዳር ወጣት እንደተናገረችው፣ "አሁን የተራክቦ-ብልት የላይኛው ክፍል የሆነውን "ሐራም" የሚባለውን ክፍል ብቻ ነው የሚያስወግዱት፡፡" የዚሁ ዞን ነዋሪ እናት ተናግራለች፡

> የሀይማኖት አባቶች የሚሰጡት ትምህርት የአፋርን ባህላዊ የግርዛት አይነት መተግበርን የሚከለክል እና የሴት ብልት የጎን ስጋን ማስወገድን ይከለክላል፡፡ በዚህ ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛት የሱና አይነት አሁን በሁሉም ቦታ እየተተገበረ ነው፡፡

ሱና ማለት በተግባር ግን በጣም የተለያየ ነው፡፡ አንዳንድ ምላሽ ሰጪዎች ሱና የሚጠራው የተራክቦ-ብልትን ጫፍ ብቻ ማስወገድ እንደሆነ፣ ሌሎች ደግሞ የተራክቦ-ብልትን ጫፍ ሙሉ ማስወገድ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡ የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነ የ17 ዓመት ልጅ እንደገለጸው፣ "የሃይማኖት አባቶች የተራክቦ-ብልት ጫፍ እንድናስወግድ ያስተምሩናል፡፡" ነገር ግን ሌሎች እንደተናገሩት የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች እንደ ሱና የሚታዩት ምንም እንኳ ሁሉንም የውጫዊ የተራክቦ-ብልትን ክፍል ማስወገድ ቢያካትቱም የተራክቦ-ብልትን መከፈት ጥበትን እካላስከተሉ ድረስ ነው፡፡ የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነች የ19 ዓመት ባለትዳር  ታዳጊ ወጣት ሱና ማለት ምን ማለት እንደሆነ ስትጠየቅ እንዲህ ስትል መለሰች፡

> ቀደም ሲል ሁሉም ነገር የተቆረጠ፣የተሰፋ እና እግር የታሰረ ይመስል ነበር…ሱና የምንለው የተራክቦ-ብልት ከንፈር ብቻ መቁረጥ  ነው፡፡

በእርግጥ  በተመሳሳይ ዕድሜ ላይ የምትገኝ፣ ነገር ግን ከሀሪ ረሱ (ዞን 5) የመጣች ታዳጊ ወጣት የእህቷን ግርዛት ገልጻለች (በእናታቸው ቤት በአንድ ሌሊት በድብቅ የተደረገ) ሱና እንደሆነ፣ ምክንያቱም የሕፃኗ እግሮች የተፈቱት ከሰባት ቀናት

በኋላ ሳይሆን ከሶስት ቀናት በኋላ ነበር:- "እግሮቿ እንደተዘጉ ቢቀመጡም ከሶስት ቀናት በኋላ ማሰሪያውን ለቀቁት።."

የአፋርን የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊት ጎልቶ እንዳይወጣ የሚያደበዝዘው "ሱና" የሚለው ቃል ብቻ አይደለም። ብዙ ምላሽ ሰጪዎች "ግርዛት" እና "የሴት ልጅ ብልት መተልተል" የሚሉትን ቃላቶች የሚጠቀሙት ባህላዊ የሴት ልጅ ብልት ተልትሎ ማጥበብ ለማመልከት ብቻ ነው። ለምሳሌ በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የሚኖር አባት ስለ ሴት ልጆቹ እንዲህ ብሏል፣

የመጀመሪያዋ ሴት ልጄ በቀድሞ መንገድ ተገረዘች፣ እና ሌሎች ሴት ልጆቼ አልተገረዙም.... የመጀመሪያዋ ሴት ልጄ በመገረዟ ብዙ ተሠቃያለች። ህመሟን ካየሁ በኋላ ሌሎቹን ሴት ልጆቼን በአዲስ መንገድ ለመግረዝ ወሰንኩ።

በዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች መሰረት እና ወጣት ልጃገረዶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ምንም አይነት መልእክቶች ተላልፈው እንደማያውቁ መግለጻቸውን የተለመደ መሆኑን እንደ እጥረት መሰረት በማድረግ፣ በሁለቱም በአውሲ ረሱ [ዞን 1] እና በሃሪ ረሱ [ዞን] የሴት ልጅ ብልት ተልትሎ ማጥበብ በጣም አደገኛ ድርጊት መሆኑን ሰፊ ግንዛቤ ነበረ። አንድ እናት ከአውሲ ረሱ እንዲህ ስትል ገልጻለች፡

ይህ መጥፎ ነው ምክንያቱም ትንሽ ስለሆኑ መሽናት አይችሉም፣ ትልቅ ሲሆኑ የወር አበባቸው አያዩም፣ ሲጋቡም በወሲብ ጊዜ ህመም ይሰማል፣ ችግር ነው፣ እና በወሊድ ጊዜ ጉዳት ያስከትላል።

የግል ልምድ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ግንዛቤ ለመፍጠርም የራሱ ዋጋ አለው። የሀሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነች የ21 ዓመት ታዳጊ ወጣት እናት እንዲህ ብላለች፡

አይነት 3 የሴት ልጅ ግርዛት ሰለባ ከሆኑት መካከል አንዷ ነበርኩ እና በምወልድ ጊዜ ብዙ ተሠቃየሁ፣በጣም ከባድ የሽንት መሽኛ ቧንቧ ኢንፌክሽን ነበረብኝ እና በወር አበባ ጊዜ ብዙ እሰቃይ ነበር።

በዚያው ዞን የሚኖሩ አንድ አባት አክለውም፣

በወሲብ ወቅት ለወንዶች በጣም ፈታኝ እና ለሴቶችም በጣም ያማል። አንዳንድ ጊዜ የሴትን ድንግልና ለመውሰድ ከአንድ ወር በላይ ይወስዳል።

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ከባህላዊ ልማዳዊ ድርጊቶች ባህሪ አንጻር ምላሽ ሰጪው መጥፎ የማይባሉት የሴት ልጅ የግርዛት አይነቶች አደጋዎች እንደሚያስከትሉ ምንም አልተናገረም።

ነገር ግን አይነታዊ ጥናቱ የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅሞች እንዳሉት የጋራ እምነቶችን አሳይቷል። ሁሉም ማለት ይቻላል ትኩረት የሚያደርጉት የሴት ልጆችን ባህሪ በመቆጣጠር ላይ ነው። ምንም እንኳን እነዚህ ልጃገረዶች የቤት ዕቃዎችን እንዳይሰብሩ እና ወላጆቻቸውን እንዲያዳምጡ ማድረግን የሚያጠቃልሉ ቢሆንም፣ አብዛኞቹ ትረካዎች - ከዳሰሳ ጥናት ግኝቶች ጋር - የሴት ልጅን የግብረ ሥጋ ፍላጎት በመቆጣጠር እና የጾታ ባህሪያቸውን በመቆጣጠር ረገድ የሴት ልጅ ግርዛት ሚና ላይ ያተኮሩ ነበሩ። አንድ አባት ከሀሪ ረሱ [ዞን 5] እንደተናገሩት፣

ሴቶች ካልተገረዙ ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ይኖራቸዋል እና ከአንድ ወንድ/ባል ጋር ብቻ አይቆዩም እና ያመነዝራሉ ወይም ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይጀምራሉ።

የ18 ዓመት ታዳጊ ወጣት ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] ስምምነቱን በመግለጽ እንደተናገረው፣

ሰዎች የሴት ልጅ ግርዛትን ድርጊት የሚፈጽሙት ሴቶች ካልተገረዙ በቀር ከፍተኛ የግብረ-ስጋ ፍላጎት እንደሚኖራቸው እና የግብረ-ስጋ ግንኙነት በመፈለግ በወንዶች ላይ እንደሚዛለሉ እና እና ልጃገረዶች ከተገረዙ የግብረ ሥጋ ፍላጎታቸው እንደሚቀንስ [እና እነሱ] መልካም በህሪ ያሳያሉ።

ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት የልጃገረዶችን ባህሪ ለመቆጣጠር አስፈላጊ እንደሆነ ብዙም እርግጠኞች አልነበሩም። የ21 ዓመቷ ወጣት የሴት ልጅ ግርዛትን ጥቅሞችን እንድትገልጽ ስትጠየቅ የሚከተለውን ብላለች፣

በትክክል አላውቅም ነገር ግን [ካልተቆረጠች] ከቁጥጥር ውጭ ትሆናለች፣ የህ ደግሞ ለሴት ልጅ ጥሩ ባህሪ አይደለም።

ምላሽ ሰጪዎችም የሴት ልጅ ግርዛት ለሃይማኖት እና ለባህል ያለውን ጠቀሜታ በሰፊው ተናግረዋል። ሁሉም ከሞላ ጎደል እንደጠቀሱት የሴቶች እና ወንዶች ልጆች "ግርዛት" የእስልምና ግዴታ ነው። የአውሲ ረሱ (ዞን 1) ነዋሪ የሆነችው በታዳጊ ወጣት ዕድሜ ላይ የምትገኝ ልጅ እናት የሴት ልጅ ግርዛት ያልተፈፀመባቸው ልጃገረዶች ከሞት በኋላ እንደሚገለሉ ተናግራለች፡

ልጄን የገረዝኩበት ምክንያት እናቴና አባቴ ሴት ልጆች ካልተገረዙ አላህ እንደማይደሰት ይነግሩኝ ስለነበረ ነው።

የ22 ዓመቷ የሃሪ ረሱ [ዞን 5] እናት ልጇን ሳትገረዝ እንድትተዋት የነገሯት እናት ስምምነቷን ስትገልጽ የሚከተለውን ብላለች፣

ልጄ ሳትገረዝ እንድትቀር አልፈለኩም... በጣም መጥፎ ነው። ሳትገረዝ ከሞተች ወደ መንግሥተ ሰማያት አትገባም።" ።

ምላሽ ሰጪዎችም የሴት ልጅ ግርዛትን ቀጣይነት ለአፋር ባህል ራሱን እየደገመ እንዲሄድ ጠቃሚ ነው ብለውታል። የአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነ የ20 ዓመት ወጣት እንደገለጸው፣ "ሴት ልጆችን ከአካባቢው ባህል ጋር ለመስማማት ግርዛት ሊመፈፀምባቸው ይገባል፡ መገረዝ ከማህበረሰባችን የባህል ወጎች መካከል በአካባቢያችን ላሉ ሴቶች የተሰጠ ነው። :" ብሏል። በርግጥ አንድ እናት ከራሱ (ዞን 5) በኩራት እንደገለጹት፣ የሴት ልጅ ግርዛት - እና የሴትን ልጅ ብልት ተልትሎ ማጥበብ - የአፋርን ባህል በዙሪያው ካሉት የሚለይ


የአፋር ሙሽራ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

ነው፡ “ተገርዘናል፤ ለዚህም ነው ልጆቻችን የምንገረዘው፡፡ ከኛ በቀር ይህ ባህል ያለው ማንም የለም፡፡” ብለዋል፡፡

በሴት ልጅ ግርዛት የድርጊቶች መለዋወጦች በስተጀርባ ያሉትን ተዋናዮችን፣ መልእክቶችን እና ኃይሎችን እንዲለዩ ሲጠየቁ፣ ምላሽ ሰጪዎች የአካባቢ ባለስልጣናትን፣ አገልግሎት ሰጪዎችን (በተለይ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ አራስ እናቶችን እና ጨቅላ ሴት ልጆቻቸውን እና አስተማሪዎች)፣ ባህላዊ ገራዦችን፣ የሃይማኖት አባቶችን፣ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን - ሁሉም ሰው የሴትን ልጅ ብልት ተልትሎ ማጠበብ አደገኛ እንደሆነ እና የሴት ልጅ ግርዛት ሕገወጥ መሆኑን ግንዛቤ ለማስጨበጥ ጥረት አድርገዋል። አንድ አባት ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] እንደገለጹት፣

> ትምህርቱ የሚሰጠው የመንግስት አካላት፣ የሀይማኖት አባቶች እና ሴቶችን በሚገርዙ ሴቶች ቅንጅት ነው… መንግስት እና ሌሎች ህዝቡን ማስተማር የጀመሩት ከረጅም ጊዜ በፊት ነው፡፡

የ18 ዓመቷ ባለትዳር ታዳጊ ወጣት ከሃሪ ረሱ [ዞን 5] እንዲህ ብላለች፡

> የስድስተኛ ክፍል እያለሁ ትምህርት ቤት ውስጥ [ስለ ግርዛት አደጋዎች] መረጃውን አውቃለሁ… በብዙዎች እንቅስቃሴዎች፣ ስለ ህጻናት ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛት መወያየትን የመሳሰሉ ተግባራት ውስጥ እሳተፍ ነበር፡፡

የ23 ዓመቷ ባለትዳር ታዳጊ ወጣት ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] አክላ እንደተናገረችው፣

> ግርዛት ሲያደርጉ የተያዙት እስከ እድሜ ልክ እንደሚታሰሩ ተነግሮናል… [የሴቶች ጉዳይ ቢሮ] የሴቶች ጉዳዮች ክትትል እያደረገ ነበር፡፡ ሰዎች ደግሞ እስር ቤት መግባት አልፈለጉም ነበር!፡

ብዙ ምላሽ ሰጪዎች በሴት ልጅ ግርዛት ላይ የጤና እና የህግ መልእክት ለውጥን ለማበረታታት ወሳኝ ሚና ቢጫወቱም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሳካው ስኬት ግን የሃይማኖት መሪዎች የሴትን ልጅ ብልት ተልትሎ ማጥበብ መወገድ እንዳለበት፣ ሱና በእስልም የተፈቀደና የሀይማኖት ግዴታ ብለው በመስበካቸው ነው፡፡ ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] የመጡ አንድ አባትእንደገለጹት፣ “ይህን ትምህርቱን የተቀበልነው ሃይማኖታችን የሆነው እስልምና ስለ ግርዛት ድርጊት ከሚናገረው ጋር የሚስማማ በመሆኑ ነው፡፡” ብለዋል፡፡ ተጠያቂዎች በጋራ ሪፖርት እንዳደረጉት ለሌሎች ባህሎች ተጋለጭነት በቅርብ ጊዜ ለተስተዋሉ የግርዛት ድርጊቶች ለውጦች አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ የሴትን ብልት ከንፈር ሁሪያውን መተልተል በብዙ ታዳጊዎች እና ወጣቶች “የአማራ ግርዛት” ተብሎ ተለይቷል፡፡

የሚገርመው፣ የሴት ልጅ ግርዛት ከወንድ ግርዛት አንፃር የሚያስከትለውን አደጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ምንም እንኳን ምላሽ ሰጪዎች የሴት ልጅ ግርዛት ሁልጊዜ የሚከናወነው በባህላዊ ገራዦች (በተለምዶ በባህላዊ የወሊድ አገልግሎት የሚሰጡ ሴቶች) እንደሆነ ገልጸው፣ ወንዶች የሚገረዙት በጤና ጣቢያዎች በጤና ጥበቃ ሠራተኞች መሆኑን ጠቁመዋል፡፡. የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነች እናት እንደገለጸችውም፣ “ወንዶችን ለግርዛት ወደ ጤና ተቋም እንወስዳለን፣ [በአንጻሩ] ግን ሴቶችን በባህላዊ መንገድ እንገርዛለን፡፡” ብላለች፡፡


## ሶማሊ

አብዛኛዎቹ በጥናት በታዎች የሚገኙ የሶማሊ ዋና ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (80%) የሴት ልጅ ግርዛት እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል (ምስል 34 ይመልከቱ)። በፋፋን (83%) ከጃራር (73%) ከፍ ያለ ሲሆን፣ ይህም (ሰፋ ያለ ዘገባ ከሆነ የሴት ልጅ ግርዛት ዓለም አቀፋዊ ነው) በፋፋን ያሉ ልጃገረዶች በጃራር ከሚገኙ አቻዎቻቸው ይልቅ በለጋ እድሜያቸው ግርዛት ይፈጸምባቸዋል። የሴት ልጅ ግርዛት እንደተፈጸመባቸው ከተናገሩት ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች 100% የሚሆኑት በስፌት እንደተዘጋ ተናግረዋል። ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች በአማካይ በ9.3 ዓመታቸው የሴት ልጅ ግርዛት እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል። በሁሉም አካባቢዎች፣ ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች (99%) በባህላዊ ገራዥች እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል። የጤናው ዘርፍ በሚገባ በተደራጀበት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጉዳትን በመቀነስ ላይ በተሰማሩበት በፋፋን 2% የሚሆኑ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት በህክምና ባለሙያ እጅ እንደተደረገላቸው ተናግረዋል። ይህንን ሪፖርት ያደረገ ልጃገረድ በጃራር የለም።


የሶማሊ ወጣት ልጃገረዶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች ያላቸው እውቀት ከወላጆች ዕውቀት ያነሰ ሊሆን ስለሚችል፣ እና የመነሻ ጥናቱ አሠራሮች በቅርብ ዓመታት ውስጥ የግርዛት ድርጊቶች ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ስለተገነዘበ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ የዳሰሳ ጥናቱ ስለ ሴት ቤተሰብ አባላት፣ የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ፣ እና አይነት ጠይቋል። በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሁሉም ልጃገረዶች እና ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛትን ሁኔታ እና አይነት በእድሜ በመከፋፈል ብዙ ሳቢ ምስለ-ኩነቶችን ይለያል (ምስል 35 ይመልከቱ)። በመጀመሪያ፣ እና አሁን ባለው መረጃ መሰረት፣ የሴት ልጅ ግርዛት ጊዜ በጣም ተለዋዋጭ ነው። አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች በመካከለኛው የልጅነት ጊዜ ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛትን ሲፈጽሙ፣ አንዳንዶቹ በለጋ የልጅነት ጊዜ እና ሌሎች በወጣትነት ዕድሜ ላይ ናቸው። በዚህ ልዩነት ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ስለመሆኑ እስካሁን ማወቅ አይቻልም፣ ምንም እንኳን ከ12-14 ዓመት የሆናቸው ልጃገረዶች ዝቅተኛ ደረጃ (88%) ከ15-17 (96%) ከሴት ልጆች ጋር ሲነጻጸር ሪፖርት የተደረገው (88%)። በሁለተኛ ደረጃ ብልትን የማጥበብ መጠን በጊዜ ሂደት ቢቀየርም፣ እምብዛም የተለመደ እየሆነ አይመስልም። የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት (ከ0 እስከ 5 ያሉ) ተማሪዎች የሴት ልጅ ግርዛት እንደተፈጸመባቸውና እንደ አዋቂ ሴቶች (ዕድሜያቸው 18+ የሆኑ) (97% እና 96% በቅደም ተከተል) ብልታቸው እንደተሰፋ ተናግረዋል። ይህም ሲባል እንደ አፋር፣ በተንሹም በጥናታችን አካባቢ የሚወገደው ሥጋ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ነው። ከ0–5 አመት የሆናቸው ልጃገረዶችን ሳይጨምር (ምክንያቱም ግርዛት የተፈፀመባቸው ከ5 አመት በታች የሆኑ ልጃገረዶች ቁጥር በጣም ትንሽ (39 ብቻ) ስለሆነ)፣ እና በለጋ እድሚያቸው መገረዝ የሶማሊ ልጃገረዶች ያልተለመደ በመሆኑ፣ ይህ ማለት እነዚያ ቤተሰቦች በአሉበት ማህበረሰብ ከሌሎች ሊለያዩ ስለሚችሉ)፣ ከውስጥ እና ከውጪ ብልታቸው የተገረዙ ልጃገረዶች በእድሜ ክልል ቡድኖች ውስጥ አሀዛቸው ወርዷል (ለምሳሌ ከ15-17 ዓመት የሆናቸው 46% ልጃገረዶች) ከ6-8 ዓመት ዕድሜ ላይ ከሚገኙ ልጃገረዶች 37% ጋር ሲነጻጸር)። የወላጆች ስለ ሂደቱ ትንሽ የሕክምና ክትትል ሪፖርት አድርገዋል። በእንክብካቤ ሰጪዎች መሰረት አንዲት የ5 አመት ሴት ልጅ ብቻ በህክምና ባለሙያ እጅ ግርዛት አድርጋለች።

በድምሩ፣ የሶማሊ ታዳጊ ወጣቶች የሴት ልጅ ግርዛት ከአደጋዎች (31%) ይልቅ ጥቅሞች (35%) አሉት በማለት ትንሽ ከፍ ያለ እምነት አላቸው (ምስል 36 ይመልከቱ)። አጠቃላይ አሃዞች ግን ጉልህ ልዩነቶችን በፆታ አያሳዩም። ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ከታዳጊ እና ወጣት ወንድ ልጆች ይልቅ ጥቅሞችን በከፍተኛ ደረጃ ገልጸዋል (38% በተቃራኒ 26%)፤ ታዳጊ እና ወጣት ወንድ ልጆች ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የበለጠ አደጋን ገልጸዋል (41% በተቃራኒ 26%)። ስለ ጉዳቶች ግንዛቤ፣ ስለ ጥቅሞች ያለው አስተሳሰብ፣ እንደየአካባቢው ይለያያል። በጃራር ያሉ ወጣቶች (ልጃገረዶች ብዙውን ጊዜ በሶማሊላንድ ውስጥ ለሴት ልጅ ግርዛት ወደ ግል ክሊኒኮች ይወሰዳሉ) በፋፋን ካሉ አቻዎቻቸው የበለጠ አደጋውን ያውቃሉ (36% በተቃራኒ 29%)። ወጣቶች የሴት ልጅ ግርዛትን ጥቅሞች

ምስል 34: የሶማሊ ታዳጊ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ




ምስል 35: በሴት ቤተሰብ የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ በእድሜ ደረጃ፣ በሶማሊ አሳዳጊዎች እንደተገለጸው




እንዲለዩ ሲጠየቁ፣ በዋናነት “ባልን መሳብ” (78%) እንደሆነ ሪፖርት አድርገዋል። በተጨማሪም ልጃገረዶችን ከአስገድዶ መድፈር መከላከል (25%)፣ ልጅ መውለድን ማቃለል (17%)፣ የሴቶችን ከወሲብ ጋር ያልተገናኘ ባህሪን ማሻሻል (17%) እና ወሲባዊ እንቅስቃሴን ማቃለል (13%) እንደሆነ ሪፖርት አድርገዋል። አደጋዎችን እንዲለዩ ሲጠየቁ ወጣቶች (83%) በግርዛት ጊዜ፣ አስቸጋሪ ልጅ መውለድ (66%)፣ የሚያሰቃይ የግብረ ሥጋ ግንኙነት (59%) እና ደም መፍሰስ (42%) በብዛት ሪፖርት ተደርገዋል።

በወጣት ዕድሜ ላይ ከሚገኙት ልጆቻቸው ጋር ሲነጻጸሩ፣ የሶማሊ የወላጆች የሴት ልጅ ግርዛት ሁለቱም አደጋዎች (41%) እና ጥቅሞች (43%) እንዳላቸው ያምናሉ (ምስል 37

ምስል 36: የሶማሊ ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳቶችና ጥቅሞች ያላቸው እምነት



### ሣጥን4: የሶማሊያ ወላጆች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያላቸው እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ይመስላል

በሶማሊ የጥናት ቦታዎች የተካሄዱ የረጅም ጊዜ ጥናት ግኝቶች እንደሚያሳዩት፣ ወላጆች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያላቸው እምነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ ወላጆች የሴት ልጅ ግርዛት ስጋቶች እንዳሉት ሪፖርት የማድረግ ዕድላቸው ከመነሻ ይልቅ አጋማሽ ጥናት ላይ ከፍተኛ ነው(41% ከ 36 በመቶ)፡፡ የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅሞች (43% ከ 68%)፣ ሀይማኖትዊነት (36% ከ 63%) እና መቀጠል እንዳለበት (55% ከ 69%) ሪፖርት የማድረግ ዕድላቸው ደግሞ ያነሰ ነበር፡፡

የሶማሊያ ታዳጊ ልጃገረዶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያላቸው እምነት በመነሻ እና አጋማሽ ጥናት መካከል አልተለወጠም፡፡


ይመልከቱ)፡፡ ሴት እና ወንድ የወላጆች በተመሳሳይ ሁኔታ ድርጊቱ አደጋዎች አሉት ብለው የበለጠ ያምናሉ (41% በተቃራኒ 38%)፡፡ ሴት የወላጆች ከወንዶች የወላጆች የበለጠ ጥቅም አለው ብለው ያምናሉ (44% በተቃራኒ 34%)፡፡ የአካባቢ ልዩነቶች ጉልህ አልነበሩም፡፡ የወላጆች የሴት ልጅ ግርዛትን ስጋቶች እንዲለዩ ሲጠየቁ፣ በዋነኛነት ኢንፌክሽን (78%)፣ አስቸጋሪ ልጅ መውለድ (66%) እና ህመም (55%) እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ የወላጆች የሴት ልጅ ግርዛትን ጥቅሞች እንዲለዩ ሲጠየቁ፣ በዋነኛነት ባልን መሳብ (68%)፣ የወሲብ ፍላጎት መቀነስ (39%) እና ልጃገረዶችን ከአስገድዶ መድፈር መከላከል (17%) ናቸው፡፡

ብዙ ቁጥር ያላቸው የሶማሊ ወጣቶች (41%) በፕሮግራም አጋማሽ ጥናት ላይ የሴት ልጅ ግርዛት የሃይማኖት ግዴታ እንደሆነ ተናግረዋል (ምስል 38 ይመልከቱ)፡፡ ታዳጊና እና ወጣት ወንዶች የሴት ልጅ ግርዛት የሃይማኖት ግዴታ ነው የሚል እምነታቸው ከልጃገረዶች እን ወጣት ሴቶች ያነሰ ነበር (31% በተቃራኒ 44%)፡፡ የቦታ ልዩነቶች አልነበሩም፡፡ ከግማሽ በላይ (54%) ወጣቶች - በቦታ ወይም በወንዶች እና በሴቶች መካከል ምንም ልዩነት ሳይኖር - ድርጊቱ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡


በአጠቃላይ ሁሉም የሶማሊ የወላጆች (88%) በአካባቢያቸው ያሉ ልጃገረዶች ከጋብቻ በፊት ግርዛት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል (ምስል 39 ይመልከቱ)፡፡ ከሞላ ጎደል (81%) ብዙዎች እንደተናገሩት ልጃገረዶች ከጋብቻ በፊት ብልታቸው ተተልትሎ መሰፋት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የቦታ ልዩነት ባይኖርም አባቶች ከእናቶች ይልቅ ልጃገረዶች ብልታቸው ተተልትሎ መሰፋትን የበለጠ ይደግፋሉ (90% ነተቃራኒ 80%)፡፡ የወላጆች ልክ እንደ ወጣቶች ልጆቻቸው፣ የሴት ልጅ ግርዛት የሃይማኖት (36%) ግዴታ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ እንደገና የወጣቶችን ምላሾች በማስተጋባት፣ ወንድ የወላጆች ከሴቶች የወላጆች (28% በተቃራኒ 37%) እምነታቸው አነስተኛ ነበር፡፡ ለሴት ልጅ ግርዛት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ በሁሉም (በአጠቃላይ 55%) ቡድኖች ከፍተኛ ነበር ፡፡

የሴት ልጅ ግርዛትን ዋና ምክንያት እንዲገልጹ ሲጠየቁ፣ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (51%) የሶማሊ ወጣቶች ሃይማኖትን ጠቅሰዋል (ምስል 40 እና ሣጥን 5ይመልከቱ)፡፡ ነገር ግን ከአንድ ሦስተኛው በላይ (36%) ባህልን ጠቅሰዋል፡፡ ጥቂቶች (8%) የሴት ልጆችን ለጋብቻ ተመራጭነትን ጠቅሰዋል፡፡ የሥርዓተ-ፆታ እና የአከባቢ ልዩነቶች ጉልህ አልነበሩም፡፡


ምስል 37: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳቶችና ጥቅሞች ያላቸው እምነት





ምስል 38: የሶማሊወጣቶች ስለ የሴት ልጅ ግርዛት ሃይማኖታዊ ግዴታ እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት



ምስል 39: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ተጠባቂነት፣ ሃይማኖታዊ ግዴታዎች እና ቀጣይነት ያላቸው እምነት




ምስል 40: የሶማሊ ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት







የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ሶማሊ፣ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

## ሣጥን5: የሶማሊ ታዳጊና እና ወጣት ወንዶች የወደፊት ባለቤታቸው የግርዛት ሁኔታ ምርጫዎች በተመለከተ

ጥናቱ የሶማሊ ታዳጊና እና ወጣት ወንዶችን ለወደፊት ለሚስታቸው ስለሚመርጡት ግርዛት ምርጫ ጠይቋል። በዚህም መሰረት 43% ብቻ ወንዶች እና ወጣት ወንዶች የእህቶቻቸውን ግርዛት እንደሚደግፉ ሲናገሩ፣ 52% ብቻ የሚሆኑት ግርዛት መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል። 85% የሚሆኑት ደግሞ የሴት ልጅ ግርዛት የተፈጸመበትን ሚስት ማግባት እንደሚመርጡ ተናግረዋል። ከእነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ (54%) የሚሆኑት ዓይነት 1 የተገረዘችን ሚስት ይመርጣሉ። አንድ ሦስተኛው (31%) የሚጠጉት ግን የተተለተለውን እና የተሰፋውን ይመርጣሉ። ግርዛት የተፈጸመበት ሚስት ምርጫቸው እንደሆነች የገለጹ ታዳጊ እና ወጣት ወንዶች የመረጡበትን ዋና ምክንያት እንዲገልጹ ተጠይቀው የሃይማኖት ግዴታ በጣም የጋራ መልስ ነበር።

ምስል 41: የሶማሊ ወንዶች ልጆችና ወጣት ወንዶች ስለወደፊት ሚስታቸው የግርዛት ሁኔታ ያላቸው ምርጫ




ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች በሚደረጉበት ጊዜ ከሶማሊ ታዳጊ ወይም ወጣት ወንዶች መካከል አንዳቸውም ቢሆኑ የሴት ልጅ ግርዛት ያልተፈፀመበትን ሴት ለማግባት ፈቃደኛ መሆናቸውን አልተናገሩም። በእርግጥም የሴት ልጅ ግርዛት የሀይማኖት ግዴታ እነደሆነ የሴት ልጅ ግርዛት ያልፈፀሙ ልጃገረዶች ማግባት እንደማይችሉ በአጽንኦት ተናግረዋል። የ24 ዓመቱ የሃርሸን ከተማ ነዋሪ ወጣት እንደገለጸው፣ “ሃይማኖታችን ግዴታ ነው ባህላችንም አካል ነው። የግዴታ ነው። አዎን፣ ከባድ ነው።” ብሏል።

ምንም እንኳን አንዳንድ ታዳጊዎች እና ወጣቶች በአብዛኛው በሀርሸን ማእከላዊ ቀበሌዎች ውስጥ ሱና የተፈፀመበትን ሚስት እንደሚመርጡ ቢናገሩም፣ ምክንያቱም እምብዛም አደገኛ ስላልሆነ እና በሃይማኖት ስለተፈቀደ፣ አብዛኛዎቹ ለሚስት ከፍተኛ ምርጫ እንደነበራቸው አምነዋል። አብዛኞቹ ተሰፍቶ የተዘጋውን በከፍተኛ ደረጃ ምርጫቸው ዝንደሆነ አምነዋል። ይህም በድንግልና ማግባታቸውን ለማረጋገጥ ባላቸው ፍላጎት ብቻ የተገፋፉ መሆኑን አምነዋል። የሃርሼን ነዋሪ የሆነው የ19 ዓመት ወጣት እንደተናገረው፡፡ “የተሰፋውን እመርጣለሁ ምክንያቱም እሷ ንጹህ ነች። ካልተሰፋች ንጽህናዋን ልታጣ ትችላለች።” ብሏል። ከጓደኛዋ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ወጣት፣ “(ካልተሰፋች) ‘አርማሊ’ ትባላለች… እንደ ፍቺ ትቆጠራለች። … ወንዶች ድንግል ሴት ይፈልጋሉ።” ብሏል።


የሶማሊ ቤተሰብ አስተዳዳሪዎች የግርዛት ዋና ምክንያት ምን እንደሆነ እንዲገልጹ ሲጠየቁ፣ ከግማሽ በታች (45%) (ምስል 42 ይመልከቱ) ለግርዛት ዋና ምክንያት ሃይማኖት እንደሆነ እና ከአንድ ሶስተኛው በላይ ብቻ (45%) ሪፖርት አድርገዋል። 34%) ባህልን ሪፖርት አድርገዋል። አንድ አምስተኛው (21%) የልጃገረዶችን መልካም ባህሪ ማረጋገጥን ጨምሮ ሌሎች ምክንያቶችን ለይቷል። በወጣቶች ላይ እንደነበረው የፆታ እና የአከባቢ ልዩነቶች ጉልህ አልነበሩም።

ናቱ እንደሚያሳየው አብዛኞቹ የሶማሊ ወጣቶች የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ሃይማኖታዊ (66%) ወይም ዓለማዊ (82%) ህግን አያውቁም (ምስል 43 ይመልከቱ)። አብዛኞቹ ቡድኖች ሁለቱንም እንዳልሰሙ ተናግረዋል።


ጥናቱ እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ የሶማሊ ወላጆች የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ሃይማኖታዊ (62%) ወይም ዓለማዊ (73%) ህግን አያውቁም (ምስል 44 ይመልከቱ)። በድጋሚ፣ እንደ ሶማሊ ወጣቶች፣ አብዛኞቹ የወላጆች ሁለቱንም እንዳልሰሙ ተናግረዋል።

የሴት ልጅ ግርዛትን ስለማስቀጠል ባላቸው እምነት መሰረት፣ ከሶማሊ ወጣቶች መካከል ግማሽ ያህሉ (46%)፣ በሁሉም ቡድኖች፣ ወደፊት ሴት ልጆቻቸው ላይ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመፈፀም ማቀዳቸውን በጥናቱ ላይ ሪፖርት አድርገዋል (ምስል 45 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ሊፈፅሙት ባሰቡት የሴት ልጅ ግርዛት አይነት ግን የጾታ ልዩነት ታይቷል። በሴት ልጅ ግርዛት እና ህመም ውስጥ ያለፉት ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች አብዛኛዎቹ ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ይልቅ ዓይነት 1 ግርዛትን ወይም የብልት ጫፍ ብቻ መቁረጥን (43% ለ 33%)፣ እና ዓይነት 2 ወይም የሴት ልጅ ብልትን ውጫዊ አካልን ዙሪያ መተልተልን (43% ለ 21%) ለማስፈፀም ፈልገዋል። በዚሁ መሠረት ታዳጊና እና ወጣት ወንዶች ከልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የበለጠ የዓይነት 3 ግርዛት ወይንም የሴት ልጅ ብልትን


ምስል 42: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ያላቸው እምነት





ምስል 43: የሶማሊ ወጣቶች ስለ ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ሕግ ያላቸው እውቀት




ምስል 44: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ሕግ ያላቸው እውቀት




ምስል 45: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ ሃይማኖታዊ እና ዓለማዊ ሕግ ያላቸው እውቀት



አስተልትሎ መስፋትን (45% ለ 15%) ለማስፈፀም ይፈልጋሉ፡፡ የአካባቢ ልዩነቶችም ታይተዋል፤ በጃራር ያሉ ወጣቶች በፋፋን ካሉት እኩዮቻቸው ያነሰ ለማስገረዝ የፀና አቋም አሳይተዋል፡፡

አይነታዊ ጥናቱ እንደሚያሳየው የሴት ልጅ ግርዛት፣ ምንም እንኳን ከ12-14 አመት የሆናቸው ልጃገረዶች ከ15-17 አመት እድሜ ክልል ውስጥ ካሉ ልጃገረዶች ያነሰ ቢሆንም፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ አይደለም፡፡ ሁሉም ምላሽ ሰጪዎች ሁሉም ልጃገረዶች በመጨረሻ የሴት ልጅ ግርዛት እንደሚደረግላቸው ተስማምተዋል፡፡ የ19 አመቱ ወጣት የጎልጃኖ ወጣት እህቶችህ ግርዛት ተፈፅሞባቸዋል ወይ ተብሎ ሲጠየቅ፣ "በእርግጥ እዚህ ያሉ ልጃገረዶች ሁሉ የተሰፉ ናቸው፡፡" ሲል መልሷል፡፡ የቀበሌ ደረጃ የሴቶች ጉዳይ ቁልፍ መረጃ አቅራቢም በተመሳሳይ 'በሃይማኖታችንና በአካባቢው ልማዶች ሴት ልጆች አይገረዙ ማለት የማይታሰብ ነገር ነው፡፡" ብላለች፡፡

በዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች መሰረት፣ ልጃገረዶች የሴት ልጅ ግርዛት የሚደረጉበት ጊዜ በጣም ተለዋዋጭ እንደሆነ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ አብዛኛዎቹ እናቶች እና ልጃገረዶች እንደሚናገሩት አብዛኛው የሴት ልጅ ግርዛት የሚካሄደው ልጃገረዶች ከ8 እስከ 10 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ሲሆኑ ነው፡፡ ከሀርሼን የመጣ አስተማሪ እንዳለው ይህ እድሜያቸው ልጃገረዶች ህመሙን የሚቋቋሙበት እና፣ የልጃገረዶች ፀሎት ተሰሚ የሆነበት ነው፡፡

> ከሀይማኖቱ ጋር በተያያዘ አንድ ሰው ከ10 አመት ጀምሮ ሶላትን እንዲጀምር የተሰጠ መመሪያ አለ፤ በሀይማኖቱ መሰረት ልጃገረዶች በዛ እድሜያቸው መቀረጥ አለባቸው፡፡ አለበለዚያ የልጃገረዶች ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው እምነት ይህ ነው፡፡

ምላሽ ሰጪዎች የሴት ልጆች ከጋብቻ በፊት ግርዛትን መፈጸም ወሳኝ እንደሆነ ተስማምተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት እና በድርቅ ሲከሰት ህልውና ቅድሚያ ስለሚሰጠውና ብዙ ቤተሰቦችን ግርዛትን እንዲያዘገዩ ስለሚያስገድዳቸው፣ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች በታዳጊ ዕድሜያቸው በራሳቸው ፍላጎት ጋብቻ መፈፀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለመደ በመምጣቱ፣ የልጃገረዶች የግርዛት እድሜ ከድሮው ይልቅ እየቀነሰ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡ የሀርሼን ቁልፍ መረጃ ሰጭ እንዳብራራው እናቶች ሴት ልጆቻቸው እንዳያፍሩ በልጅነታቸው ግርዛት እንዲደረግላቸው እያመቻቹ ነው ሲል እንደሚከተለው ተናግሯል፡፡

> ልጃገረዶች በለጋ እድሜያቸው ይገረዛሉ... በ6 እና 7 አመት እድሜያቸው እየተገረዙ ናቸው... በ ያለ እድሜ ጋብቻ ምክንያት ነው፣ እና ቤተሰቦች ሴት ልጆቻቸው አልተገረዙም የሚለውን መገለል ማስወገድ ይፈልጋሉ፡፡

በአጠቃላይ፣ በጎልጃኖ የሚገኙ ምላሽ ሰጪዎች ከሀርሸን ከተማ ነዋሪዎች በበለጠ ሁኔታ ልጃገረዶች አሁንም በባህላዊ መንገድ እየተሰፉ ነው፣ ወይንም የብልት ትልተላና ማጥበብ ይፈፀምባቸዋል ብለዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሁሉንም ውጫዊ የሴት ብልትን በማስወገድ እና ከዚያም በመስፋት ወይም እሾህ በመጠቀም የሴት ብልትን ቀዳዳ ለማጥበብ - ልጅቷ አልጋ ላይ ታስራ እስከ አንድ ወር ድረስ እንዳትንቀሳቀስ እና ስፌቱ እንዳይፈታ ይደረጋል ብሏል፡፡ የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ19 አመት ወጣት ልምዷን እንደሚከተለው ገልጻለች፣ "ከቆረጡ በኋላ የሰውነት አካልን በእሾህ ይሰፉታል...እስከ አንድ ወርም ይቆያል፡፡" ይህም ሲባል፣ በሁለቱም ወረዳዎች ያሉ ምላሽ ሰጪዎች የግርዛት አሠራሮች እየተለወጡ መሆናቸውንና የሴት ልጅ ግርዛት አክራሪነት እየቀነሰ መምጣቱን ይናገራሉ፡፡ አንድ የወረዳ ደረጃ የሃርሸን ነዋሪ፣ "አሁን ሱና ብቻ ነው የቂንጥርን ትንሽ ክፍል ብቻ እየቆረጠ ያለው፡፡" በማለት ሲገልጽ፣ የ22 አመት ወጣት የጎልጃኖ ወጣት ደግሞ፣ "ዛሬ ልጃገረዶች የሱና አይነት ነው የሚገረዙት፡፡" ስትል ተናግራለች፡፡

በአፋር እንደታየው ግን የ'ሱና' የሴት ልጅ ግርዛት ልማድ አሁንም የተለያየ ነው፡፡ በተለይም ርቀው በሚገኙ ማህበረሰቦች ውስጥ ከፍተኛ ነው፡፡ በእርግጥ በሶማሊ ምላሽ ከሰጡ ልጃገረዶች ወይም እናቶች አንዳቸውም ቢሆኑ የብልት ጫፍ ወይም የቂንጥር መቁረጥ 'ብቻ' ግርዛት እንደተደረገላቸው አልመሰከሩም፡፡ ሱና እንደተፈፀመባቸው የተናገሩ አብዛኞቹ ልጃገረዶች ቢያንስ ሁለት ስፌት ነበራቸው (ይህም ካለፉት ስድስት እና ሰባት ስፌቶች አንፃር ትልቅ መሻሻል እንደነበረ አምነዋል)፡፡ እናም ምንም አይነት ስፌት እንደሌለባቸው የተናገሩ ልጃገረዶችም እንኳ የውጭ ብልታቸው በሙሉ መወገዱን ተናግረዋል፡፡ የ17 ዓመቷ የሀርሼን ልጅ እንዲህ ብላለች፣

> ከሱና አይነት ግርዛት በኋላ ለ 7 ቀናት እግሮችን ያስራሉ፡፡ ሴት ልጆች የሱና አይነት ግርዛት ከተደረገባቸው በኋላ ለአንድ ሳምንት ያህል እቤት ውስጥ ይቆያሉ፡፡ ወደ ሽንት ቤት አይወጣም፡፡ ለመዳን 1 ሳምንት ወይም 2 ሳምንታት ይወስዳል፡፡

የ22 ዓመቷ የጎልጃኖ ነዋሪ ወጣት አክላ፣ "ሱና የሚለየው በስፌት ብቻ ነው፡፡ የብልት አካልን በማስወገድ ተመሳሳይ ነው፡፡" ብላለች፡፡ የሱማሊ ግርዛትን የሚያወዛግበው 'ሱና' የሚለው ቃል ብቻ አይደለም፡፡ አንዳንድ ምላሽ ሰጪዎች 'ቂንጥር' የሚለውን ቃል የብልትን የውስጥ (አንዳንዴም ውጫዊ) ከንፈርን ጨምሮ ለመግለፅ ይጠቀማሉ፡፡ እናም ልክ እንደ አፋር እኩዮቻቸው አብዛኛዎቹ 'ግርዛት' የሚለውን ሀረግ የሚጠቀሙት ለባህላዊው ግርዛት (ብልትን ተልትሎ መስፋት) ብቻ ነው፡፡ የሃርሸን ተወላጅ የሆነ የጎሳ መሪ፣ "እነሆ፣ የሴት ልጅ ግርዛት አብቅቷል፣ እኛ ያለን የሱና ግርዛት ብቻ ነው፡፡" ብሏል፡፡

ከዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች በተቃራኒ፣ በአይነታዊ ዘዴ የተደረገው ጥናት በሴቶች ላይ የሴት ልጅ ግርዛትን ማን እንደሚፈፅም አንዳንድ ልዩነቶች አሳይቷል፡፡ በአንድ በኩል፣ አብዛኞቹ ምላሽ ሰጪዎች በአብዛኛዎቹ ልጃገረዶች ላይ ለሚደረገው ተግባር አሁንም ባህላዊ ገራዦች እንደሆኑ ተስማምተዋል፡፡ የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ21 ዓመቷ ወጣት፣



የ4 ልጆች እናት የሆነች የ21 አመት እናት፣ አፋር፣ ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

“ከወረዳው የመጣች አንድ የታወቀች ገራዥ (ግርዛት ፈፃሚ) አለች። ሴት ልጆችን የምትገርዝ እሷ ነች።” ስትል በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ በሃርሸን ውስጥ፣ በህክምና ባለሙያዎች የሴት ልጅ ግርዛትን እንደሚፈጽሙ ምላሽ ሰጪዎች ተናግረዋል። የሀርሸን ከተማ አንድ የሀይማኖት መሪ “በአንዳንድ ሁኔታዎች ነርሶቹ ራሳቸው ሴት ልጆችን ይገርዛሉ” ሲሉ የሃርሸን የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ሃላፊ በበኩላቸው፣ “የሴት ልጅ ግርዛት አብዛኛውን ጊዜ በጤና ጣቢያዎች ነው” የሚፈፀመው ብለዋል። በሐርሸን ከተማ ውስጥ የግርዛት ተግባር እየተከናወነ መሆኑን አጥብቃ የካደች የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ  በአሁኑ ጊዜ ልጃገረዶች የህመም ማስታገሻ እና አንቲባዮቲኮች እየተሰጡ ነው፤ ብዙውን ጊዜ እነዚህን ነገሮች የሚያቀርቡት ባህላዊ ገራዦች እንጂ የጤና አጠባበቅ ሠራተኞች እንዳልሆኑ ገልፃለች። አክላም፣ በሠርግ ምሽት ላይ የተሰፋውን ብልት የማላቀቅ ተግባሩም በመድሃኒት መታገዙ እየጨመረ እንደመጣ አስረድታለች።

የሴት ልጅ ግርዛትን አባባሽ ምክንያቶች ሲጠየቁ፣ በአይነታዊ ጥናት ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ሃይማኖት እና ባህልን ማለያየት አልቻሉም። በጥሞና ሲመረመሩ ግን አብዛኛውን ጊዜ ሃይማኖትና እና የሶማሊ ባሕልን የሴት ልጅ ግርዛት አንቀሳቃሽ ዋና ምክንያት አድርገው ይጠቅሳሉ። የሀርሼን ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደገለፀችው

> እኛ ሀይማኖተኛ ነን፤ ሃይማኖታዊ ዶግማውን የመከተል ግዴታ አለብን። በሃይማኖታዊ አስተምህሮታችን ላይ የተመሰረተ ሱና መከተል አለብን።

የዚያ ወረዳ ነዋሪ የሆነች የ18 አመት ወጣት በተመሳሳይ መልኩ፣ “ሀይማኖቱ ለሱና አይነት 1 ወይም 2 ስፌት መተግበር ይፈቅዳል ስለ ግርዛት ብቻ ይነግረናል ነገር ግን የልጅቷን ብልት ስለ መስፋት አይደለም… ከባህል የተነሳ ነው።” ስትል ተናግራለች። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች እናት ግርዛትን አለመፈጸም ለሶማሊ ሴት የማይታሰብ ነገር እንደሆነ ተስማምታለች፤ ምክንያቱም እሷን እና ልጇን ለትችት ያጋልጣል።

> አለመገረዝ ለኛ ነውር ነው። እኔ ሶማሊ ስለሆንኩ ልጄ መገረዝ አለባት። ሴት ልጄን ካላስገረዝኩ ሌሎች ደግሞ ሴት ልጇን እንደማታስገርዝ ሴት እየፈረጁ ይሰድቡኛል። ከዚህም በላይ ልጃገረዷ ያልተገረዘች ተብላ ትዋከባለች።

የሴት ልጅ ግርዛትን እና በተለይ የብልትን ተልትሎ የመስፋት አደጋን በተመለከተ በሶማሊ ወጣቶች እና ወላጆች ዘንድ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ነበር። ምንም እንኳን በታዳጊነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ሽንት ለመሽናት እንደሚያስቸግር እና በወር አበባቸው ጊዜ ህመም እንዳለው ቢናገሩም አብዛኞቹ ምላሽ ሰጪዎች የሴት ልጅ ግርዛት ህመም እንዳለው እና በግብረስጋ ግንኙነት ጊዜም ህመም እንደሚኖረው ቢስማሙም፣ በጤና ላይ ስላለው ጉዳት ዝርዝር ምላሾችን መስጠት የቻሉት ግን የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ብቻ ነበሩ። የሴት ልጅ ግርዛት አደጋዎችን በእርግጥም በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የሴት ልጅ ግርዛት ምን አይነት ጉዳት እንዳመጣባቸው ሲጠየቁ ምንም አይነት ጉዳት ሪፖርት አላደረጉም። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ21 ዓመቷ ወጣት ለጥያቄው ስትመልስ፣ “ምንም የለም… ለእኛ ጥሩ ነበር።” ብላለች። በተለይ ወጣት ወንዶች አያውቁትም። የሃርሸን ከተማ የ26 አመት ወጣት በሰርግ ምሽት የግብረስጋ ግንኙነት ከመፈፀሙ በፊት የሴት ልጆችን የተሰፋ ብልትን የመክፈት ሒደት በተመለከተ ጥያቄ ሲቀርብላት ተግባሩ ጥሩ እንደሆነ ተናግራለች። ወዲያውኑ የግብረ ሥጋ ግንኙነት

ሲደረግበት ልጃገረዶችን የሚያጋጥማቸው ከባድ ህመም ቢኖርም አካሉ እንደገና ተመልሶ እንዳይገጥም እና የወደፊት ህመምንም እንደሚከላከል ስታስረዳ የሚከተለውን ብላለች፣

> “የወሲብ አካል ከተከፈተ በኋላ ወዲያውኑ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም በልጃገረዶቹ ላይ ያለውን ህመም ሊቀንስ እንደሚችል አስባለሁ።” ።

የዚሁ ወረዳ ነዋሪ የሆነ የ21 ዓመት ወጣት የልጁን በቀዶ ጥገና መወለድ የፈጠረበትን ጭንቀት እና ያም የሆነው ከሚስቱ ግርዛት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ሲጠየቅ እንዲህ ብሏል፣

> ልጄ የተወለደው በቀዶ ሕክምና ነው። ያኔ በጣም አሳሳቢ ጭንቀት ውስጥ ነበርኩ... እህቴ ሰባት ልጆችን ወልዳለች። ለሁሉም ጊዜ ለቀዶ ጥገና ሄዳለች፤ ለቀዶ ጥገና መሄድ የተለመደ ነገር ነው።” ።

በሀርሸንም ሆነ በጎልጃኖ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ፋይዳ የሚሰጠው ሀሳብ ግን የተለያየ ነበር። ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ሃይማኖታዊ ግዴታን ከመከተል እና የሶማሊን ባህል ለማስቀጠል እንደሆነ የተስማሙ ቢሆንም በመካከላቸው የተወሰነ የፆታ ልዩነት ነበር። በመነሻ ጥናት ላይ እንደነበረው፣ ሴቶች እና ልጃገረዶች በማህበረሰቡ ውስጥ ቦታ እንዲኖራቸው፣ ወቀሳ እና እፍረትን ለማስወገድ አስፈላጊነቱ ላይ ትኩረት ሰጥተው ነበር። ከሃርሽን የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ዋና መረጃ ሰጪ ስታብራራ፣ ‘’መገረዝ አለመኖሩ ብዙ ጊዜ አሳፋሪ ነው’’ ስትል፣ በባህላዊው መንገድ የተሰፋች የዚሁ ወረዳ ነዋሪ የሆነች የ18 አመት ወጣት ሴት እናቷ ስታስገርዛት መጀመርያ ቀለል ያለውን ግርዛት ለማስፈፀም አስባ በሌሎች የማህበረሰቡ ሴቶች ከፍተኛ ጫና ደርሶባት እንደነበርና፣ “እናቴ ለእኔ የሱና አይነት ግርዛትን እያሰበች ነበረች። ነገር ግን ሌሎች ተቃወሟት።” በማለት ተናግራለች። በሀርሽን የሚኖሩ መምህር ሲያስረዱ ምንም እንኳ ጥቂት የወንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እውቅና እንደሰጡት ባህልን አጥብቀው የማይከተሉ ልጃገረዶች እና ሴቶች በብዙዎች የተለያዩ ትችቶች ስለሚደርስባቸው ቢሆንም አብዛኞቹ ታዳጊና ወጣት ወንዶች ግን የሴት ልጅ ግርዛት በእርግጥም ብልትን መስፋት ጥቅሙ የማግባት እድላቸውን ለመጨመር ወይም ለትዳር ተስማሚ ተደርጎ መመረጥ እንደሆነ በዋነኛነት ገልፀዋል። የ15 አመት የሀርሼን ወንድ ልጅ፣ “ሴት ልጆች የብልት ትልተላ ካልተፈጸመባቸው አያገቡም” ብሎ ተናግሯል። በተመሳሳይ እድሜ ላይ የሚገኝ የጎልጃኖ ታዳጊም፣ “እንደ ባለጌ ይቆጠራሉ፤ ማንም አያገባቸው።” በማለት ተስማምቷል። የ21 ዓመቷ ነፍሰ ጡር የሃርሺን ወጣት እንደገለፀችው የወደፊት ሴት ልጇ ጋብቻ ዋና ጉዳዩዋ ባይሆንም የልጇን ብልት ለወደፊት ባሏ ማራኪ እንዲሆን ጥረት እንደምታደርግ እንደሚከተለው ገልጻለች፡

> ነፍሰ ጡር ነኝ፤ ሴት ልጅ ከወለድኩ ባህላዊውን ዓይነት 3 ግርዛት (መስፋት) እንድትገረዝ እፈልጋለሁ... ወድጄዋለሁ... ለባሏ ማራኪ ነው። ልብሷ ሲወልቅ ብልቷ አይታይም።

ከአንዲት የጎልጃኖ ነዋሪ ልጃገረድ በቀር የሶማሊ ምላሽ ሰጪዎች በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ማን ውሳኔ እንደሚሰጥ ስምምነታቸውን ሲገልጹ፣ እናቶች እና እናቶች ብቻ ናቸው በማለት ተናግረዋል። የሃርሽን ከተማ ነዋሪ የሆነች እናት ባለቤቷ የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ የሰጠውን አስተያየት ችላ በማለቷ ተናድዶ እንደነበር እንደሚከተለው ገልፃለች፤

> በሶማሊ ባህል የሴቶችን ግርዛት በተመለከተ ሴቶች ውሳኔ ሰጪዎች ናቸው፤ እናም ለባሎች መንገር ምንም ፋይዳ አይኖረውም... ባሎች ልጃገረዶች እንዲገረዙ ባይፈቅዱም እናቶች እንዲገረዙ ያስገድዷቸዋል... ሁለቱን ሴት ልጆቼን አስገረዝኳለሁ። ባለቤቴ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ አስገረዝኩ፤ እሱ እዚህ ቢሆን ኖሮ ሂደቱን እንዳከናውን አይፈቅድም ነበር... በእውነት ተናደደብኝ!

ሌላዋ የዚሁ ወረዳ ነዋሪ እናት አያቶችም ያላቸው ግብአት ወይም ተሰሚነት ውስን ነው ሲሉ እንደሚከተለው አክለዋል፣

> የልጅ ልጆቼ አይነት 3 ግርዛት እንዲደረግላቸው (እንዲሰፉ) እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን እናቶቻቸው አይፈልጉም፤ እንድናስገርዝ አይፈቅዱም፤ ስለ የልጅ ልጆች ግርዛት ከሴት ልጆቻችን ጋር መወያየት አልቻልንም፤ በመረጡት ዓይነት ይገርዟቸዋል።

ምላሽ ሰጪዎች አክለውም በፋፋን የሚታየው ለውጥ አዝጋሚ የሆነበት ምክንያት ብዙ እናቶች የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ የብልት ጫፍ መቁረጥን ብቻ ሳይሆን የብልት መስፋትን በመፈለጋቸው ነው ብለዋል። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ17 ዓመቷ ልጅ ይህንን ብላለች፣

> እናቶች እንደሚያምኑት ሴት ልጅ ካልተሰፋች ተጋላጭ ናት፣ የተሰፋችው ደግሞ የተጠበቀች ነች፤ ለሴቶች ጥሩ ነው፤ የተሰፋች ልጅ በደንብ ትሸፋፈናለች ፀጉሯን በሻሽ እንዳስረች ሴት።

የዚሁ ወረዳ ነዋሪ የሆነ የ19 አመት ወጣት አክሎ እርሱና ጓደኞቹ ለሚስትነት የተሰፉ ሴቶችን ቢመርጡም ውሳኔው እና የማስገረዝ (የማሰፋት) ሃላፊነቱ ግን እናቶች ልማዳዊ ድርጊቱን ለማስቀጠል ባላቸው ቁርጠኝነት ላይ የተመሰረተ ነው ብሏል።

> ወንዶች ሴት ልጅ ክፍት እንድትሆን አይፈልጉም፣ ነገር ግን ይህን የሚደግፉ ቁጥር አንድ እናቶች ናቸው። .. ባህሉን ማስቀጠል ስለሚፈልጉ … የሴት ልጅ ጉዳይ የእናቶች ሃላፊነት ነው።

በአይነታዊ ጥናት ላይ የተካተቱት ተሳታፊዎች እና መልእክቶች በቅርብ ጊዜ በሴት ልጅ ግርዛት አይነት ላይ ምን አይነት ለውጥ እንዳመጣ ተጠይቀው በዋነኛነት የጠቆሙት ሃይማኖታዊ ያልሆኑ እና የህክምና ህጎችን ቢሆንም፣ ጥቂት የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የብልት መስፋትን አደገኛ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ያደረጉትን ጥረት ጠቅሰዋል። የጎልጃኖ ከተማ ነዋሪ የሆነች የ17 ዓመቷ ታዳጊ እንደገለፀችው፣ እስር ቤት መግባትን ስለሚፈሩ ባህላዊ ገራዦች መስፋት አቁመዋል፣

> ሴት ልጅን መስፋት የሚፈልግ ገራዥ የለም። ያን ሲያደርጉ ከተገኙ ወደ ወረዳው ከተማ ተወስደው እዚያው ይታሰራሉ። ገራዦች ቅጣቱን ስለሚፈሩ ስፌት ከመስፋት ተቆጥበዋል።

የሀርሸን ወረዳ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደተናገረቸው የእስር ፍራቻው እውነት ነው፣ "ለ 6 ወር እንርትታሰርና ከዚያም በኋላ ከከተማው እንድትለቅ ይደረጋል።" ብላለች። አንድ የዚያው ወረዳ ነዋሪ እናት ደግሞ የጤና ባለሙያዎች በሴት ልጅ ግርዛት እንዲገቡ ምክንያት የሆነው ልጃገረዶች እንደተሰፉ እና እንዳልተሰፉ እንዲያጣሩ ነው በማለት ስታስረዳ፣

> የጤና ባለሙያዎች ሴት ልጆች ሲገረዙ በቅርብ ክትትል ስለሚያደርጉ... ምንም አይነት የመስፋት ግርዛት የለም።

የሀይማኖት መሪዎች በተለይ የወንዶችን እምነቶችን እና ልምዶችን በመለወጥ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፤ ምክንያቱም "አብዛኛውን ጊዜ ብዙ ሴቶች ወደ መስጊድ ስለማይሄዱ ነው።" በማለት የ 18 አመቷ የሀርሸን ነዋሪ ገልፃለች። የእምነት አባቶች የሴት ልጅ ብልት መተልተልና መስፋትን እንጂ ግርዛት ሙሉ በሙሉ ማቆምን እንደማይሰብኩ ቢታወቅም አንድ የጎሳ መሪ እንዲህ በማለት አስረድተዋል።

> ከእስልምና ፍርድ ቤት ተቋማት ብዙ ሃይማኖታዊ አባቶች ከክልል እዚህ መጥተው አስተምረውናል፤ ሃይማኖታችን የሴቶችን አካል መቁረጥ አይፈቅድም።

የዚሁ ወረዳ የሀይማኖት አባት የሚከተለውን ተናግረዋል።፣

> የሃይማኖት አባቶቻችን የሴት ልጅ ግርዛት ከባድ ስህተት መሆኑን አስጠንቅቀዋል። በሴት ልጆቻቸው ላይ ግርዛትን የፈፀሙ ሰዎች ይቅርታ እንዲጠይቁ አሳስበዋል። ካላደረጉት "ለምን በሴት ልጅ ላይ ጉዳት እንዳደረሱ በፍርድ ቀን ይጠየቃሉ።

## የህጻናት ጋብቻ

### አፋር


የፕሮግራሙ አጋማሽ ጊዜ ጥናት ሲደረግ በአፋር ናሙና ውስጥ ያለው ታዳጊ አማካኝ እድሜ 16 ዓመት ስለነበር ትዳር የመሰረቱት ጥቂት ነበሩ። ከታዳጊ ልጃገረዶቹ መካከል ያገቡ 5% ብቻ ነበሩ፤ ከወንዶቹ መካከል እንዳገቡ የተናገሩ አልነበሩም። ከ39ኙ ልጃገረዶች መካከል ግማሾቹ ያገቡት 18 ዓመት ሳይሞላቸው ነበር። በልጃገረዶች ላይ የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው ልጃገረዶች በአማካይ በ17.3 ዓመታት ያገቡ ሲሆን የተዳሩትም በአማካይ እነሱን 4.6 ዓመት ለሚበልጡ ወንዶች ነበር። በተጨማሪም እነዚህ ጋብቻዎች ከሞላ ጎደል (95%) የሚወሰኑት በልጃገረዶቹ ወላጆች እንጂ በልጃገረዶቹ እንዳልሆነ ተረጋግጧል። በወላጆች ላይ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት ከሁሉም አባወራዎች መካከል ካሉት 1,703 ጋብቻዎች መካከል ሁለቱ ብቻ በወረዳው በህጋዊ መንገድ የተመዘገቡ ናቸው። በአስፈላጊ ሁኔታ, ወደፊት የሚከሰተውን የህጻናት ጋብቻ ለመከላከል በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበው ከ 5% ያነሱ ልጆች ውልደት ብቻ ነበር ።

ጥናቱ እንደሚያመለክተው ሁሉም የአፋር ምላሽ ሰጪዎች (88%) የአዋቂዎች ጋብቻን እንደሚመርጡ፣ ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ከ18 ዓመታቸው በፊት እንደሚጋቡ (60%) እና የህጻናት ጋብቻ ህገ-ወጥ መሆኑን የሚገነዘቡት ውስን ቢሆንም 44% (ምስል 46 ይመልከቱ)። ታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ይልቅ የጎልማሳ ጋብቻን ይመርጣሉ (99% ለ 87%)። ታዳጊዎቹ የጎልማሳ ጋብቻን የሚመርጡበት ምክንያት ላይም የፆታ ልዩነቶች ነበር። ብዙውን ጊዜ የልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ምርጫዎች በአካላዊ ብስለት (37%) እና ትምህርት ማጠናቀቅ (28%) ምክንያት ነው። በአብዛኛው



የ17 አመት ልጃገረድ በሶማሊ፣ ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

ምስል 46: የአፋር ወጣቶች ምርጫ፣ እምነት እና ስለ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ያላቸው እውቀት





ታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ (49%) እና የስሜታዊ ብስለት (23%) ምክንያት እንደሆነ ሪፖርት አድርገዋል፡፡ የአዋቂዎች ጋብቻ የመረጡበት ምክንያት ላይም የዞን ልዩነቶች ነበሩ፡፡ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ያሉት በሃሪ ረሱ [ዞን 5] ካሉት ሲነፃፀሩ (92% ለ 86%) የበለጠ የአዋቅዎችን ጋብቻ መርጠዋል፡፡ ስለ የህጻናት ጋብቻ የተለመደ መሆን ከፍተኛ የጾታ እና የአከባቢ ልዩነቶች ነበሩ፡፡ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ከ18 ዓመታቸው በፊት ማግባት ከታዳጊና እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ይልቅ (64 ለ 37 በመቶ) የበለጠ የተለመደ እንደሆነ አምነዋል፡፡ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] (65%) ከሃሪ ረሱ [ዞን 5] (ከ 52%) ሲነፃፀር የህጻናት ጋብቻ በጣም የተለመደ እንደሆነ አምነዋል፡፡ ምንም እንኳን በየአካባቢው ስለ የህጻናት ጋብቻ ህጎች ግንዛቤ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ከታዳጊ እና ወጣት ወንዶች የበለጠ ያውቃሉ (46% ለ 33%)፡፡

በአፋር የጥናት ቦታዎች ያሉ ወላጆችወላጆች ስለ ህጻናትህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና እውቀት ከታዳጊዎቹ ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ ሁሉም (84%) ማለት ይቻላል በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ከ18 ዓመታቸው በፊት እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ሴት ወላጆች (86%) ከወንዶች አስተዳዳሪዎች (66%) እና በሃሪ ረሱ (ዞን 5) (90%) ያሉ የወላጆች በአውሲ ረሱ [ዞን 1] (74%) ካሉት የበለጠ ተስማምተዋል (ምስል 47ን ይመልከቱ)፡፡ በግምት ግማሽ በላይ የሚሆኑ ወላጆች - ያለ ጾታ እና ቦታ ልዩነት - የህጻናት ጋብቻ ህጎች እንዳሉ ያውቃሉ፡፡

በተለይ በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ብዙ ልጃገረዶች ለተጨማሪ አመታት ትምህርት ቤት በሚማሩበት እና የልደት ምዝገባ መዘግብት በብዛት በሚታይበት የህጻናት ጋብቻ እየቀነሰ መምጣቱን በርካታ የአይነታዊ ጥናት ተሳታፊዎች ተናግረዋል፡፡ የአውሲ ረሱ ነዋሪ የሆነች የ18 ዓመቷ ወጣት፣ ‘አሁን የህጻናት ጋብቻ የለም’ ስትል የ12 ዓመቷ የሀሪ ረሱ [ዞን 5] ነዋሪ ደግሞ በጣም ርቀው በሚገኙ ማህበረሰቦችም ቢሆን መዘግየቱ የተለመደ ሆኗል፡፡ ሴት ልጆች በህጋዊ መንገድ አዋቂ እስኪሆኑ ድረስ ጋብቻውን ያዘገዩታል: “ህጻናት ጋብቻ በህግ የተከለከለ ነው… ልጅቷ 18 ዓመት እስኪሞላት ድረስ ጋብቻቸውን ያዘገዩታል” በማለት ገልፃለች፡፡ የአውሲ ረሱ [ዞን 1] የ18 ዓመት ወጣት እንዳብራራው ልጃገረዶች በልጅነታቸው ቢታጨም እንኳን የሚጋቡበት ዕድሜ ግን ቀስ በቀስ እየጨመረ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

> ቀደም ባሉት ጊዜያት በአካባቢያችን ያሉ ልጃገረዶች በለጋ እድሜያቸው ልክ በ 13, 14 ወይም 15 አመት ያገቡ ነበር… አሁን ግን በመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት

ምስል 47: የአፋር አሳዳጊዎች ስለ ህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና እውቀት



## ሣጥን6: በአፋር ክልል የህጻናት ጋብቻ በጊዜ ሂደት

በመነሻ ጥናት፣ ከ1% ያነሱ የአፋር ሴት ልጆች አግብተዋል (ይህ በጣም ዝቅተኛ ቁጥር የሚጠበቅ ነበር፣ በዚያን ጊዜ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙት አማካኝ እድሜ 13 ዓመት ብቻ ነበር)። በአጋማሽ ጥናት ጊዜ ይህ ወደ 4% ከፍ ብሏል። ታዳጊዎች ለህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና ምርጫዎች በመነሻ እና በአጋማሽ ጥናት መካከል ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ እንዲሁ ተቀይሯል። በአጋማሽ ጥናት ወቅት የነበሩ ታዳጊዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ከ18 ዓመታቸው በፊት ነው ብለው የማመን እድላቸው በመነሻ ጥናት ወቅት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነበር (60% በ 82%)። በግል ጎልማሳ ሲሆኑ ማግባትን ይመርጣሉ(88% ከ 65%)።

ወላጆች ስለ ህጻናት ጋብቻ መስፋፋት ያላቸው እምነት በጊዜ ሂደት አልተለወጠም።

> መሪዎች እና የሸሪዓ ወንዶች ጥረት፣ የሴቶች ጋብቻ ዕድሜ ትንሽ አድጓል፣ እና አሁን እዚህ ያሉ ልጃገረዶች 17 ዓመት ከሞላቸው በኋላ ያገባሉ።

ሌሎች ምላሽ ሰጪዎች፣ በተለይም በሃሪ ረሱ [ዞን 5] የጥናት ቦታዎች የሚገኙት፣ ምንም አይነት ለውጥ እንደሌለ ተናግረዋል። የሃሪ ረሱ ነዋሪ የሆነች የ14 ዓመቷ ታዳጊ፣ በቅርብ ጊዜ አብዛኞቹ ልጃገረዶች በሚያገቡበት ዕድሜ ላይ ለውጦች እንደነበሩ ስትጠየቅ፣ *"ምንም ለውጥ የለም… አንዳንድ ልጃገረዶች ያገቡት 13 ወይም 14 ዓመት ሲሆናቸው ነው። "* ብላለች። የ17 አመት የዚያው ዞን ወጣት በታዳጊዋ ሀሳብ ተስማምቶ እና ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ከማግባታቸው በፊት ከሚያደርጊዙ ይልቅ ቀድመው ቢያገቡ እንደሚመርጡ ተናግሯል፣

> 15 ዓመት ከሞላቸው በኋላ ነው የሚጋቡት… ወደ መጥፎ ነገር ከመግባታቸው በፊት አባቶቻቸው እና እናቶቻቸው ይድሯቸዋል … ሊፀንሱም ይችላሉ።

በእርግጥም አንድ አባት ከአውሲ ረሱ [ዞን 1]፣ ልጃገረዶች የሚጋቡት በእድሜያቸው ሳይሆን በአካል እድገታቸው እንደሆነ፣ የልጃገረዶች ባህሪ እያሽቆለቆለ እና ወላጆች ስለ ሴት ልጆቻቸው ድንግልና ያላቸው ስጋት እያደገ በመምጣቱ የጋብቻ እድሜያቸው በቅርቡ እንደቀነሰ ተናግሯል።

> የልጃገረዶች የጋብቻ እድሜ የሚወሰነው በልጃገረዷ አካላዊ እድገት፣ የወር አበባ መጀመር እና የወላጆች ፍላጎት ነው … በአሁኑ ጊዜ ልጃገረዶች ወደ ግንኙነቶች እና ከጋብቻ በፊት ወደ ወሲብ ይጣደፋሉ፤ ይህም ከጋብቻ በፊት እርግዝና መከሰትን ያስከትላል. ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ የልጃገረዶች ወላጆች ልጃገረዶች 13 እና 14 ዓመት ከሆናቸው በኋላ ሴቶቻቸውን ሳያገቡ ለመተው ይፈራሉ፤ ወላጆች ስማቸው እንዲጠፋ አይፈልጉም።

ልክ እንደ የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች፣ በአፋር ባህላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች ላይ ምን እንደሚያስከትል መላሾች በመካከላቸው ተመሳሳይት ነበር። ልጃገረዶች በእናቶች በኩል ካለው የአጎት ልጅ (አብሱማ) ጋር ይጋባሉ፣ በሙሽራው እና በልጅቷ አባት በወሰኑት ጊዜ፣ ልጅቷ ሰርጓ ሳምንት ወይም ቀናት እስከሚቀረው ድረስ አይነገራትም። የ15 ዓመቷ ልጅ የሀሪ ረሱ [ዞን 5] *"አብሱማዋ ልጅቷን እንድታገባው ሲጠይቅ ወላጆች ሰርጉን ያመቻቻሉ"* ብላለች። ሌላኛዋ መላሽ ከአውሲ ረሱ [ዞን 1] ያገባች የ 21 አመት ሴት እንደገለፀችው፣

> እሱን ስለማግባት የሰማሁት በሠርጉ ቀን ነው። ያዙኝና ነገሩን በዚያው ቀን አሳወቁኝ… ላገባ የወሰነው አባቴ ነው"

ስትል በተመሳሳይ እድሜ ላይ ያለች ልጃገረድ ከ ሃሪ ረሱ [ዞን 5] ደግሞ " የሴቶችን ፈቃድ የመጠየቅ ልምድ የለም።"

አብዛኞቹ ምላሽ ሰጪዎች በተለይ በሃሪ ረሱ [ዞን 5] ውስጥ አብዛኞቹ ጋብቻዎች አሁንም በባህላዊ መንገድ የሚፈፀሙ መሆናቸውን ተናግረዋል። የሀሪ ረሱ አንድ እናት፣ "አብሱማ ከጠየቀ እምቢ ማለት አንችልም። የወንድየው ታላቅ ወንድም አብሱማ ትዳሩን ሊቃወም ይችላል፤ ሴቷ ግን ጋብቻውን የመቃወም መብት የላትም።" በማለት አስረድታለች። ብዙ ትረካዎች እንደሚያስረዱት፣ በሃሪ ረሱም [ዞን 5] ቢሆን የወጣቶች የራሳቸውን አጋር የመምረጥ እድል በየጊዜው እያደገ መጥቷል። በሃሪ ረሱ የምትኖር አንዲት እናት እንዲህ ብላለች፣

> በዚህ ጊዜ ልጃገረዶች ባሎቻቸውን ለመምረጥ የተሻሉ እድሎች አሏቸው።

ከዚያው ዞን የ 22 አመቷ ባለትዳር የሚከተለውን በማለት ተስማምታለች፣

> እንደ ወላጅ ልጆቻችን የፈለግነውን እንዲያገቡ ማስገደድ አንችልም። እኔም ያገባሁት በፍላጎቴ ነው፣ ከወላጆች ምንም ኃይል የለም።

በተመሳሳይ ዞን የሚኖር አንድ አባትም እንደሚከተለው ብሏል፣

> በዚህ ጊዜ ልጃገረዶች ባሎቻቸውን ለመምረጥ የተሻለ እድሎች አሏቸው። እንደ ወላጅ ልጆቻችን እኛ የፈለግነውን እንዲያገቡ ማስገደድ አንችልም። ያገባሁት በፍላጎቴ ነው እንጂ በወላጆች ምንም አይነት ሃይል የለም።

የህጻናት ጋብቻ እና በጋብቻ ላይ የተደረጉ ለውጦችን ያመጡ ተዋናዮችን፣ መልእክቶችን እና ኃይሎችን እንዲገልጹ ሲጠየቁ፣ ብዙ ምላሽ ሰጪዎች በተለይም በአውሲ ረሱ [ዞን 1] መደበኛ ትምህርትን ጠቅሰዋል። ይህም በከፊል ወጣቶች በትምህርት ቤት ከሚማሩት ጋር የተያያዘ ነው። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የምትኖር አንዲት የ18 ዓመቷ ወጣት በሳይንስ ክፍል የህጻናት ጋብቻ ለአካል አደገኛ እንደሆነ እንደተገነዘበች

ገልጻለች፣ “ማህፀናቸው ጠባብ ነው እና ለመውለድ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል።” በተመሳሳይ እድሜ እና ከአንድ ዞን የመጡ ሰዎች በተመሳሳይ መልኩ፣ “በትምህርት ቤት ውስጥ ለወንዶች እና ለሴቶች ልጆች የጋብቻ ሕጋዊ ዕድሜ 18 እንደሆነ ተምሬያለሁ።” ብለዋል። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] የምትኖር ያላገባች የ18 ዓመት ወጣት፣

> የ9ኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ ጀምሮ እንዳገባ ጠየቁኝ፤ ለሦስት ዓመታት ያህል እንዳገባ ሲጠይቁኝ ነበር ነገር ግን አባቴ እንዳገባ አልፈለገም። ተማሪ ስለሆንኩ ትምህርቴን እንደጨረስኩ እንዳገባ እንደሚፈልግ ተናግሯል።

በሃሪ ረሱ [ዞን 5] ልጃገረዶች ገና በታዳጊ ዕድሜያቸው መገባደጃ ላይ መመዝገባቸው ባልተለመደበት አካባቢ አንዲት የ14 ዓመቷ ልጃገረድ እንደተናገረችው ብዙውን ጊዜ ወደ ሳውዲ አረቢያ የቤት ውስጥ ሥራን ለማከናወን ከሥራ ጋር የተያያዘ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ በተመሳሳይ የህጻናት ጋብቻን የመከላከል ሚና እየተጫወተ ነው፣

> የጋብቻ ጥያቄ ነበር፤ ባለፈው አመት ሁለት ግለሰቦች እኔን ለማግባት በተለያየ ጊዜ ጠይቀዋል፤ እናቴ ለትዳር ፍላጎት አልነበራትም። ወደ ሳውዲ አረቢያ ልትልከኝ ስታስብ ትዳር እንደማትፈልግ ነገረቻቸው። እዚህ ከሚኖር አርብቶ አደር ጋር ከመጋባት መሰደድ ይሻላል።

በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ማህበረሰቦች በሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ የሀይማኖት መሪዎች፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በተለያዩ ጊዜያት ሲደረጉ የነበሩ የጋብቻ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች አስፈላጊ እነደሆኑ ምላሽ ሰጪዎች በሰፊው ተናግረዋል። የሀሪ ረሱ [ዞን 5] አንድ አባት ይህን ብለዋል።

> እነዚህ በመንግስት እና በሌሎች እንደ ሀይማኖት መሪዎች ያሉ ትምህርቶች የህዝቡን አስተሳሰብ በመቀየር የሴቶች የጋብቻ እድሜ ወደ 18 እና ከዚያ በላይ እንዲያድግ አድርጓቸዋል።

አሁን ያለቀው በመንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ፓዝፋይንደር የተተገበረው አክት ዊዝ ኸር (Act With Her) የተሰኘው ትግበራ በተለይ ለውጥ እንዳሳየ ተለይቷል። በሀሪ ረሱ [ዞን 5] የሚኖረው የ18 አመት ወጣት እንዲህ ሲል ያስታውሳል፡

> ሉላ የምትባል ሴት እዚሁ ትሰራ የነበረች እና የህጻናት ጋብቻ መፈፀም የሚያስከትለውን ጉዳት ለህብረተሰቡ ስታስተምርና የህጻናት ጋብቻን ለማጥፋት ከዛሬ ሶስት አመት በፊት ስትሰራ ነበር።

ልጃገረዶች ራሳቸው ብዙውን ጊዜ ወላጆቻቸውን ለመናገር ስለሚፈሩ እና የመንግስት ባለስልጣናትም በህብረተሰቡ ውስጥ የራሳቸውን ክብር አደጋ ላይ ሊጥሉ እንደሚችሉ በመፍራት ጣልቃ ከመግባት ስለሚቆጠቡ እንጂ በወላጆች እና ልጃገረዶች የህጻናት ጋብቻን ተግባር በቀጥታ ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ባለስልጣናት ማሳወቅ እንደሚችሉ፣ ወላጆች ህጉን በመጣስ ሊቀጡ እና ሊታሰሩ እንደሚችሉም ግንዛቤው እንዳላቸው በስፋት እየተነገረ ነው። በጥልቅ ቃለ ምልልስ ወቅት ወላጆቻቸውን ለባለሥልጣናት ስለከሰሱ ሁለት ልጃገረዶች ሰምተናል። በአውሲ ረሱ (ዞን 1) የምትገኝ የ15 አመት ልጅ ለአባቷ ብዙ ገንዘብ ከከፈለ ባለፀጋ ጋር ያለፍላጎቷ ልታገባ የነበረች ልጅ አባቷን ከሳ ትዳሯ ተሰርዟል። በተመሳሳይ ዕድሜ ላይ የምትገኝ ከሀሪ ረሱ [ዞን 5] የመጣች ልጅ፣ በወላጅ ፈቃድ ታፍና የተደፈረች፣ ትዳሯ መሰረዙ ብቻ ሳይሆን ወላጆቿ እና የአካባቢው ባለስልጣናት በተግባራቸው ምክንያት እስር ቤት ገብተዋል። አንድ የሃይማኖት መሪ እንዲህ ሲል ገልጿል፤

> በሀይማኖት ልጆች ያለፈቃዳቸው ማጋባት ክልክል ነው... በግዳጅ ጋብቻ ያደረጉ ተከሳሾች ይታሰራሉ። ከየትኛውም አካባቢ እንደዚህ አይነት ግለሰቦችን ፍርድ ቤት እናቀርባለን። በቅርቡ፣ ቤተሰቦች (እናትና አባት) አንዲት የ15 ዓመት ልጅ እንድታገባ አስገደዷት... አሁን እናትና አባቷን ጨምሮ አምስት ግለሰቦች በእስር ላይ ይገኛሉ። የቀበሌ አስተዳዳሪዎችም ስራቸውን ባለመስራታቸው ለእስር ተዳርገዋል።

### ሣጥን7: የህጻናት ጋብቻ በሶማሌ በጊዜ ሂደት

በመነሻ ጥናት ወቅት ፣ ከ1% ያነሱ የሶማሊ ሴት ልጆች አግብተዋል (ይህ በጣም ዝቅተኛ መጠን በወቅቱ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች 13 ዓመት ብቻ ስለነበር የሚጠበቅ ነው)። በአጋማሽ ጥናት ጊዜ ይህ አሃዝ 4% ነበር። በማኅበረሰባቸው ውስጥ ያለ የህጻናት ጋብቻ ምን ያህል የተለመደ እንደሆነ የወጣቶች እምነት በመነሻ እና አጋማሽ መካከል ጨምሯል፣ ይህም ምናልባት አንዳንድ እኩዮቻቸው ማግባት ስለጀመሩ ሊሆን ይችላል። በመነሻ ጥናት ወቅት፣ 56% የሚሆኑ ታዳጊዎች አብዛኞቹ ልጃገረዶች በልጅነታቸው እንደሚያገቡ ያምኑ ነበር፤ በአጋማሽ ጥናት ጊዜ ይህ ወደ 76% ከፍ ብሏል። ወላጆች ስለ ህጻናት ጋብቻ መስፋፋት ያላቸው እምነት በመነሻ (79%) እና አጋማሽ (83%) መካከል ጨምሯል። የህጻናት ጋብቻ ደንብ ነው የሚል እምነት እያሳደገ ቢሄድም፤ ታዳጊዎች ለጉልምስና ጋብቻ ያላቸው የግል ምርጫ በመነሻ (53%) እና አጋማሽ ጥናት (84%) መካከል ጨምሪ ይታያል።

## ሶማሊ

በሶማሊው ናሙና ውስጥ ያለው አማካይ የታዳጊዎቹ እድሜ 15.7 አመት ብቻ ስለነበር የፕሮግራሙ አጋማሽ ጥናት ሲደረግ የህጻናት ጋብቻ የፈፀሙ ልጃገረዶች ጥቂት ነበሩ። ያገቡ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ብዛት 5% ነበር፤ ከወጣት ወንዶች መካከል 1% ያህሉ ብቻ ነበሩ ያገቡት። ከተጋቡ 34 ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች መካከል ሶስት አራተኛው የተጋቡት 18 ዓመት ሳይሞላቸው ነበር። ታዳጊዎች እና ወጣቶች ላይ በተደረገው ጥናት መሠረት ልጃገረዶቹ በአማካይ በ16 ዓመት እድሜያቸው ያገቡ ሲሆን ያገቧቸው ወጣት ወንዶች ደግሞ በአማካይ 2.2 ዓመት ይበልጧቸዋል። እነዚህ ሁሉ ጋብቻዎች (94%) ደግሞ ከወላጆቻቸው ይልቅ በራሳቸው ወጣት የትዳር አጋሮች ስምምነት የተወሰኑ ነበሩ። በወላጆች ላይ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት በሁሉም አባወራዎች መካከል ካሉት 1,682 ጋብቻዎች መካከል በወረዳው የተመዘገቡት ጋብቻዎች አምስቱ ብቻ ነበሩ። በተጨማሪም የወደፊት የሴት ልጆችን የህጻናት ጋብቻ ለመከላከል ጠቃሚ የሆነው የልደት መረጃ ከ0.5% ያነሰ ውልደት ብቻ ነበር በሕጋዊነት የተመዘገበው።

ጥናቱ እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ የሶማሊ (84%) ወጣቶች፣ ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ (76%)የማህበረሰቡ ልጃገረዶች ከ18 ዓመታቸው በፊት ቢያገቡም፣ የጎልማሳዎች ጋብቻን ይመርጣሉ (ምስል 48 ይመልከቱ)። ምንም እንኳን ዋና ምክንያቶቻቸው ቢለያዩም፣ የወጣቶች የጎልማሳነት እድሜ ጋብቻ ምርጫዎች በሁሉም ጾታዎች ተመሳሳይ ነበሩ። ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች የጎልማሳ እድሜ ጋብቻን የመረጡት በአእምሮ ስለሚበስሉ (22%)፣ በገንዘብ ራሳቸውን ስለሚችሉ (22%)፣ በአካል የጠነከሩ ስለሚሆኑ (13%) እና ትምህርታቸውን ስለሚያጠናቅቁ (9%) ነበር። ታዳጊና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ደግሞ በገንዘብ ረገድ ራሳቸውን ስለሚችሉ (45%)፣ በአእምሮ የበሰሉ ስለሚሆኑ (15%) እና በአካል የበሰሉ (11%) ስለሚሆኑ ነበር። ስለ የህጻናት ጋብቻ መስፋፋት ያለው እምነትም በጾታ ይለያያል።ታዳጊና እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ከልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች የበለጠ (83% ለ74%) በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ከ18 ዓመታቸው በፊት እንደሆነ አምነዋል። ምንም እንኳን ታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች (20%) ከልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች (10%) የበለጠ ቢያውቁም፣ ስለ የህጻናት ጋብቻ ህጎች መኖር የወጣቶች ግንዛቤ ዝቅተኛ ነበር።

በሶማሊ ጥናት ቦታዎች የሚገኙ ወላጆች ስለ የህጻናት ጋብቻ መስፋፋት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው እምነት የወጣቶችን ያንፀባርቃል። 83 በመቶዎቹ በቦታ ወይም በሴቶች እና በወንዶች መካከል ምንም ልዩነት ሳይኖራቸው፣ አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት 18 ዓመት ሳይሞላቸው ነው ብለው ያምናሉ (ምስል 49 ይመልከቱ)። ወላጆች ከወጣቶች የበለጠ የህጻናት ጋብቻ ህጎች እንዳሉ ያውቃሉ፤ አንድ አራተኛ የሚሆኑት ወላጆች ህጉን እንደሚያውቁ ተናግረዋል ።


ከጥቂቶች በስተቀር ሁሉም ከበርካታ ማእከላዊ ቀበሌዎች የተውጣጡ በፋፋን የሚገኙ የአይነታዊ ጥናት ተሳታፊዎች ህጻናት ጋብቻ የተለመደና የበለጠ እየጨመረ እንደሄደ ተስማምተዋል። አንድ የጎሳ መሪ እንደሚከተለው አብራርቷል።

> "አብዛኞቹ ልጃገረዶች 18 ዓመት ሳይሞላቸው ያገቡ ናቸው። 18 ዓመት የሞላው ሰው በጣም ያረጀ እና ታጋሽ እንደሆነ ይቆጠራል። 70% የሚሆኑት ጋብቻዎች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ግለሰቦችን እንደሚያጠቃልል እገምታለሁ።


ከሁሉም በላይ ደግሞ አብዛኞቹ ወጣቶች እና ጎልማሶች ዕድሜያቸው 15 ዓመት ሲሞላ አብዛኞቹ ልጃገረዶች የሚያገቡበት መሆኑን ቢስማሙም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ (በተለይም በሃርሸን) የጋብቻ ዕድሜ እየቀነሰ መምጣቱን ተናግረዋል። በ15 ዓመቷ ያገባች የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ21 ዓመቷ ወጣት፣ "ሴቶች የሚጋቡት በ14 እና በ15 ዓመታቸው ነው" ስትል የሀርሼን የቀበሌ ሰብሳቢ ደግሞ፣ "በ10 ፣ 12 እና 13 ዓመት ዕድሜ ላይ ያሉ ያገቡ ልጃገረዶች አይቻለሁ።" በማለት አስተያየቷን ሰጥታለች።

ምንም እንኳን በፋፋን ያሉ ሴቶች ልጆች ከወንዶች ይልቅ በየህጻናት ጋብቻ የመጋለጥ እድላቸው ከፍ ያለ ቢሆንም፣ በሱማሌ ያሉ ወጣት ጥንዶች አብዛኛውን ጊዜ የዕድሜ

ምስል 48: የሶማሊ ወጣቶች ስለ የህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና እውቀት



ምስል 49: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለ የህጻናት ጋብቻ ያላቸው እምነት እና እውቀት




ጓደኞሞች በመሆናቸው፣ ታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች በልጅነታቸው ጋብቻ መፈጸማቸው የተለመደ ነው። የ2 አመት መንታ ልጆች አባት የሆነ የ16 አመት የሀርሼን ታዳጊ በ13 አመቱ የ12 አመት ሴት ልጅ ማግባቱን ዘግቧል። ስለ ጋብቻ እድሜው ትንሽነት ሲጠየቅ፣ "አዎ በጊዜው ትንሽ ነበርኩ።" በማለት መለስ ሰጥቷል። ሚስህ በጣም ልጅ ነበረች ወይ ተብሎ ሲጠየቅ፣ "አይ ተዘጋጅታለች" ሲል መለሷል። አንድ እደሜው 20 አመት የሆነ ባለትዳር በ11 ዓመቱ ያገባው ጋብቻ የተሻለ አማራጭ መሆኑን እንዴት እንዳወቀ ሲጠየቅ የሚከተለውን ብሏል።፤

> ጋብቻ ጥሩ ነገር እንደሆነ እናውቃለን። ሁሉም ሰው ያውቃል። ሰዎች ሲጋቡ እናያለን እናም ከዚህ በፊት ሰርጋቸው ላይም እንገኝ ነበር።

ትምህርት ያልገቡ በታዳጊ ዕድሜ ላይ በሚገኙ ወጣቶች መካከል መጋባት የተለመደ ቢሆንም በፋፋን የተማሪዎች ማግባት የተለመደ ነው፤ አብዛኞቹ ወጣቶች በተለይም ሴት ልጆች ከጋብቻ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት አይመለሱም።

ያለ ምንም ልዩነት፣ በሃርሸንም ሆነ በጎልጃኖ ያሉ ምላሽ ሰጪዎች የህጻናት ጋብቻ መከሰት እየጨመረ መምጣቱ እና ወጣቶች የሚጋቡበት ዕድሜ ማሽቆልቆሉ በታዳጊ ዕድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች የጋብቻ ፍላጎት ውጤት እንደሆነ ይስማማሉ። አንዳንዶች ትምህርት ቤቱን እና ታዳጊዎቹን ለእርስ በርስ ግንኙነት መጨመሩ ተጠያቂ አድርገዋል። አንዳንዶች ተንቀሳቃሽ ስልኮችን መጠቀም ወጣቶች ያለወላጅ እውቅና እንዲግባቡ ያስችላቸዋል ሲሉ ተጠያቂ አድርገዋል። አንዳንዶች ከፈተና መውደቅን ተጠያቂ አድርገዋል፣ ምክንያቱም በትምህርት መቀጠል የማይችሉት ወጣቶች የጎልማሳ ደረጃን የሚያገኙበት አንድ መንገድ ጋብቻ ብቻ ነው። ጥቂቶቹ በሴት ልጅ ግርዛት አይነት ላይ የተደረጉትን ለውጦችም ተወቃሽ አድርገዋል፤ ምክንያቱም ያልተገረዙ ልጃገረዶች ለወሲብ የበለጠ ፍላጎት አላቸው ብለዋል። ይሁን እንጂ ሁሉም ተስማምተው መቼ እና ማን ማግባት እንዳለበት ምርጫው የራሳቸው የወጣቶቹ ነው ብለዋል። የሃርሼን አንድ የሃይማኖት መሪ እንዳሉት፣

> እርስ በርሳቸው ይመራረጣሉ። ቀደም ሲል ወላጆች የበለጠ ተጽእኖ ነበራቸው እና ልጅቷን ማን እንደሚያገባ ይወስኑ ነበር። በአሁኑ ጊዜ እንደ ሞባይል ያሉ ቴክኖሎጂዎች እና ቀላል ጉዞዎች ለወላጆች ለሴት ልጃቸው ባል መምረጥ እምብዛም ነው።

በ 15 ዓመቷ ያገባች የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ18 ዓመቷ ወጣት እሷና ባለትዳር ጓደኞቿ ወደ ትዳር ስትገቡ ጫና ደርሶባችኋል ወይ ስትባል፣ "ቤተሰቤ ስለ ጉዳዩ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም፤ እኔ ራሴ ነኝ የወሰንኩት።" ብላለች ።

ምንም እንኳን ብዙ ምላሽ ሰጪዎች አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች ከጋብቻ በፊት የፆታ/ወሲባዊ ግንኙነትን ስለሚያስቀር የህጻናት ጋብቻን እንደሚደግፉ ቢናገሩም አብዛኞቹ ወላጆች (የልጃገረዶችም ሆኑ የታዳጊ ወንዶች) በአጠቃላይ ድርጊቱን እንደማይደግፉ ይስማማሉ። ይህ ለወንዱ ወላጆች ስለ ልጃቸው ጋብቻ ከተፈፀመ በኋላ ቢነገራቸውም የሙሽራዋን ዋጋ እንዲያቀርቡ ስለሚጠበቅባቸው ነው፤ ምክንያቱም የወንዶች ወላጆች ብዙውን ጊዜ ወጣት ጥንዶችን እና ልጆቻቸውን ለዓመታት ይደግፋሉ። በ15 አመቱ ያገባ የ20 አመት የሀርሼን ወጣት እንዲህ ሲል ያስታውሳል፤

> ስለማግባት ከማንም ጋር አልተማከርኩም። ይህን ባደርግ ቤተሰቦቼ እምቢ ይሉ ነበር። ባህሉ በሌሊት ወደ ቤቷ ሄደን ማንም ሳያውቅ እንወስዳታለን። ቤተሰብህን ሳታሳውቅ ወደ ቤትህ ታመጣታለህ…ይህን በሰማ ጊዜ አባቴ ሽማግሌዎችን ወደ ቤተሰቧ ላከ እና ለጋብቻ ጠየቃት።

የዚሁ ወረዳ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያም አስተያየታቸውን እንደሚከተለው ሰጥተዋል፤

> ከጋብቻ በኋላ ሚስቱ 3፣ 4 ወይም 5 ልጆችን እስክትወልድ ድረስ ከእርሱ [ሙሽራው] ምንም ነገር አይጠበቅበትም፣ ቤት መሥራትም ሆነ መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት አይጠበቅበትም። ወላጆቹ ያስገቡትን ሰው የመንከባከብ ሃላፊነት አለባቸው። ልጃገረዶች ሴት ልጆችን የህጻናት ጋብቻ እንዲያቆሙ ልትመክር ትችላለህ ነገር ግን ወጣት ወንዶችን ማስቆም ከባድ ነው። እሱ ቤተሰቡን ማሟላት ስለማይጠበቅበት ቀደም ብሎ ያገባል።



የ16 አመት ሴት ልጅ ውሃ ስትቀዳ፣ሶማሊ፣ ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

በሌላ በኩል ለልጃገረዶች ወላጅ የህጻናት ጋብቻን አለመቀበል ብዙውን ጊዜ ወላጆች ስለ የህጻናት ጋብቻ እና በታዳጊ ዕድሜ ላይ ያሉ እርግዝና አደጋዎችን እና እንዲሁም ወላጆች ለአማቶች ልጃገረዶችን ለጉልበት ብዝበዛን ለመስጠት ፈቃደኛ ካለመሆናቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከሃርሸን የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ዋና መረጃ ሰጪ ሴት እንደገለፀችው

> ወላጆች ልጃቸው ገና በለጋ እድሜዋ ካረገዘች ገና በእድሜ ስላለበሰለች መውለድ እንደማትችል ያውቃሉ፡፡

20 አመት የሞላት - በ15 ዓመቷ ያገባቸው የሃርሸን ተወላጅ የሆነች አሮጊት እናቷ እነዚህን ክርክሮች ለመጠቀም ብትሞክርም ሀሳቧን መቀየር እንዳልቻለች ታስታውሳለች:

> ወላጆቼ በደንብ ሳድግ ማግባት ስለምችል ቀደም ብዬ ማግባት እንደሌለብኝ ነግረውኛል፡፡ … እኔ ለወላጆቼ ጋብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚፈጸም ነገርኳቸው፡፡ ጋብቻ የሚወሰነው በእግዚአብሔር ነው፤ ይህን ነገርኳቸው፡፡

አንዳንድ የጥናት ተሳታፊዎችም የአየር ንብረት ለውጥ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የህጻናት ጋብቻን ዘይቤ እንደቀየረው ተናግረዋል፡፡ በድርቁ ወቅት ሁሉም ማለት ይቻላል ጋብቻዎች - የታዳጊም ሆነ አዋቂ - ለሌላ ጊዜ ይተላለፋሉ፤ ምክንያቱም ቤተሰቦች የድግሱን ወጪ መሸፈን አይችሉም፡፡. የሃርሼን አንድ የጎሳ መሪ እንደገለፀው

> ባለፉት ሁለት ዓመታት ድርቅ በተከሰተ ቁጥር የጋብቻ መጠኑ እየቀነሰ የሚሄደው ሰዎች ሀብት ስለሌላቸው ነው፡፡

አሁን ግን ድርቁ ካበቃ በኋላ የህጻናት ጋብቻ ላይ ከፍተኛ ጭማሪ ታይቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በፍላጎት ብቻ ሳይሆን በድርቁ ምክንያት የትምህርት ውጤታቸው የተበላሸባቸው ታዳጊዎች በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት ትዳር በመመሥረታቸው ነው፡፡ የ17 አመቷ የሀርሼን ነዋሪ የሆነች ትዳር መስርታ “ባለፈው አመት ድርቁ አብቅቶ የዝናብ ወቅት ሲጀምር ነው ያገባሁት” ስትል ገልጻለች፡፡ ከዚያው ወረዳ ሌላ ያላገባች ልጃገረድ ጓደኞቿ ለምን ባለፈው ዓመት እንዳገቡ ስጥጠየቅ እንዲህ ስትል መልሳለች፡ “ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ሁላችንም በትምህርት ወድቀናል ቀጣይ ክፍሎችንም መድገም በመፍራት ማግባት ይመርጣሉ፡፡ ሌላ አማራጭ የላቸውም፡፡”

## የልጃገረዶችንና የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም ማጎልበት

### አፋር


በአፋር የጥናት ቦታዎች ውስጥ ያሉ ወጣቶች (1%) ባለፈው አመት በእጃቸው ገንዘብ የማግኘት ዕድላቸው ከፍተኛ ነበር። አንዳንዶች ቁጠባዎች የማግኘት ዕድላቸው ከፍተኛ ነበር። ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች (4%) የበለጠ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች (14%) ቁጠባ እንዳላቸው ተናግረዋል። በመካከላቸው በቦታ ምክንያት ልዩነቶች አልነበሩም።

ይህ የአጋማሽ ዳሰሳ ጥናት የአፋር ልጃገረዶችን እና የወንዶችን ማህበራዊ ብቃትን ለማጤን የተነደፉ የተለያዩ ጥያቄዎችን አካትቷል። በሁሉም አመላካቾች፣ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ከወንዶች እና ወጣት ወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ አነስተኛ ተጠቃሚ ነበሩ። ለምሳሌ ጓደኛን ወይም ጎረቤትን አዘውትረው የመጎብኘት ዕድላቸው አናሳ (53% ለ 70%) እና በመደበኛነት መስገድ የመሄድ እድላቸው አነስተኛ (39% ለ 88%) ነበር (ምስል 50 ይመልከቱ)። ያላቸውን አስተያየት ከመግለጽ አንጻር ለእድሜ አቻዎች (69% ለ 76%) ለአዋቂዎች (26% ለ 37%) እና አርአያ ከማግኘት አንፃር (49% ለ 57%) ይለያዩ ነበር።


ምንም እንኳን የአፋር ወጣቶች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልበት ፍትሃዊ እምነቶች ቢናገሩም ስለሴቶች ማህበራዊ ተጠቃሚነት ያላቸውን እምነት በተመለከተ ግን ተመሳሳይ ነገር ሊገልፁ አልቻሉም። ሴቶች ከወንዶች እኩል የመሥራት እድል ሊኖራቸው ይገባል (99%) እና ሴቶች ለወደፊት ቁጠባ (98%) እንዲኖራቸው - ሁሉም ወጣት ያለ ጾታ እና ቦታ ልዩነት ማለት ይቻላል - ተስማምተዋል (ምስል 51 ተመልከቱ)። ነገር ግን የበለጠ ወግ አጥባቂ አመለካከቶችን ተንጸባርቀዋል - በማስረጃ 99% የሚሆኑት ቤተሰቦች ከወንዶች ይልቅ ሴት ልጆችን መቆጣጠር እንዳለባቸው ተስማምተዋል፤ 89% ደግሞ ሚስት ባሏን በሁሉም ነገር መታዘዝ እንዳለባት ተስማምተዋል። አብዛኞቹ (72%) “በፖለቲካ ወይም በአመራር ቦታ ላይ የሚሳተፉ ሴቶች ጥሩ ሚስት ወይም እናት ሊሆኑ አይችሉም” በማለት ተስማምተዋል።

በአፋር የጥናት ቦታዎች የሚገኙ ወላጆች በታዳጊ ዕድሜ ላይ ከሚገኙት ልጆቻቸው ይልቅ ባለፈው ዓመት ገንዘብን የመቆጣጠር እና የቁጠባ እድላቸው ሰፊ ነበር። ይህ ግን አሁንም በአንጻራዊ ሁኔታ ያልተለመደ ነበር። ወንዶች ከሴቶች

ምስል 50: ለአፋር ወጣቶች የማህበራዊ አቅም መጎልበት አመላካቾች




ምስል 51: የአፋር ወጣቶች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም መጎልበት ያላቸው እምነት




ይልቅ ገንዘብን የመቆጣጠር ዕድላቸው ከፍተኛ ነው (32% ለ 20%) (ስእል 52 ይመልከቱ)። አብዛኛዎቹ ወንዶች እና ሴቶች እንደሚናገሩት በእነሱ ቁጥጥር ስር ያለ ገንዘብ የሚገኘው ከብት ወይም ሰብል በመሸጥ ነው። ሴቶች ከወንዶች የበለጠ የመቆጠብ ዕድል ነበራቸው (21 በመቶ ለ 9 በመቶ)። ቁጠባ ካላቸው ሴቶች መካከል ወደ ሁለት ሦስተኛ የሚጠጉ (63%) በባንክ መቆጠባቸውን ተናግረዋል። ምንም እንኳን ከሞላ ጎደል ሁሉም ሴት እና ወንድ የወላጆች፣ በገቢያቸው፣ በትዳር ጓደኛቸው ገቢ እና በቤት ንብረታቸው ሽያጭ ላይ የእነርሱ የጋራ ውሳኔ እንዳለበት ቢናገሩም፣ የአፋር ወንዶች በሶስቱም አመላካቾች ከሴቶች ብልጫ ነበራቸው። ለምሳሌ 93% የሚሆኑት ሴቶች በራሳቸው የሚቆጣጠሩት ገቢ እንዳላቸው ሪፖርት ሲያደርጉ የወንዶች 99% ነበር። በተመሳሳይ 93% የሚሆኑ ሴት የወላጆች የቤት ውስጥ ንብረት ሽያጭ ላይ የእነርሱ ውሳኔ ሃሳብ እንዳለበት ሲገልጹ የወንዶች 98% ነበር (ምስል 53 ይመልከቱ)።

የእንስሳት ሀብት ባለቤትነትን በተመለከተ ከተናገሩት የአፋር ወላጆች መካከል አንድ ሶስተኛ የሚሆኑ ሴት ወላጆች በላሞች (33%)፣ ግመሎች (31%) እና ፍየሎች (36%) ላይ የተወሰነ ቁጥጥር እንዳላቸው ተናግረዋል። ከግማሽ በላይ (57%) በዶሮዎች ላይ የተወሰነ ቁጥጥር እንዳላቸው ተናግረዋል። ሴቶች በእንስሳት ላይ ያላቸውን ቁጥጥር በተመለከተ የወንዶች ሪፖርት በጣም ያነሰ ነበር። በአማካይ ከሴቶቹ ግማሽ ያህሉ ወንዶች ነበሩ ሴቶች በላሞች፣ ግመሎች እና ፍየሎች ላይ ቁጥጥር እንዳላቸው ሪፖርት ያደረጉት።8


የአፋር ወላጆች ልክ እንደ ወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጆቻቸው፣ ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም ከማህበራዊ ማንልበት የበለጠ ፍትሃዊ እምነቶችን ገልጸዋል። ሁሉም ማለት ይቻላል ሴት (98%) እና ወንድ (90%) የወላጆች ሴቶች ከወንዶች እኩል የመስራት እድል ሊኖራቸው እንደሚገባ እና ሴቶች ቁጠባ (99% እና 96%) ሊኖራቸው ይገባል ብለዋል (ምስል 54 ይመልከቱ)። ነገር ግን፣ ሁሉም ማለት ይቻላል ሴት (92%) እና ወንድ (96%) የወላጆችም ወንዶች የመጨረሻውን አስተያየት እንዲሰጡ እና 97% ወንዶች እና 91% ሴቶች ሚስቶች ሁል ጊዜ መታዘዝ እንዳለባቸው ተስማምተዋል። አብዛኛዎቹ ሴቶች (87%) እና ወንድ (68%) ወላጆች ከወንዶች ይልቅ የሴቶችን ልጆች ባህሪ መቆጣጠር እንዳለባቸው ተስማምተዋል። እነዚህ የፆታ ልዩነቶች በጣም አስፈላጊ ነበሩ፡ ፡ ለቅርብ ጓደኛ/አጋር ጥቃት ሪፖርት የተደረገው ድጋፍ ዝቅተኛ ነበር፣ በግምት ግማሽ ያህሉ የወላጆችም ተቀባይነት ያለው እና የግል ጉዳይ እንደሆነ ተስማምተዋል። ልዩነቶች ከትክክለኛ እምነት ይልቅ በሪፖርት አቀራረብ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያ ሲሰጡ፣ ሴቶች በሁለቱም ጥያቄዎች ላይ ከወንዶች በበለጠ ለቅርብ ጓደኛ ጥቃት ድጋፍ ሰጥተዋል። ለምሳሌ፡ 49% ወንዶች እና 63% ሴቶች ለቅርብ ጓደኛ/አጋር ጥቃት የግል ጉዳይ እንደሆነ ተስማምተዋል። አብዛኛዎቹ የወላጆች ያለ ጾታ ልዩነት፣ “በፖለቲካ ወይም በአመራር ቦታ የሚሳተፉ ሴቶች ጥሩ ሚስት ወይም እናት ሊሆኑ አይችሉም” በማለት ተስማምተዋል።

የአይነታዊ ጥናት መረጃ እንደሚያመለክተው የወጣቶች እና ወላጆች በአንጻራዊነት ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የሴቶችን

ምስል 52: የአፋር አሳዳጊዎች ወጪ እና ቁጠባ




ምስል 53: የአፋር አሳዳጊዎች የገቢና ንብረትን የመቆጣጠር ሁኔታ




8 በጣም ጥቂት ወንዶች ስለ ዶሮዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል።

ኢኮኖሚያዊ አቅምን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት በዋናነት በሁለት አይነት አውነታዎች የተከፈለ ነው። በመጀመሪያ፣ ምንም እንኳን የሚከፈልበት ሥራ ጥቂት ቢሆንም፣ በተለይም በሐሪ ረሱ [ዞን 5]፣ የሴቶች የቤት እንስሳትን የማርባት ሥራ ለቤተሰብ መተዳደሪያው ወሳኝ ነው። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነች እናት በህብረተሰቡ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች ለደሞዝ እንደሚሰሩ ሲጠየቁ የሚከተለውን ብለዋል።

> የሚከፈልበት ሥራ ለሁሉም የተለመደ አይደለም። ሥራ የሚሰሩት ጥቂት ወንዶች ብቻ ናቸው። በዚህ ቀበሌ የስራ እድል ቢፈጠር ሁሉም ሴቶች እና ወንዶች ይሰሩ ነበር።

የዚሁ ዞን ነዋሪ የሆነች ወጣት፣ “ፍየል ገዝቼ እሸጣለሁ። ለቤተሰቦቼ በማገኘው ትርፍ እቃ እገዛሁ እና በዋናው ሌላ ፍየል እገዛለሁ።” ብላለች። ሁለተኛ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተከፈቱ ከስራ ጋር የተያያዙ የስደት እድሎችን በዋነኝነት የሚያገኙትና ገቢያቸውን ለቤተሰባቸው ኑሮ ለማሻሻል ለሚጠቀሙ ልጃገረዶች እና ሴቶች ነው። አንድ የ15 አመት የሃሪ ረሱ [ዞን 5] ልጅ እንደገለፀው፣ “አብዛኞቹ ስደተኞች ሴቶች ናቸው…ሴቶች ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ሳኡዲ አረቢያ ይሰደዳሉ።” ሴት ልጇን ለስራ ወደ ውጭ ሀገር ልታስወጣ ትችል ዘንድ የምትጠባበቅ አንድ እናት እንዳለችው፤

> ልጄ እንድትሰደድ፣ እዚያ እንድትሰራ እና ገንዘብ እንድታገኝ እፈልጋለሁ። ደስተኛ ሕይወት እየመራን አይደለም። ገንዘብ የለንም። ልጆቻችን እንዲሰሩ እና የገንዘብ ህይወታችንን እንዲቀይሩ እንፈልጋለን። ስለ ወደፊቱ ጊዜ አናውቅም፤ አላህ ያውቃል። ልጄን 15 ወይም 16 ዓመት ሲሞላት ወደ አረብ ሀገር ልልካት አስቤያለሁ።


ቀደም ሲል በአፋር የገጅ ጥናት እንዳረጋገጠው የቅርብ አጋር ጥቃት እጅግ በጣም የተለመደ መሆኑን በመግለጽ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ምላሽ ሰጪዎች ልጃገረዶች እና ሴቶች መብታቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያወቁ እና የማሳወቅ እድሎች መኖራቸውን ዘግበዋል። በአውሲ ረሱ [ዞን 1] ነዋሪ የሆነች አንዲት ባለትዳር የ21 ዓመት ወጣት ሚስቶች ቅሬታቸውን ወደ አካባቢው ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤት እንደሚወስዱ እንዲህ ስትል ገልጻለች፡ “አሁን ሴቶቹ ምንም ዓይነት አካላዊ ጥቃት ቢደርስባት ጉዳዩን ለሸሪዓ ያሳውቃሉ።” የሃሪ ራሱ [ዞን 5] ነዋሪ የሆነው የ20 ዓመት ወጣት ይህ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለመደ መሆኑን ይስማማል፤

> በአሁኑ ጊዜ ሴቶች እና ልጃገረዶች ስለ መብታቸው እና እንዲሁም የት ሄደው የጥቃት ጉዳዮችን ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ፣ በባሎቻቸው ወይም በሌሎች ጥቃት ቢደርስባቸው… ባሎች ሚስቶችን አይቀጡም። ሚስት ስህተት ብታደርግ ባል ሳይገርፉት ይመክራል ያስተካክላታል። ነገር ግን ባሎች ሚስቶችን ለመቅጣት ወይም ለመግረፍ ከሞከሩ ሚስቶች ወደ ወረዳው ቦዋሳ (የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ) ቀበሌ በመሄድ ባለቤታቸውን በመውብት ረገጣ ይከሳሉ።

## ሶማሊ

ባለፈው አመት በሶማሊ የሚገኙ ወጣቶች በእጃቸው ገንዘብ እንደነበራቸው ሪፖርት ያደረጉት ትቂት (6%) ነበሩ ። ለወጣቶች ምንም አይነት ቁጠባ እንዳላቸው ሪፖርት ያደረጉም በጣም ዝቅተኛ (9%) ነበር ። ለሁለቱም ጠቋሚዎች ምንም ዓይነት የፆታ ልዩነቶች አልነበሩም ነገር ግን በጃራራ ውስጥ ያሉ

ምስል 54: የአፋር አሳዳጊዎች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መጎልበት ያላቸው እምነት




ወጣቶች በፋፋን ከሚገኙት እኩዮቻቸው ይልቅ የመቆጠብ ዕድላቸው ከፍተኛ (18% ለ 5%) ነበር ። ቁጠባ ካላቸው አናሳ ወጣቶች መካከል አብዛኞቹ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በቤት ውስጥ ያስቀመጡ ናቸው።

የፕሮግራም አጋማሽ ጊዜ ዳሰዛ የሶማሊ ልጃገረዶች እና ወንዶች ልጆችን ማህበራዊ አቅምን ለመመልከጽ የተነደፉ የተለያዩ ጥያቄዎችን አካትቷል። በአብዛኛዎቹ አመላካቾች፣ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ችግር አለባቸው። ለምሳሌ ጓደኛን ወይም ጎረቤትን አዘውትረው የመጎብኘት ዕድላቸው አናሳ (40% ለ 52%)፣ በመደበኛነት መስጊድ የመሄድ እድላቸው አነስተኛ (26% ለ 52%) እና አርአያ የማግኘት እድላቸው አነስተኛ (42% ለ47%) ነበር (ስእል 55 ይመልከቱ)። ለእኩያ ወይም ለአዋቂ ሰው ሃሳብና ስሜታቸውን መግለጽ ከመቻል አንጻር ወጣት ሴቶች እና ወንዶች በተመሳሳይ መልኩ አልቻሉም፣ ይህንን ለማድረግ የተመቻቸው ከግማሽ በታች ነበሩ።


ምንም እንኳን የሶማሊ ወጣቶች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ ማጎልበት ፍትሃዊ እምነቶች ቢናገሩም ስለሴቶች ማህበራዊ ብቃት ያላቸውን እምነት በተመለከተ ተመሳሳይ ነገር ሊባል አይችልም። ሴቶች ከወንዶች እኩል የመሥራት እድል ሊኖራቸው ይገባል፣ እና ሴቶች ለወደፊት ቁጠባ እንዲኖራቸው ይስማማሉ ወይ ተብለው ሲጠየቁ፣ ሁሉም ወጣት (93%) ማለት ይቻላል - በጾታ እና በቦታ ልዩነት ሳይኖር - ተስማምተዋል (ምስል 56 ይመልከቱ)። ሆኖም 95% የሚሆኑት ቤተሰቦች ሴቶች ልጆቻቸውን ከወንዶች በላይ እንዲቆጣጠሩ ተስማምተዋል። 82% የሚሆኑት ደግሞ ሚስት ባሏን በሁሉም ነገር መታዘዝ እንዳለባት ተስማምተዋል። ወደ ሶስት አራተኛ የሚጠጉ (71%) "በፖለቲካ ወይም በአመራር ቦታ የሚሳተፉ ሴቶች ጥሩ ሚስት ወይም እናት መሆን አይችሉም።" በማለት ስምምነታቸውን ገልጸዋል።

በማያስገርም ሁኔታ በሶማሊ የጥናት ቦታዎች የሚገኙ ወላጆች በታዳጊ ዕድሜ ላይ ከሚገኙት ልጆቻቸው ይልቅ ገንዘብን የመቆጣጠር እና የቁጠባ እድላቸው ከፍተኛ ነው። ከሴት የወላጆችም 46% የሚሆኑት ባለፈው አመት ገንዘብ ተቆጣጥረው 28% ቁጠባ ነበራቸው (ምስል 57 ይመልከቱ)። ከወንድየወላጆች ውስጥ 52% ገንዘቡን ተቆጣጠሩ እና 37% ቁጠባ ነበራቸው። አብዛኛዎቹ ወንዶች እና ሴቶች እንደሚናገሩት በእነሱ ቁጥጥር ስር የሚገኘው ገንዘብ የሚገኘው ከብት ወይም ሰብል በመሸጥ ነው። ቁጠባ ያላቸው አብዛኛዎቹ የወላጆች እነዚያን ቁጠባዎች በቤታቸው አስቀምጠዋል።

ምስል 55: ለሶማሊ ወጣቶች የማህበራዊ አቅም መጎልበት አመላካቾች




ምስል 56: የሶማሊ ወጣቶች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አቅም መጎልበት ያላቸው እምነት




ምንም እንኳን አብዛኛው ሴት እና ወንድ የወላጆች ቢያንስ አንዳንዶች በራሳቸው ገቢ፣ በተዳር ጓደኛቸው ገቢ እና በቤተሰብ ሀብት ሸያጭ ላይ አስተያየት ማድረጋቸውን ቢገልጹም፣ በሦስቱም ጠቋሚዎች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ተጠቃሚ ሆነዋል። ለምሳሌ፣ 82% የሚሆኑ ሴት የወላጆች የቤት ውስጥ ንብረት ሽያጭ ላይ መሳተፋቸውን ሲገልጹ፣ 90% ወንድ የወላጆችም ተመሳሳይ ነበር (ምስል 58 ይመልከቱ)።


የእንስሳት ሀብት ባለቤትነትን ከሚናገሩት የወላጆች መካከል አብዛኞቹ በሶማሊ የሚኖሩ ሴት የወላጆች ላሞች (71%)፣ ግመሎች (76%) እና ፍየሎች (76%) የተወሰነ ቁጥጥር እንዳላቸው ተናግረዋል። ወደ ሁለት ሦስተኛ የሚጠጉ (63%) በዶሮዎች ላይ የተወሰነ ቁጥጥር እንዳላቸው ሪፖርት አድርገዋል። የወንድ ወላጆች የናሙና መጠን ትንሽ ነው፤ መረጃው በጥንቃቄ የሚታይ ሆኖ፣ ወንድ ወላጆች ከሴት ወላጆች ጋር ስለ ሴቶች ላሞች ቁጥጥር (74%) ስምምነት ላይ ነበሩ። ወንዶቹ ግን ሴቶች በግመሎች እና በፍየሎች ላይ የቁጥጥር መብት አላቸው በሚለው የመስማማት ዕድላቸው አነስተኛ ነበር፣ በግመሎች ላይ (50%) እና በፍየሎች ላይ (54%) ብቻ ነበር።[9]

በሶማሊ የጥናት በታዎች የሚገኙ ወላጆች ልክ በታዳጊ ዕድሜ ላይ እንደሚገኙ ልጆቻቸው፣ ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልበት ከማህበራዊ አቅም ማጎልበት የበለጠ ፍትሃዊ እምነቶችን ገልጸዋል ። ሁሉም ማለት ይቻላል ሴት እና ወንድ ወላጆች፣ ለምሳሌ፣ ሴቶች ከወንዶች እኩል የመስራት እድል ሊኖራቸው ይገባል (~95%) እና ሴቶች ቁጠባ (~93%) ሊኖራቸው ይገባል ብለው ያምኑ ነበር (ምስል 59 ይመልከቱ)። ነገር ግን፣ በተመሳሳይ ትልቅ ክፍል (~89%) ቤተሰቦች ሴቶች ልጆቻቸውን ከወንዶች ይልቅ መቆጣጠር እንዳለባቸው ተስማምተዋል፣ እና አብዛኞዎቹ (~69%) የቅርብ አጋር ጥቃት ተቀባይነት እንዳለው ተስማምተዋል። ከትክክለኛ እምነቶች ይልቅ በሪፖርት አቀራረብ ምክንያት ልዩነቶች እንደሚበዙ በመግለጽ፣ በአንዳንድ የሴቶች ማህበራዊ አቅምን የሚያሳዩ የፆታ ልዩነቶች ነበሩ። ለምሳሌ፣ ሴት የወላጆች ሴቶች ሁል ጊዜ ባሎቻቸውን መታዘዝ አለባቸው (87% ለ 78%) እና (IPV) የግል ጉዳይ ነው (86% ለ 78%) ከወንዶች የበለጠ የማመን እድላቸው ሰፊ ነው። በአንፃሩ ወንድ የወላጆች ከሴቶቹ የበለጠ "በፖለቲካ ወይም በአመራር ቦታ ላይ የሚሳተፉ ሴቶች ጥሩ ሚስት እና እናት ሊሆኑ አይችሉም" በሚለው ይስማማሉ።

ምስል 57: የሶማሊ አሳዳጊዎች ወጪ እና ቁጠባ





ምስል 58: የሶማሊ አሳዳጊዎች የገቢና ንብረትን የመቆጣጠር ሁኔታ




9 በጣም ጥቂት ወንዶች ስለ ዶሮዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል።

ምስል 59: የሶማሊ አሳዳጊዎች ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መጎልበት ያላቸው እምነት




የአይነታዊ ጥናት ተሳታፊ ልጃገረዶች እና ጎልማሳ ሴቶች ለእንክብካቤ እና ለቤት ውስጥ ስራ ብቻ ተጠያቂ እንደሆኑ ተናግረዋል። የ14 ዓመት የሃርሼን ታዳጊ እነዳለው ምንም እንኳን ወንዶች ልጆች አልፎ አልፎ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ቢረዱም እህቶቻቸው ይበልጥ አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎች ላይ ሲመደቡ ብቻ ነው (ለምሳሌ "ሴቶቹ ሱቅ በማስተዳደር ሲቀሩ")፣ በታዳጊ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች እና ወጣቶች ሴቶች ባሎቻቸው እና ወንድሞቻቸው የቤት ውስጥ ሥራዎችን እንደማያደርጉ ያለ ልዩነት ተናግረዋል። የጎልጃኖ ነዋሪ የሆነች የ22 ዓመቷ እናት "ሁሉንም የቤት ውስጥ ሥራዎችን የምሠራው በራሴ ብቻ ነው" ስትል ተናግራለች። በእርግጥም የ20 ዓመቱ አባት ከጎልጃኖ በተጨማሪ ሚስቱ፣ እናቱ እና እህቱ ልጁን መንከባከብ ካልቻሉ ምን እንደሚያደርግ ተጠይቆ፣ "ሌላ ሴት ጋር እጸውላለሁ… የሴቶች ስራ ነው" ብሏል።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በፋፋን ልጃገረዶችና ጎልማሳ ሴቶች በደመወዝ ሥራ የሚሰማሩበት ዕድል ውስን መሆኑን (በተለይ ጎልጃኖ ለወጣትና ጎልማሳ ወንዶችም የደሞዝ ስራ የማይገኝበት) የሴቶች ሥራ በእንስሳት እርባታና በራስ


የ22 አመት ነርስ በጤና ጣቢያ፣ አፋር፣ ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.



የ25 ዓመቷ የሶስት ልጆች እናት በጤና ጣቢያ፣አፋር፣ ኢትዮጵያ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

ተቀጣሪነት እንደሆነ ምላሽ ሰጪዎች ተስማምተዋል፡፡ ይህም ለረጅም ጊዜ ለቤተሰብ ኑሮ እና ለማህበረሰብ ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ይህ ስለሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም ማጎልበት የወላጆች እና የወጣቶችን በአንጻራዊነት ፍትሃዊ እምነት ለማብራራት ይረዳል፡፡ የሀርሸን ከተማ አንድ የሀይማኖት መሪ የአካባቢው ሴቶች ምን አይነት ስራ ይሰራሉ ተብሎ ሲጠየቅ ፍየሎችን ማደለብ ብቻ ሳይሆን “እንደምታየው እዚህ ያሉት አብዛኛዎቹ ሱቆች የሴቶች ንብረት ናቸው… በሆቴልና በሱቅ ንግድ ላይ ተሰማርተዋል” ሲሉ መልሰዋል፡፡ እንደውም እንደ ሻይ ወይም ጫት መሸጥ ያሉ የራሳቸውን አነስተኛ የንግድ ሥራዎችን መሯሯጥ ለሴት ልጆች እና ሴቶች በተለይም በሃርሸን ከተማ የተለመደ ነው ብለዋል፡፡[10] የሃርሸን ነዋሪ የሆነች የ20 ዓመቷ ወጣት ሴት ይህ ክስተት ብዙም አዲስ እንዳልሆነ አስተውላለች፡፡ አሁን ሁለት አስርት ዓመታትን ያስቆጠረው የእናቷ የጫት ንግድ ለቤተሰቡ የቤትም ሆነ መኪና ባለቤት አድርጓቻ ነበር፡ “መኪናውን የገዛነው ከአምስት አመት በፊት ነው ቤቱ የተገነባው ከ10 አመት በፊት ነው፡፡”

ምላሽ ሰጪዎች በተለይም ከሀርሸን እንደተናገሩት በሶማሊም ሆነ በሶማሊላንድ ወደ ተለያዩ ከተሞች የሚደረገው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ ወጣቶች ገቢ የሚያገኙበትን እድል አስፍቷል፡፡ በተጨማሪም ልጃገረዶች እና ጎልማሻ ሴቶች ከጳዳጊና እና ከጎልማሻ ወንዶች ያነሰ እድሎች እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ አንድ የ18 ዓመት ወጣት የሃርሼን ልጅ እንዲህ ሲል ገለጸ፤

> ሴቶችም ወንዶችም ወደ ሀርጌሳ አካባቢ እየሄዱ ነው፣ ነገር ግን አብዛኞቹ ወንዶች ናቸው… ምክንያቱም የስራ እድሎች ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች በብዛት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ወንዶች በሱፐርማርኬቶች ውስጥ ሊሠሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን ሴቶች ብዙውን ጊዜ ለነዚያ ሚናዎች አይቀጠሩም… ወንዶችም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ሥራ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛዋም አንዳንድ ልጃገረዶች ወደ ሌሎች ሀገራት በተለይም ወደ ሶማሊላንድ እንደሚሰደዱ ገልፃ ሁሉም ሴት ስደተኞች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ስራ እንደሚይዙ አብራርታለች፡ “ልጃገረዶች… የቤት ሰራተኛ ይሆናሉ፡፡”

በፋፋን ውስጥ ያሉ ጥቂት ምላሽ ሰጪዎች ብቻ ስለልጃገረዶች እና ጎልማሳ ሴቶች ሰፋ ያለ ማህበራዊ አቅም እና የጥቃት ስጋት ተናግረዋል፡፡ የሃርሼን ነዋሪ የሆነች የ17 ዓመቷ ልጅ ሴት ልጆች ከወንዶች ይልቅ ለጥቃት የተጋለጡ ናቸው፤ ምክንያቱም በአባታቸው እና በወንድሞቻቸው ስለሚደበደቡ፡፡ የዚሁ ወረዳ የሀይማኖት መሪ አክለውም ሴቶች በባሎቻቸው የሚጨቆኑ ሲሆን ኑሮን ለማስጠበቅ ሴቶችን የቤት ውስጥ ትተው ወንዶቹ ጫት በመቃም ጊዜያቸውን ያባክናሉ ብለዋል፡፡

> ሴቶቹ በአብዛኛው ተገዢ እና ተጨቋኝ ናቸው፡፡ ባሎቻቸው በጣም ይጨቁኗቸዋል፡፡ ሴቶቹ ከብቶቹን የመንከባከብ እና ለቤተሰብ ምግብ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ባሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ፍለጋ በከተማው ሲንከራተቱ እና ጫታቸውን ሲቃሙ ልጆቹ እና ሚስቶች ለዚህ አይነት ተግባር ተጠያቂው አካል ናቸው፡፡

10 ጫት በመላው አፍሪካ ቀንድ የሚበቅል ተክል ነው፡፡ ቅጠሎቹ የሚታኘኩት ለአበረታች ውጤት ነው፡፡

# መደምደሚያ እና ለፕሮግራም እና ፖሊሲ ያለው አንድምታ

በአጠቃላይ፣ የእኛ የፕሮግራም አጋማሽ ጥናት ግኝቶች ከመነሻ ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በእኛ ናሙና ውስጥ በታዳጊ ዕድሜ ላይ ባሉ ወጣቶች እና የወላጆች ሕይወት ላይ ከፍተኛ ለውጦች መኖራቸውን ያሳያል። ከእነዚህ ለውጦች መካከል ጥቂቶቹ (ለምሳሌ ለድርቅ መጋለጥ) በሁለቱ ክልሎች ተመሳሳይ ናቸው፤ ሌሎች ደግሞ በአንድ ክልል ብቻ ተወስነዋል (ለምሳሌ በሶማሊ የጋብቻ ዕድሜ እያሽቆለቆለ ነው) ከዚህም አልፎ በአንድ ክልል ውስጥ ባለ አንድ ዞን ብቻ (ለምሳሌ በሃሪ ረሱ (ዞን 5) ግጭት) ተከስቷል። ከእነዚህ ለውጦች መካከል አንዳንዶቹ አዎንታዊ ነበሩ (ለምሳሌ በአፋር ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛትን አደጋዎች የተሻለ መገንዘብ) እና ሌሎች ደግሞ አሉታዊ ናቸው (ለምሳሌ፣ በሶማሊ ህጻናት ጋብቻ መጨመር እና የጋብቻ ዕድሜ መቀነስ)። ወላጆችከዚህ በመቀጠል እነዚህን ለውጦች ጠቅለል አድርገን እና ግኝቶቻችንን በፖሊሲ እና በፕሮግራም ላይ ያለውን አንድምታ በመጠቀም እናጠቃልላለን።

የፕሮግራም አጋማሽ ጥናቱ እንዳመለከተው የእንስሳት ሀብት አሁንም ለአፋር እና ሶማሊ ቤተሰቦች ኑሮ ጠቃሚ ቢሆኑም፣ ወቅታዊ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀሳቀስ እየቀነሰና የገቢ ማግኛ ዘዴዎች እየጨመሩ መጥተዋል። በተለይ በሶማሊ ብዙ አባወራዎች በእርሻ ላይ ብቻ ሳይሆን በንግድም የሚሰማሩበት ሁኔታዎች አሉ። ይህም በክልሎቹ ያለውን የምግብ ዋስትና እጦት መጠን የሚንፀባረቅ ሲሆን በአፋር ያለው ከሶማሊው በእጥፍ ከፍ ያለ ነው። በሁለቱም ክልሎች የአየር ንብረት ለውጥ እና የምግብ ዋስትና እጦት ተባብሷል፣ ድርቅ፣ ጎርፍ፣ በሽታ እና ወራሪ ዛፍ ዝርያዎች የእንስሳት ሀብትና የሰብል ምርትን አውድመዋል። በከፋ ድርቅ ወቅት አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ቢደረግም ምላሽ ሰጪዎች (በተለይም በአፋር በሃሪ ረሱ (ዞን 5) ዞን) አሁን ያለው የማህበራዊ ጥበቃ ደረጃ ከፍላጎት ጋር የማይመጣጠን መሆኑን ተስማምተውበታል።

ትምህርትን በተመለከተ የፕሮግራም አጋማሽ ጥናቱ እንዳመለከተው የትምህርት ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም በሁለቱም ክልሎች ከፍተኛ የስርዓተ-ፆታ ልዩነት አለ። የልጃገረዶች እና የወጣት ጎልማሳ ሴቶች ፍላጎት ከታዳጊ እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ያነሰ ነው። የወላጆች ለሴቶች ልጆች ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ለወንዶች ልጆቻቸው ካላቸው ያነሰ ነው። በምዝገባና ትምህርት ገበታ ላይ መገኘት ላይም የፆታ ልዩነት አለ። በሁለቱም ክልሎች ያሉ ሴት ልጆች በትምህርት ቤት የመመዝገብ እድላቸው አነስተኛ ሲሆን የማቋረጥ ዕድላቸው እጥፍ ነው። ምላሽ ሰጪዎች፣ ምንም እንኳን ህጻናት ጋብቻ እና የልጃገረዶች በለጋ እድሜያቸው ለህገ-ወጥ ስደት መጋለጥ ወሳኝ ነገሮች ቢሆኑም ይህ በአብዛኛው በልጃገረዶች የቤት ውስጥ እና የእንክብካቤ ስራ ላይ ወላጆች በሚጠይቁት ጥያቄ ምክንያት እንደሆነ ይስማማሉ።

በተጨማሪም መደበኛ ትምህርት በአፋርና በሶማሊ አዲስ በመሆኑ (በተለይም በአፋር በሃሪ ረሱ [ዞን 5]) የመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት አሁንም በከተሞች ብቻ በመሆኑ እና በመንከባከብ ሃላፊነት ምክንያት ብዙ ህጻናት አይማሩም። ይህ ማለት እስከ ታዳጊነት እድሜ መጀመሪያ ድረስ መመዝገብ አይችሉም። የአብዛኞቹ ተማሪዎች እድሜ ከሚማሩበት ክፍል አንፃር ከሚጠበቀው በላይ ናቸው። ይህ ማለት ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በላይ የመማር እድል ያላቸው (በተለይም ልጃገረዶች) ጥቂቶች ብቻ ናቸው።በድርቅ እና በአፋር በሃሪ ረሱ [ዞን 5] ግጭቶች ምክንያት የህብረተሰቡ አባላት እና መምህራን ከትምህርት ይልቅ ህልውናቸውን እንዲያስቀድሙ በመገደዳቸው የወጣቶችን የትምህርት እድል ገድቧል።

በተደረገው ጥናት መሰረት ምንም እንኳን የሴት ልጆች ግርዛት የሚደረግባቸው ጊዜያት ልዩነት በመኖሩ በሶማሊ የጥናቱ ናሙና ውስጥ የነበሩት በታዳጊ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች ሁሉም ላይ ባይፈፀምም የሴት ልጅ ግርዛት በአፋር እና በሶማሊ ላሉ ልጃገረዶች በነበረበት ሁኔታ እንደሚቀጥል ተደርሶበታል። የሴት ልጅ ግርዛት አይነት በሁለቱም ክልሎች አከራካሪ ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም ምላሽ ሰጪዎች የሚረዱት አሁን ያሉ ድርጊቶችን ከባህላዊ ድርጊቶች ጋር በተገናኘ ብቻ ነው። ይህም እጅግ በጣም ፅኑ እና ወግ አጥባቂነት የሚስተዋልበት ነው። በመሆኑም ምላሽ ሰጪዎች (በተለይ በከተሞች ያሉ) ድርጊቱን እንደ ሱና (በሀይማኖት የተፈቀደ) አድርጎ ለመቀበል ይቸገራሉ። ምንም እንኳን አብዛኛው የሁለቱም ክልሎች ልጃገረዶች ብልት መጥበብ ቢደርስባቸውም፣ ከመጠበቡ በፊት የተወገደው ሥጋ መጠን እና የመጥበብ ደረጃው ከጊዜ ወደ ጊዜ ቀስ በቀስ "እየተሻሻለ" ይመስላል። ይህም በአብዛኛው የሃይማኖት መሪዎች በሚሰጡት ምክር ነው። የሃይማኖት መሪዎቹ በሴት ልጅ ግርዛት ህግ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ውስን ቢሆንም ከ የሴት ለጅን ብልት ዙሪያ ተልትሎ መግጠምና መስፋት (infibulation) ይልቅ የብልትን ጫፍ ብቻ መቁረጥ (clitoectomy) ይመክራሉ። ምንም እንኳን በክልሎች መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም፣ በአፋር ያሉ ምላሽ ሰጪዎች በአጠቃላይ የሴት ልጅ ግርዛት አደጋን የሚያውቁ፣ ድርጊቱን ለመቀጠል የመደገፍ ዕድላቸው አነስተኛ እና ለ"መለስተኛ" የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች ከሱማሌ እኩዮቻቸው የበለጠ የሚቀበሉ ቢሆንም፣ በሁለቱም ክልሎች ለድርጊቱ አሁንም ጠንካራ ድጋፍ አለ። ይህ የሆነበት ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛት በሃይማኖት (በተለይ በሶማሊ) ያስፈልጋል፣ ለባህል መስፋፋት አስፈላጊ ነው፣ የሴት ልጆችን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ይቆጣጠራል እና ለትዳር ተስማሚ ያደርጋቸዋል በሚለው እምነት ነው። በእርግጥ በሶማሊ፣ ጎልማሳ ሴቶች እና የወደፊት ሙሽሮች ብዙውን ጊዜ የሴት ልጅ ግርዛትን መደገፍ ብቻ ሳይሆን በተለይም የሴት ብልት ማጥበብን እንደሚደግፉ ይገልጻሉ። ይህም ሙሽሪት በፆታ ግንኙነት ወቅት ንፁህ መሆኗን ለማረጋገጥ ብቸኛው መንገድ ስለሆነ እንደሆነ ተለይቷል። በሶማሊ የሴት ልጅ ግርዛት እና በግርዛት የጠበበን ብልት የማስፋት ድርጊቶች በህክምና እየታገዙ እንዳሉ፤ የሴት ልጅ ግርዛት ሙሉ በሙሉ የሴቶች እይታ እንደሆነ ጎልማሶች እና ወጣቶች እንደሚስማሙ እና የመንግስት ባለስልጣናት እና

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞችም ብዙውን ጊዜ መለስተኛው ግርዛት (የሴት ልጅ ብልትን ጫፍ ብቻ መቁረጥ) ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንደተቀበሉ አንዳንድ ማስረጃዎችን ተገኝተዋል። በአፋር ክልል፣ አባቶች ሴት ልጆቻቸው ምን አይነት የሴት ልጅ ግርዛት እንደሚደረግባቸው ሃሳብ የመስጠት እና አንዳንድ ፍቃደኞች (በአውሲ ረሱ ከተማ አካባቢዎች [በዞን 1] ብቻ) ድርጊቱን ሙሉ በሙሉ ለመተው የተወሰነ ፍላጎት ነበራቸው።

የአጋማሽ ጊዜ ጥናቱ ሲደረግ በናሙና ውስጥ ያሉት አማካይ ወጣቶች ገና 16 ዓመት ያልሞላቸው ስለነበሩ ያገቡት ጥቂቶች ነበሩ። በሁለቱም ክልሎች በተለይም ራቅ ባሉ የገጠር ቀበሌዎች ልጃገረዶች የወር አበባ እንዳዩ 15 ዓመታቸው ገደማ እንደሚያገቡ ሰፊ ስምምነት ላይ በተደረሰበት ሁኔታ ይህ አሀዝ በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ ለውጥ ያመጣል ብለን እንጠብቃለን። ሶማሊዎች ለ የህጻናት ጋብቻ የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው። ለአደጋ የተጋለጡበት ምክንያቶች በጣም የተለያዩ ናቸው። በአፋር ክልል፣ ምላሽ ሰጪዎች በወላጆች ምክንያት የህጻናት ጋብቻ የተለመደ መሆኑን ገልፀዋል። አሁንም በዋነኛነት የትዳር ጓደኛሞች በእናቶች በኩል የአጎት ልጆች መሆናቸውን የሚገልጽ የጋብቻ ባህልን በመከተል ላይ ናቸው። ይሁን እንጂ በልጃገረዶች የተሻሻለ የመደበኛ ትምህርት ዕድል ምክንያት ልጃገረዶች (እና መምህራኖቻቸው) የዘገየ ጋብቻን ለመደገፍ እና ልጃገረዶች የሚፈልጉትን የትዳር አጋር እንዲመርጡ ማድረግን ለማስተዋወቅ እድሉ ሰፍቷል። በሱማሌ ክልል የሃይማኖት መሪዎች ሴት ልጆች በህጋዊ መንገድ እድሜያቸው ልጅ ቢሆኑም ጋብቻን የማፅደቅ መብት እንዳላቸው ተስማምተው፣ የሴት እና ወንድ ልጆች የህጻናት ጋብቻ የበለጠ እየተለመደ መምጣቱን እና የጋብቻ እድሜ እየቀነሰ መምጣቱን፤ ይህም ሙሉ በሙሉ በታዳጊዎቹ ፍላጎት ላይ የመሰረተ ክስተት መሆኑን ገልፀዋል። ይህ ብዙውን ጊዜ በሞባይል ስልኮች እና በከፍተኛ ሁኔታ ትምህርት መግባት ምክንያት የሴቶች እና ወንዶች ልጆች እርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት መጨመር ምክንያት ነው ይላሉ። በሁለቱም ክልሎች ጎልማሶች እና ወጣቶች ስለ ጋብቻ ህግ ያላቸው ግንዛቤ ውስን ነው።

በአፋርም ሆነ በሶማሊ፣ እና በተለይም በብዙ የገጠር ማህበረሰቦች፣ የልጃገረዶች እና የሴቶች ሰፋ ያለ የስልጣን ተጠቃሚነት ውስን ነው፣ ምክንያቱም በሰፊው፣ ጥልቅ የአባቶች የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች ምክንያት። ልጃገረዶች እና



የሶማሊያ ወጣት እናት ሰብሎቿን ስትጠብቅ ©ናታሊ በርትራምስ/ ጌጅ 2017 ዓ.ም.

ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ከታዳጊና እና ወጣት ጎልማሳ ወንዶች ያነሰ የመንቀሳቀስ እና በጣም የተገደበ ድምጽ አላቸው፡ ፡ በተመሳሳይ፣ ሴቶች በንብረት እና በገንዘብ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ከወንዶች ያነሰ ቁጥጥር አላቸው፣ በተለይም በአፋር (ሴቶች በብዛት በንግድ ስራ የማይሳተፉበት)። ምንም እንኳን ልጃገረዶች እና ሴቶች የሚያገኙበት እና ለቤት ውስጥ መተዳደሪያ የሚያበረክቱት ቦታ እያደገ ቢመጣም በወጣቶች እና በአሳዳጊዎች መካከል ከወንዶች ልጆች ይልቅ የሴቶች ልጆች ባህሪ መቆጣጠር እንዳለበት እና ባልም የራሱን ሚስት ሀይልንም ተጠቅሞ ቢሆን የመቆጣጠር ስልጣን እንዳለው በስፋት መግባባት ላይ ተደርሷል።

ወላጆችህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻናትህጻናት ህጻናትሰፋ ያለ የጥናት ግኝቶቻችንን በማንሳት የኢትዮጵያ መንግስት እና አጋሮቹ የህጻናት አድን ድርጅቱን ጨምሮ የህጻናትን ጋብቻ እና ግርዛትን ለማስቀረት የወጣው ብሄራዊ ፍኖተ ካርታ ግቦች እንዲሳኩ ከተፈለገ የሚከተሉትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት እንጠቁማለን። በታዳጊ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች እና ወጣት ጎልማሳ ሴቶች ለውጦችን በፍጥነት ለመከታተል የሚያስፈልጉትን ተዋናዮች እና በሚሰጣቸው ኃላፊነት ውስጥ የሚኖራቸውን ልዩ ተግባራት እናሳያለን፤ ጥረቶች በጥሩ ሁኔታ የተቀናጁ እና እርስ በርስ የሚደጋገፉ እንዲሆኑ እናስገነዝባለን።

**የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን የሚከለክለው ህግ ውስን በመሆኑ፣ እንዷ አፈጻጸምም ሁሉም የፍትህ ሴክተሩ በጎጂ ልማዶች ላይ ሀገራዊ ህጎችን የማስተዋወቅ እና የማስከበር ጥረቶችን ማጠናከር አለበት።** ይህም የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- በመብት ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶችና (የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበርን ጨምሮ) ከክልል መንግስታት ጋር በመተባበር ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን የሚከለክሉ የክልል ህጎች ከሀገራዊ ህጎች ጋር እንዲጣጣሙ እና የቤተሰብ ህጉን በማፅደቅ እነዚህ ድርጊቶች በወንጀል እንዲከሰሱ ማድረግ።
- የሴት ልጅን እና የሴቶችን የትምህርት፣ የውርስ እና ከጥቃት ነፃነታቸውን (የሴት ልጅ ግርዛትን ጨምሮ) ለማሻሻል ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር መስራት እና በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እና በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እና የፍትህ ስርዓት መካከል ያለውን ትብብር ማሳደግ፣
- በኢትዮጵያ የሃይማኖት ምክር ቤት በ2023 ዓይነት-1 ግርዛት (የሴት ልጅን ብልት ጫፍ መቁረጥ) ተቀባይነት አለው የተባለውን ፈትዋ ዲክላሬሽን ለመቀልበስ የህጻናት ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም የተቋቋመው ህብረት ከሌሎች የመንግስት ዘርፎች ጋር በመተባበር መስራት፣
- ማንኛውም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት ህገወጥ መሆኑን ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ከባህላዊ እና ማህበረሰቡ መሪዎች ጋር በመስራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳቱን በመቀነስ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ እና በረዥም ጊዜ ውስጥ ድርጊቱን ወደ ማጥፋት መሸጋገር እንዳለበት ማሳሰብ፤ ይህ ረጅም እና ቀጥተኛ ያልሆነ ሂደት ሊሆን እንደሚችል ማስገንዘብ፣
- የታቀዱ የሴት ልጅ ግርዛትን እና ህጻናት ጋብቻን ለመከላከል እና በቅርብ ጊዜ የተፈጸሙ ህጻናት ጋብቻዎችን ለመሰረዝ የሚረዱ ስም-አልባ (የሪፖርት አቅራቢውን ማንነት የማይጠቁሙ) የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን በትምህርት ቤቶች እና በሌሎች የማህበረሰብ ቦታዎች ማቋቋም፣
- በተለያዩ አካባቢዎች ጥሰቶችን በሚፈፅሙ ወላጆች፣ ባህላዊ ግርዛት ፈፃሚዎች፣ ጎልማሳ ባሎች እና ጋብቻ አስፈፃሚዎች ላይ የቅጣት እርምጃዎችን ለመውሰድ እና የማጠናከሪያ ዘዴዎችን እና ቁጥጥርን በቀበሌ ደረጃ ለማከናወን ከማህበረሰቡ ጋር መስራት፣
- ሴቶች የራሳቸውን እና ወደፊትም የሴት ልጆቻቸውን መብቶቻቸውን እንዴት እንደሚጠይቁ እና የሴት ልጅ ግርዛትን ቅጣት እንዲያውቁ ለማድረግ ከልጃገረዶች እና ሴቶች በተለይም ከእናቶች ጋር በመሆን መስራት፣
- ህጉን እና በሴት ልጅ ግርዛት እና በህጻናት ጋብቻ ጥሰት ቅጣቶችን አባቶች እንዲያውቁ ለማድረግ ከታዳጊ እና ከጎልማሳ ወንዶች ጋር መስራት ያስፈልጋል።

**ገዳቢ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች የልጃገረዶች እና የሴቶችን የትምህርት፣ የስራ እና የውሳኔ አሰጣጥ እድል ስለሚገድቡ እና በመጨረሻም ሁለቱንም የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ስለሚያበረታቱ ሁሉም የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክተር እነዚህን እምነቶች እና ልምዶች በቀጥታ ለመፍታት ጥረቶችን ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።** ይህም የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- ልጃገረዶች እና ሴቶች የመብት ጥሰቶችን በሚስጥር የሚያመለክቱባቸውን ቦታዎች መፍጠር እና ማጠናከር (አውዱ ላይ በመመስረት)፤
- ልጃገረዶች እና ሴቶች ስለራሳቸው እና ለወደፊት ሴት ልጆቻቸው መብት ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ እና ጥሰቶችን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉ (በሚስጥር) ማሳወቅ ላይ ቅድሚያ መስጠት(ለትምህርት ባለሞያዎች፣ ሴቶች ጉዳይ፣ ፖሊስ እና የፍትህ አካላት)፣
- ልጃገረዶች እና ሴቶች የራሳቸውን ክህሎት የሚያዳብሩበት መንገዶችን መፍጠር (የመደበኛ ትምህርት ማግኘት ለተከለከሉት ማንበብና መቁጠርን ጨምሮ)፣
- ሴቶች ልጆቻቸውን ለማጎልበት እና ወንዶች ልጆቻቸው የተሻሻለ የወንድ አመለካከት እንዲከተሉ (ያልተገረዙ ልጃገረዶችን "እንዳያገቡ" ከሚያደርጉት ደንቦች መራቅን ይጨምራል) ለማበረታታት ከእናቶች ጋር መስራት፣
- ስለልጃገረዶች ትምህርት አስፈላጊነት እና ትምህርታቸውን በተጨባጭ እንዴት እንደሚደግፉ ከህብረተሰቡ ጋር በመስራት የጊዜ አጠቃቀማቸው እና ደህንነቱ የተጠበቀ ወደ ትምህርት ቤት ጉዞን ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ማመቻቸትን (ለምሳሌ በቡድን ወይም ከአዋቂ ጋር መሄድ)፣

- የሴቶችን ከሴት ልጆች ወሲባዊ ንፅህና እና “የተሳካ” ጋብቻ ጋር የተያያዘውን አቋም ለማስታረቅ በማህበረሰቡ ውስጥ መስራት፣
- ሴት ልጆችን፣ ቤተሰቦቻቸውን እና ማህበረሰባቸውን በማስተማር የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን በክልል ደረጃ በተስተካከለ መንገድ መፍታት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ሴት ልጆች በሶማሊ የበለጠ አስተዋፅዖ አላቸው ምክንያቱም የሴት ልጅ ግርዛት ዘግይቶ ይከናወናል፤ እናም በዚያ ክልል ውስጥ ጋብቻዎችም ብዙውን ጊዜ በታዳጊ የሚመሩ ስለሆኑ ስለሁለቱም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚታሰቡትን ጥቅሞች መቃወም እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶቹን ማሰቀም ስላለው አውነተኛ ጥቅሞች ግንዛቤን ማሳደግ፣
- በማህበረሰቡ ውስጥ እና በማህበራዊ ሚዲያዎች ውስጥ የለውጥ አርአያ ሆነው የሚሰሩ - የተማሩ ልጃገረዶች እና ሴቶች እንዲሁም ተራማጅ ወንዶች - አርአያ መፍጠር;
- ጥቃቶች ላይ የሚሰራውን የአንድ ቦታ ማዕከላትን (one-stop centres) ማስፋፋት እና በማኅበረሰቦች መካከል መኖራቸውን ግንዛቤ ማሳደግ ከጾታዊ እና ጾታ-ተኮር ጥቃት የተረፉ ሰዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ፣ በግጭት የተጎዱ አካባቢዎችን ቅድሚያ በመስጠት እና በአንድ ማቆሚያ ማዕከላት ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመስራት እንዲችሉ በህጻናት ጋብቻ እና በሴት ልጅ ግርዛት ስጋት ላይ ያሉትን ለመደገፍ ኃይላቸውን ማስፋት፣

**አባቶች፣ ወንድሞች፣ ወንድ ጓደኞች እና ባሎች የሴቶችን እና ሴቶችን ችግር የሚጎዳውን ሰፋ ያለ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን እና ልምዶችን ለማስቀጠል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የሴቶች፣ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የሴቶች ንፅህና እንደማረጋገጫ ሆኖ የሚታሰበውን ለሴት ልጅ ግርዛት የለውን አመለካከትን ለመቀየር መተባበር አለባቸው።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:

- አባቶች እና ወንድሞች የሚስቶቸን እና እህቶችን የጥናት ጊዜ እንዲያሳድጉ እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ መርዳት፣
- የሴት ልጅ ግርዛት የተፈፀመባትን ሴት ማግባት ለምን አስፈላጊ እንዳልሆነ እና ታዳጊና እና ጎልማሳ ወንዶች እህቶቻቸውን እና ሴት ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚከላከሉ እና በሚስታቸው ላይ ተጨማሪ ከግርዛት ጋር የተያያዘ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ለወንዶች እና ለወንዶች ልጆች ማስተማር፣
- በማህበረሰቡ ውስጥ የወንዶችን ደረጃና ክብር ከሴት ልጆች የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ንፅህና እና “የተሳካ” ጋብቻ ጋር በማቆራኘት የሚታሰበውን ለመለወጥ መስራት፣
- ታዳጊና ጎልማሳ ወንዶችን ስለ አንድ በእድሜዋ የበሰለች ጎልማሳ ሚስት ማግባት ተግባራዊ ጠቀሜታዎች (ለምሳሌ የተሻለ ረዳት ማግኘት፣ በወሊድ ወቀት የሚያጋጥሙትን አደጋዎች ያነሱ መሆን) እና ልጅን ማግባት ያለውን ጉዳት (የኻኙነት አለመጣጣም) ማስተማር፣
- የበለጠ ፍትሃዊ የሆነ የቤተሰብ ውሳኔ አሰጣጥ እና የስራ ጫናን ማበረታታት እና ጉዳት ፈፃሚ የወንዶች የበላይነትን አለመቀበል ያስፈልጋል።

**የልጃገረዶች እና የሴቶችን ህይወት የሚገድበው የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች ማህበረሰቦችን እና መሪዎችን እነዚህን መመዘኛዎች የመለየት እና የመፍትሄ አቀማቸውንም ስለሚገድቡ በልጆች እና በስርዓተ-ፆታ ላይ ያተኮሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከወጣቶች እና ጎልማሶች ጋር በመተባበር እነዚህን እምነቶችን እና ልምዶችን እንዲቀይሩ እና የአካባቢያዊ አቅምን እንዲያጎለብቱ መስራት አለባቸው።** እነዚህም የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው:

- ልጃገረዶች የትምህርት እድል እንዲያገኙ እና ስኬታማ እንዲሆኑ መደገፍ፣
- በታዳጊ ዕድሜ ላይ ከሚገኙ ወጣቶች ጋር በሴት ልጅ ግርዛት እና ህጻናት ጋብቻ ዙሪያ በመስራት አሁን ያሉትን ልምዶች በአሁኑ ወቅታዊ አውድ ላይ በመመስረት መቀየር ወይም የትውልዱን ለውጥ ማበረታታት፣
- ሴቶች ስለ ራሳቸው እና ሴት ልጆቻቸው መብቶች እንዲማሩ እና እንዴት እነሱን ማስከበር እንደሚችሉ እንዲያውቁ መደገፍ፣
- የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን በቀጥታ የሚመለከቱ እና ልጃገረዶችን እና ሴቶችን እንዴት እንደሚጎዱ የሚያሳውቁ የወላጅ ትምህርት ኮርሶችን ለእናቶች እና ለአባቶች መስጠት፣
- በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ የሴቶች እና የሥርዓተ-ፆታ ክበቦችን ማጠናከር፣
- በማህበረሰቡ ውስጥ እና በማህበራዊ ሚዲያዎች ውስጥ የለውጥ አርአያ ሆነው የሚሰሩ - የተማሩ ልጃገረዶች እና ሴቶች እንዲሁም ተራማጅ ወንዶች - አርአያ መፍጠር;
- አድሎአዊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ጎጂ ውጤቶች ላይ እና በትምህርትና በኢኮኖሚ የጎለበቱ ልጃገረዶች እና ሴቶች ጥቅም ላይ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ከአካባቢው አመራሮች እና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመስራት ያስፈልጋል።

**ሴት ልጆች ከወንዶች ይልቅ ከትምህርት የመገለል እድላቸው ከፍተኛ በመሆኑ የትምህርት ሴክተሩ ሁሉም ልጃገረዶች ቢያንስ እስከ መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድረስ የትምህርት እድል እንዲያገኙ እና እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ጥረቶችን ማጠናከር ይኖርበታል።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- ሁሉም ማህበረሰቦች (ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ አርብቶ አደሮችን ጨምሮ) ጥራት ያለው ትምህርት ቢያንስ እስከ

6ኛ ክፍል የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች እንዲኖራቸው ማድረግ። የሚማሩበት ትመህርትም ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመሸጋገር የበለጠ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የእንግሊዘኛ ቋንቋን ማካተት አለበት፤ ቀደም ብለው ትምህርት የተነፈጉ ትልልቅ ልጃገረዶች እና ሴቶች የማንበብ፣ መጻፍ እና የቁጥር እውቀትን እንዲያገኙ ለማግኘት ዕድሎች መስፋፋት አለባቸው።

- ከትምህርት ቤት ውጪ የሆኑትን ወይም በመደበኛነት የማይገኙ ልጆችን ለማስመዝገብ ከቤት ወደ ቤት የሚደረግ ግልጋሎት እንደአግባቡ ከወላጆች ቀጣት ጋር ተደምሮ እንዳስፈላጊነቱ መተግበር አለበት።
- መደበኛ የሆኑትም ሆነ ያልሆኑት ተጨማሪ ትምህርቶች በስርዓተ-ፆታ ላይ ማተኮር አለባቸው፤ ለምሳሌ በወር አበባ እና በመጸዳጃ ቤት ዙሪያ ያለውን መገለል፣ የሴት ልጅ ግርዛትን፣ የህጻናት ጋብቻን እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን፣
- ልጃገረዶች አዎንታዊ አርአያ እንዲሆኑላቸው ተጨማሪ ሴት አስተማሪዎች መቅጠር፣
- ከድሀ ቤተሰብ ለመጡ ተማሪዎች የበለጠ የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦትን ማረጋገጥ፣
- በሁሉም የክፍል ደረጃዎች፣ በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብሮች፣ የንፅህና አጠባበቅ እና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች አቅርቦቶች፣ አሳታፊ የሥርዓተ-ፆታ ክበቦች፣ የመማሪያ መጽሀፍት፣ ቤተመጻሕፍት እና አጋዥ ስልጠናዎች ላይ የተጨመሩ ኢንቨስትመንቶችን ቅድሚያ መስጠት፣
- በገጠር ተጨማሪ መካከለኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መገንባት እና በገዜያዊነት ለተማሪዎች (በተለይ ልጃገረዶች) አስተማማኝ እና ተመጣጣኝ የመሳፈሪያ አማራጮች ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣
- ለመምህራን ማበረታቻዎችን እንደ አስፈላጊነቱ መለዋወጥ እና መቅረትን ለመቀነስ በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ጽ/ቤቶች የበለጠ ቁጥጥርን ማድረግ ያስፈልጋል።

**አለማቀፋዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የህጻናት ጋብቻን ለመከላከል ከሁሉ የተሻለው መንገድ ልጃገረዶችን በተቻለ መጠን ለረጅም ጊዜ በትምህርት ቤት ማቆየት ነው። ማህበራዊ ጥበቃን በመጠቀም ቤተሰቦች ልጃገረዶችን በማስተማር እና ጋብቻን ለማዘግየት ማበረታታት አለባቸው፡** ፡ ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሞችን ለሴት ልጆች ከተጨማሪ ወደቤት ከሚወሰዱ ምግቦች ጋር መጀመር ወይም ማስቀጠል፣
- የልጃገረዶችን ትምህርት ለመደገፍ የልጃገረዶችን በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት እና የህጻናትያቸው ሳያገቡ ትምህርት መቀጠላቸውን፣ እና የወላጆች እና ታዳጊዎች በስርአተ-ፆታ ላይ ያተኮረ ፕሮግራም ላይ መሳተፋቸውን ቅድመ-ሁኔታ ያደረገ በጥሬ ገንዘብ እና መስሪያ ቁሳቁሶች ማስተላለፍ ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ፤ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜም ያለውን ለምርታማነት የሚያግዙ ሴፍትኔት ፕሮግራም መድረክ በመጠቀም ኢላማ ማድረግ እና ትግበራን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

**በአርብቶ አደር ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች እና ሴቶች የራሳቸውን ገቢ የማግኘት እድሎች እጅግ በጣም ውስን በመሆኑ የግብርና እና የሰራተኛ እና ማህበራዊ ሴክተር ያላገቡ እና የተጋቡ ሴቶችን የመተዳደሪያ አማራጮችን የማስፋፋት ጥረቶችን ማጠናከር አለባቸው። የልጃገረዶች እና የሴቶች የተሻሻለ የፋይናንስ ተደራሽነት የሴት ልጅ ግርዛትን የበለጠ እንዳያስቀጥል ከግንዛቤ ማስጨበጫ ጋር ሊጣመሩ ይገባል።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- የልጃገረዶችን እና የሴቶችን የመደበኛ ትምህርት ተደራሽነት ውስንነት ለመቅረፍ ማህበረሰብ-ተኮር የሆኑ ሴቶችን ብቻ ያካተቱ ማንበብ፣ መፃፍ እና መቁጠር ላይ ያተኮሩ ትምህርቶች ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ለትላልቅ ልጃገረዶች እና ሴቶች የእንስሳት እርባታ፣ የሰብል እርሻ፣ ንግድ እና ሌሎች በባህላዊ ተቀባይነት ያላቸውን የሙያ ክህሎቶችን እና የስልጠና ኮርሶችን (የአየር ንብረት ለውጥን እና ወራሪ ዝርያዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተነደፈ) ከህይወት ክህሎቶች እና የገንዘብ / የንግድ ችሎታዎች ጋር የተቆራኘ ትምህርት እንዲያገኙ ማስቻል፣
- ለትላልቅ ልጃገረዶች እና ሴቶች መደበኛ የቁጠባ እና የብድር ተቋማትን ለማግኘት ተጨማሪ እድሎች መፍጠር።
- ወጣት ልጃገረዶችን ለማነሳሳትና ባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ልማዶችን የሚፈታተኑ የሬዲዮ ፕሮግራሞች እና ትርኢቶችን ውጤታማ የግብርና ሥራ ፈጣሪዎችንና (ለምሳሌ በወተት፣ በንብ እርባታ ወይም በዶሮ እርባታ) የተሳካላቸውን ሴቶች ማሳየት።

**የሴት ልጅ ግርዛት የተፈፀመባቸው ልጃገረዶች እና ሴቶች እድሜ ልክ ለህመም እና ለበሽታ ስለሚጋለጡ፣ የሴት ልጅ ግርዛትን በህክምና የመከታተል አዝማሚያ እያደገ በመምጣቱ እና የህጻናት ጋብቻ እና የታዳጊ እርግዝና መፍታት ስለሚቻል በክልል እና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የጤና ቢሮዎች የጤና አጠባበቅ ሰራተኞች የመፍትሄው አካል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥረቶችን በእጥፍ ማሳደግ አለባቸው።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን እና ሌሎች የጤና እንክብካቤ ሰጪዎችን ስለ ሴት ልጅ ግርዛት አካላዊ፣ ስነልቦናዊ እና ወሲባዊ ስጋቶች ማሰልጠን፣
- የማህበረሰቡ አባላትን በቅድመ ወሊድ እና ህጻናት ክትባቶች ጉብኝት እና የአካባቢ እምነት እና ልማዶች አውዳዊ ግንዛቤን ጨምሮ ስለ የተለያዩ የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች

(በሱና ህግ ስር የማይወድቁትን ጨምሮ) እና የሴት ልጅ ግርዛትን የህይወት መዘዞችን በማካተት ማስተማር፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን በመመዝገብ የሚለወጡ አሰራሮችን እንዲከታተሉ እና እነዚህንም ለሁለቱም የጤና ቢሮዎች እና የ ሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ባለስልጣኖች የመልእክት መላላኪያዎችን እና ፕሮግራሞችን በተሻለ ሁኔታ ለማስተካከል በየጊዜው ማሳወቅ፣
- የተገረዙ ልጃገረዶች እና ሴቶች በተለያዩ የህይወት ዘመናቸው ተገቢውን የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በ2017 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመሪያ መሰረት የቤተሰብ ህግ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ስለሚጥለው እገዳ የጤና ባለሙያዎችን ማወቃቸውን እንዲያረጋግጡ ማሰልጠን እና ይህን ተግባር ሲፈፅም የተገኘ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ላይ ቅጣቶችን ማስፈጸም። ይህም ከክልል ጤና ጥበቃ ቢሮዎች እስከ ወረዳ እና ቀበሌ ድረስ ባሉት የጤና ባለሙያዎች ላይ ያለውን ክልከላ በተመለከተ ግልጽ መመሪያን ማካተት ይኖርበታል።
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን መደገፍ - ፍላጐት ዝቅተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች እንኳን - ያገቡ ልጃገረዶች ሰውነታቸው እስኪበስል ድረስ የእርግዝና መከላከያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
- የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ) እና የተባበሩት መንግስታት የስነ ህዝብ ፈንድ (UNFPA) ካቋቋሙት እና የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ከሆነው የምስራቅ አፍሪካ መድረክ ጋር በመተባበር የሴት ልጅ ግርዛት ለመቅረፍ ስልታዊ ድርጊቶችን ለማሳወቅ በተቋቋሙ አመታዊ ስብሰባዎች ላይ ማስረጃዎችን ማካፈልን ጨምሮ መሳተፍ ያስፈልጋል።

**አፋርና ሶማሊ በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን በመቀነሱ ረገድ ያሳዩትን እድገት ገና እያረጋገጡ ባለመሆናቸው፣ የክልሉ መንግስት አመራሮች የልጃገረዶችና የሴቶችን ህይወት የሚያሻሽል ማህበራዊ ለውጥ እንዲሁም ሰፋ ያለ የእድገት ውጤቶችን በማስተዋወቅ ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴት ልጅ ግርዛትንና የህጻናት ጋብቻን የሚከለክለውን የቤተሰብ ህግን ማጽደቅ፤
- ለውጥን አርበኞችን (በተለይ የጎሳ እና የሀይማኖት መሪዎች፣ የባህላዊ ግርዛት ፈፃሚዎች እና በራሳቸው ወይም በሴት ልጆቻቸው ህይወት ላይ በግርዛት ወይም በየህጻናት ጋብቻ የተጎዱ ሴቶች ለመለየት የሚደረጉ ጥረቶችን ማበረታታት፣
- ልጃገረዶች እና ሴቶች መብቶቻቸውን እንዲያገኙ የሚከለክሉትን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን እና ተግባራትን ለመቋቋም በቂ የሰው እና የገንዘብ ሀብቶችን መመደብ፣
- በሴክተር ደረጃ ያሉ ተዋናዮች ከግርዛት እና ህጻናት ጋብቻ ጋር በተያያዘ የተጣለባቸውን ግዴታ እየተወጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- የሴት ልጅ ግርዛትን እና ህጻናት ጋብቻን ለመከላከል የተነደፉ ፕሮግራሞችን በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ክትትል እና ግምገማ ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣ ስርጭቱ ከፍተኛ በሆነባቸው ራቅ ባሉ ማህበረሰቦች ላይ በማተኮር።

**የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ሀይማኖታዊ ግዴታ ስለሚታይ እና የህጻናት ጋብቻ በሃይማኖታዊ ተቀባይነት እንዳለው እና እንዲያውም ተመራጭ ተደርጎ ስለሚታይ መንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ከሀይማኖት መሪዎች ጋር በቅርበት በመስራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳቱን መቀነስ እና በመጨረሻም እነዚህን ጎጂ ልማዶች መተው።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-
- የሀይማኖት አባቶች የሴት ልጅ ግርዛትን እና ህጻናት ጋብቻን በተመለከተ ጥብቅና መቆም ህገወጥ መሆኑን እና ህጻናት ጋብቻን በመፈጸማቸው ሊከሰሱ እንደሚችሉ ግንዛቤን ማሳደግ/ ከ18 ዓመት በታች ለሆናቸው ልጃገረዶች ኒካህ (የሸሪዓ ጋብቻ ሰርተፍኬት) ማጽደቅ፤
- የሴት ልጅ ግርዛትን (በተለይም በሴት ብልት) እና በህጻናት ጋብቻ የሚያስከትለውን ጉዳት እና ጋብቻን እስከ አዋቂነት ድረስ ማዘግየት ስላለው ጥቅም ትምህርት መስጠት፣
- የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች በሱና ስር እንደማይወድቁ ወይም እነደማይገናኙ ማህበረሰቦችን ማስተማር፣
- የሃይማኖት መሪዎች ዝምታቸውን እንደ ስምምነት ከመውሰድ ይልቅ የሴቶችን ለትዳር ንቁ ፈቃድ እንዲፈልጉ ማበረታታት፤
- የሴት ልጅ ግርዛት እና የህጻናት ጋብቻ በእስልምና ይፈለጋል/ ይፈቀዳል የሚሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን መፍታት እና ልማዶቹን ለማስቀረት አሳማኝ ሀይማኖታዊ ክርክሮችን ማዘጋጀት (ልጃገረዶች ወደ መስጊድ ለመግባት እና ለመስገድ መቀረጥ አለባቸው የሚለውን እምነት ጨምሮ)፣
- ለልጃገረዶች ለእራሳቸው እና ለወደፊት ትውልዶች የትምህርት ድጋፍ መገንባት፣
- ልጃገረዶች እና ሴቶች ለቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ማወቅ እና ወንዶች እና ወንዶች ልጆችን ከጥቃት እንዲርቁ ማስተማር እና የሴት ቤተሰብ አባላትን በደግነት እና በአክብሮት መያዝን ጨምሮ ሰፋ ያለ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን መገንባት ያስፈልጋል።

**ጎሳ እና ባህል የአፋር እና የሶማሊ ማንነት ማዕከል ስለሆኑ ለግርዛት እና የህጻናት ጋብቻ ቀጣይነት - የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ልጃገረዶችን እና ሴቶችን የሚጎዱ እምነቶችን እና ልምዶችን ለመቀየር ከጎሳ መሪዎች ጋር ተቀራርበው መስራት አለባቸው።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- የሴቶችን ትምህርት ማሳደግ፣
- በራዲዮ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በቲቪ፣ በማህበረሰብ ውይይቶች፣ ትምህርት ቤትን መሰረት ባደረጉ የስርዓተ-ፆታ ክለቦች እና በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ጨምሮ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት በተለይም የብልት ትልተላና ማጥበብን ጉዳት በተቀናጀ መልኩ ግንዛቤን ማሳደግ፣
- የህጻናት ጋብቻን አደጋዎች እና ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ማዘግየት ያለውን ጥቅም ግንዛቤን ማሳደግ፣
- ማህበረሰቦች - በተለይም ባህላዊ ቆራጮች እና እናቶች - ሁሉም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት ህገወጥ እና ቅጣት እና እስራት የሚደርስባቸው መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ።

**የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናትን ጋብቻን ለማስቆም ብሔራዊ ጥምረት በልዩ ሁኔታ ለመቀጠል እና ለማጥፋት ጥረቶችን ለማፋጠን የተቋቋመ በመሆኑ የጥምረቱን አባላት በጋራ በመሆን አዳዲስ የለውጥ መንገዶችን መክፈት እና አዳዲስ መሪ የለውጥ ሀይሎችን በየደረጃው ያለውን የማጥፋት ዘመቻ እንዲደግፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው።** ህብረቱ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:-

- ከክልል ባለስልጣናት ጋር መስራት፣ የብሄራዊ እና ክልላዊ ህጎችን ለማስማማት መሟገት፤ ከዞንና ወረዳ ባለስልጣናት ጋር ግንዛቤን ለማሳደግ እና አፈፃፀምን ማሻሻል፣ ከአካባቢው ባለስልጣናት ጋር ልማዳዊ አሠራሮችን ለማስወገድ በቁርጠኝነት ለመስራትና እና በቀበሌ ደረጃ ለመደገፍ ቁርጠኝነትን ማጠናከር፣ እና ከሀይማኖት እና የጎሳ መሪዎች ጋር የሚተገበሩ እቅዶችን ማዘጋጀት፣
- ሴት ልጆችን በትምህርት ቤት ለማቆየት የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር፣ የሴቶች ክበባትና የሥርዓተ ጾታ ክበባት መስፋፋትን መደገፍ እና በግርዛት ተግባር ውስጥ የሚደረገውን የመድኃኒት ሕክምናን መፍታትን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች (በተለይ ከጤና፣ ከትምህርትና ከፍትሕ) ጋር በመተባበር የሕፃናት ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን መከላከል በመንግሥት ሴክተር ዕቅዶች ውስጥ መስራት፣
- በታዳጊ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች እና የወላጆች ከአድሎአዊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች ለመራቅ እና ነፃነት ያለው ህይወት ለመምራት ያላቸውን አቅም ማሳወቅ፣ ጋዜጠኞች እና የሚዲያ አዘጋጆች ስለ ልጃገረዶች እና ሴቶች ብቃት ሪፖርት እንዲያደርጉ የአቅም ግንባታ ድጋፍን ማድረግ፣
- በማስረጃ ማሰባሰብን እና በመረጃ የተደገፈ ቅስቀሳ እና ትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድረግን ማስቀጠል።

**የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህጻናት ጋብቻን ማስቀረት ሃብትን የሚጠቅም እና ተከታታይነት ያለው የረጅም ጊዜ ስራን የሚጠይቅ በመሆኑ የልማት አጋሮች በፕሮግራም አወጣጥ ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው።** ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

- በሩቅ አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉትን ጨምሮ ለሁሉም ህጻናት በትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ተጽእኖ ያላቸውን የመምህራንን ማሰልጠኛ እና የትምህርት ቤት ምገባን።
- በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ቤተሰቦች ማህበራዊ ጥበቃን ማጎልበት፣ በተቻለ መጠን የሴቶችን ትምህርት ለማሻሻል (እና የህጻናት ጋብቻን ለመቀነስ) መጠቀም፣
- የአካባቢ አገልግሎቶችን ለማሻሻል የክፍለ-ሀገራዊ አቅምን ማጠናከር፣
- ገዳቢ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለመቀየር በፕሮግራም አወጣጥ ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣
- የአውድ ልዩነትን ከፍ ለማድረግ ፕሮግራሞችን ማሻሻል እና ማስተካከል፣
- በጠንካራ የረጅም ጊዜ ክትትል፣ ግምገማ እና ምርምር ላይ ኢንቨስት ማድረግ እድገትን ለመከታተል፣ ከአውድ ልዩነት አንፃር እንዴት በጣም አነስተኛ የሆኑ ሀብቶችን ማሰማራት እንደሚቻል እና ውጤታማ የፕሮግራም አወጣጥን እንዴት ማስተዋወቅ እንደሚቻል ማሳወቅ።

# ዋቢ መጻህፍት


Abathun, A.D., Sundby, J. and Gele, A.A. (2016) "Attitude toward female genital mutilation among Somali and Harari people, Eastern Ethiopia" International Journal of Women"s Health 8: 557–569 (https://doi.org/10.2147/IJWH.S112226)

Abathun, A.D., Sundby, J. and Gele, A.A. (2018) "Pupil"s perspectives on female genital cutting abandonment in Harari and Somali regions of Ethiopia" BMC Women"s Health 18: 167 (https://doi.org/10.1186/s12905-018-0653-6)

Abdisa, B., Desalegn, M. and Tesew, A. (2017) "Assessment of the prevalence of FGM and associated factors among women"s of reproductive age group in Kebirbeyah town, Somali region eastern Ethiopia, 2017" Health Science Journal 11(4): 517

Abebe, A. (2014) "Pastoralists" response to sedentarization and its effect on resource use pattern and poverty alleviation (the case of Awra and Uwwa woredas, Afar regional state, Ethiopia)" SSRN (https://dx.doi.org/10.2139/ssrn.2618751)

Abebe, S., Dessalegn, M., Hailu, Y. and Makonnen, M. (2020) "Prevalence and barriers to ending female genital cutting: the case of Afar and Amhara regions of Ethiopia" International Journal of Environmental Research and Public Health 17(21): 7960 (https://doi.org/10.3390/ijerph17217960)

Adinew, Y. and Mekete, B. (2017) "I knew how it feels but couldn"t save my daughter; testimony of an Ethiopian mother on female genital mutilation/cutting" Reproductive Health 14: 162 (https://reproductive-health-journal.biomedcentral.com/articles/10.1186/s12978-017-0434-y)

Alemu, Y. and Solomon, S. (2019) "Implementation of alternative basic education program in SITI pastoral zone of Somali regional State, Ethiopia" International Journal of Multidisciplinary Research and Development 6(3): 236–242 (http://www. allsubjectjournal.com/archives/2019/vol6/issue3/5-11-55)

Andarge, M.Y. (2014) "The difficulties of ending female genital mutilation (FGM): case of Afar pastoralist communities in Ethiopia". MA thesis, Institute of Social Studies, The Hague (www.ohchr.org/Documents/Issues/Women/WRGS/FGM/NGOs/ActionForIntegratedSustainableDevelopmentAsso-ciation.pdf)

Asmani, I. and Abdi, M. (2008) De-linking female genital mutilation/cutting from Islam. New York: United Nations Population Fund (UNFPA) (www.unfpa.org/publications/delinking-female-genital-mutilationcutting-islam)

Balehey, S., Tesfay, G. and Balehegn, M. (2018) "Traditional gender inequalities limit pastoral women"s opportunities for adaptation to climate change: evidence from the Afar pastoralists of Ethiopia" Pastoralism 8: 23 (https://doi.org/10.1186/s13570- 018-0129-1)

Central Statistical Agency of Ethiopia (CSA) and ICF (2017) Ethiopia Demographic and Health Survey 2016. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland, USA: CSA and ICF (https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR328/FR328.pdf)

Dessalegn, M., Ayele, M., Hailu, Y., Addisu, G., be, S., Solomon, H. and Stulz, V. (2020) "Gender inequality and the sexual and reproductive health status of young and older women in the Afar region of Ethiopia" International Journal of Environmental Research and Public Health 17(12): 4592 (https://doi.org/10.3390/ijerph17124592)

Elezaj, E., Ramful, N., Cebotari, V. and De Neubourg, C. (2019) Gender equality, women"s empowerment and child wellbeing in Ethiopia. UNICEF Ethiopia and Ministry of Women, Children and Youth (www.unicef.org/ethiopia/media/2811/file/Gender%20Equality,%20Women"s%20empowerment%20 and%20child%20wellbeing%20in%20Ethiopia.pdf)

Endale, K., Jones, N., Presler-Marshall, E., Woldehanna, T., Yadete, W., Abdisalam, A., Alemu, A., Gebeyehu, Y., Gezahegne, K., Murha, R., Neumeister, E., Tesfaye, A., Tilahun, K. and Workneh, F. (2022) Exploring the patterning and drivers of FGM/C and child marriage in pastoralist Ethiopia. Baseline report from Afar and Somali regions. London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Endale, K., Yadete, W., Woldehanna, T., Presler-Marshall, E., Jones, N., Gebeyehu, Y., Abdiselam, A. and Tesfaye, A. (2024a) Adolescent girls" and women"s economic and social empowerment in pastoralist Ethiopia: midline survey. Caregiver module. Round 2 (2023/2024). London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Endale, K., Yadete, W., Woldehanna, T., Presler-Marshall, E., Jones, N., Gebeyehu, Y., Abdiselam, A. and Tesfaye, A. (2024b) Adolescent girls" and women"s economic and social empowerment in pastoralist Ethiopia: midline survey. Core respondent module. Round 2 (2023/2024). London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Ethiopia Peace Observatory (n.d.) Afar-Somali border conflict (https://epo.acleddata.com/afar-somali-border-conflict/)

Flintan, F. (2008) Women"s empowerment in pastoral societies. World Initiative for Sustainable Pastoralism, Global Environment Facility, United Nations Development Programme and International Union for Conservation of Nature (www.iucn.org/sites/default/files/import/downloads/gender_format.pdf)

GAGE consortium (2019) Gender and adolescence: why understanding adolescent capabilities, change strategies and contexts matters. Second edition. London: Gender and Adolescence: Global Evidence (www.gage.odi.org/wp-con-

tent/uploads/2020/01/Conceptual-Framework-2nd-Edition_WEB.pdf)

Gebremariam, K., Assefa, D. and Weldegebreal, F. (2016) "Prevalence and associated factors of female genital cutting among young adult females in Jigjiga district, eastern Ethiopia: a cross-sectional mixed study" International Journal of Women"s Health 8: 357–365 (https://doi.org/10.2147/IJWH.S111091)

Getanehe, T.M. (2017) "Knowledge, attitude and practice of female genital mutilation among the community of Gursum woreda, Somali regional state of eastern Ethiopia". MA thesis, Addis Ababa University

Goshu, D., Ketema, M., Bessie, S., Tazeze, A. and Teshale, D. (2021) Socioeconomic development in Afar region: achievements, gaps, and priorities. Addis Ababa: Ethiopian Economics Association (https://eea-et.org/wp-content/uploads/2021/09/Afar-Research-Report-setup.pdf)

Gurmu, B.W. (2018) "The role of women in livelihood security at household level among pastoral and agro-pastoral societies of Ethiopian Somali region: the case of two selected districts from Fafen zone of Ethiopian Somali region" International Journal of Sociology and Anthropology 10(4): 27–42 (https://academicjournals.org/journal/IJSA/article-full-text-pdf/4A0B5C357410)

Haji, J. and Legesse, B. (2017) "Impact of sedentarization program on the livelihood and food security of Ethiopian pastoralists" Journal of Arid Environments 136: 45–53 (https://doi.org/10.1016/j.jaridenv.2016.10.007)

Inkermann, H. (2015) Diversification of livelihood strategies and the transformation of pastoralist life among Afar women in Baadu Ethiopia. Occasional Papers of the Centre for Development Geography, No. 04, Bonn (https://bonndoc.ulb.uni-bonn.de/xmlui/handle/20.500.11811/8580)

Jackson, E. (2011) The role of education in livelihoods in the Somali region of Ethiopia. Boston, MA: Feinstein International Center, Tufts University (https://resourcecentre.savethechildren.net/pdf/5812.pdf)

Jones, N., Tefera, B., Emirie, G., Gebre, B., Berhanu, K., Presler-Marshall, E., Walker, D., Gupta, T. and Plank, G. (2016) One size does not fit all: the patterning and drivers of child marriage in Ethiopia"s hotspot districts. London: Overseas Development Institute and UNICEF Ethiopia (www.unicef.org/ethiopia/media/1536/file/One%20size%20does%20not%20fit%20all.pdf)

Kabeer, N. (2003) Making rights work for the poor: Nijera Kori and the construction of "collective capabilities" in rural Bangladesh. Working Paper 200. Brighton: Institute of Development Studies (www.ids.ac.uk/publications/making-rights-work-for-the-poor-nijera-kori-and-the-construction-of-collective-capabilities-in-rural-bangladesh-2)

Lelieveld, M. (2011) Child protection in the Somali region of Ethiopia. BRIDGES Project, Save the Children UK (https://resourcecentre.savethechildren.net/sites/default/files/documents/5115.pdf)

Mahamoud, A.A. and Ahmed, M.E. (2019) "The social consequences of pastoralist sedenterisation schemes in Somali regional state, Ethiopia" Interdisciplinary Description of Complex Systems 17(4): 738–752

Management Entity (2021) Ethiopia"s livestock systems: overview and areas of inquiry. Gainesville, FL, USA: Feed the Future Innovation Lab for Livestock Systems (https://livestocklab.ifas.ufl.edu/media/livestocklabifasufledu/pdf-/LSIL_Livestock_Systems_Overview_Ethiopia_2021_08.pdf)

Ministry of Education 2023 https://moe.gov.et/storage/Books/ESAA%202022-23%20Final.pdf

McGavock, T. (2021) "Here waits the bride? The effect of Ethiopia"s child marriage law" Journal of Development Economics 149 (https://econpapers.repec.org/article/eeedeveco/v_3a149_3ay_3a2021_3ai_3ac_3as0304387820301553.htm)

Ministry of Education (2023) Education statistics annual abstract 2022/2023 (2015.E.C). Addis Ababa: Federal Ministry of Education (https://moe.gov.et/storage/Books/ESAA%202022-23%20Final.pdf)

Mohamud, M., Kaba, M. and Tamire, M. (2016) "Assessment of barriers of behavioral change to stop FGM practice among women of Kebri Beyah district, Somali regional state, eastern Ethiopia" Global Journal of Medical Research 16(6): 39-61 (https://medicalresearchjournal.org/index.php/GJMR/article/view/1248)

Muhumed, M. (2017) "Factors that affect the effectiveness of alternative basic education performance in Awbare district of Ethiopian Somali regional state: the case of Lafaissa Cluster Resource Center". MA thesis, Jigjiga University

National Planning Commission (2017) Ethiopia"s progress towards eradicating poverty: an interim report on 2015/16 poverty analysis study. Addis Ababa, Ethiopia

Nussbaum, M. (2011) Creating capabilities: the human development approach. Cambridge, MA: The Belknap Press of Harvard University Press

Østebø, T. (2023) "Religious minorities in Ethiopia" in E. Baffelli, A. van der Haven and M. Stausberg (eds) Religious minorities online. Berlin, Boston: De Gruyter (https://doi.org/10.1515/rmo.20651707)

Oxfam (2016) Consolidated gender analysis for the Ethiopian drought response. CARE, Consortium of Christian Relief and Development Associations (CCRDA), ChildFund, Concern Worldwide, GOAL Ethiopia, Oxfam, Rift Valley Children and Women Development Organisation (RCWDO), Sustainable Environment and Development Action

(SEDA) (https://policy-practice.oxfam.org/resources/consolidated-gender-analysis-for-the-ethiopian-drought-response-620088)

Presler-Marshall, E., Jones, N., Oakley, E., Dutton, R., Baird, S., Yadete, W. and Gebeyehu, Y. (2022a) Exploring the diversity of FGM/C practices in Ethiopia: drivers, experiences and opportunities for social norm change. London: Gender and Adolescence: Global Evidence

Presler-Marshall, E., Endale,K., Yadete, W., Jones, N., Gebreyehu, Y., Murha, R., Workneh, F., Woldehanna, T. and Tilahun, K. (2024a) "The impacts of the northern Ethiopia conflict on adolescents in Afar". Policy brief. London: Gender and Adolescence: Global Evidence (www.gage.odi.org/publication/the-impacts-of-the-northern-ethiopia-conflict-on-adolescents-in-afar)

Presler-Marshall, E., Endale, K., Jones, N., Woldehanna, T., Yadete, W., Murha, R. and Gebeyehu, Y. (2024b) "Female genital mutilation in Ethiopia"s Afar region: Patterning, drivers, and decision-making" Journal of Adolescent Health 75(3): 496-501 (https://www.jahonline.org/article/S1054-139X(24)00248-9/pdf)

Presler-Marshall, E., Jones, N., Endale, K., Woldehanna, T., Yadete, W. and Abdiselam, A. (2024c) ""People will talk about her if she is not circumcised": exploring the patterning, drivers and gender norms around female genital mutilation in Ethiopia"s Somali region" Social Science & Medicine: 116664

Presler-Marshall, E., Jones, N., Yadete, W., Abdisalem, A., Gebreyehu, Y., Murha, R., Tilahun, K. and Workneh, F. (2024d) Adolescent girls" and women"s economic and social empowerment in pastoralist Ethiopia: midline qualitative research instruments. London: Gender and Adolescence: Global Evidence (https://www.gage.odi.org/publication/adolescent-girls-and-womens-economic-and-social-empowerment-in-pastoralist-ethiopia-midline-qualitative-research-instruments/)

Ridgewell, A. and Flintan, F. (2007) Gender & pastoralism vol 2: livelihoods & income development in Ethiopia. Addis Ababa: SOS Sahel Ethiopia (https://sahel.org.uk/wp-content/uploads/Gender-Pastoralism-Vol-2-ebook.pdf)

Sen, A.K. (1984) Commodities and capabilities. Oxford, UK: Oxford University Press

Sen, A.K. (2004) "Capabilities, lists, and public reason: continuing the conversation" Feminist Economics 10(3): 77–80

Tadesse, B., Beyene, F., Kassa, W. and Wentzell, R. (2015) "The dynamics of (agro) pastoral conflicts in eastern Ethiopia" Ethiopian Journal of the Social Sciences and Humanities 11(1)

Teka, A.M., Woldu, G.T. and Fre, Z. (2019) "Status and determinants of poverty and income inequality in pastoral and agro-pastoral communities: household-based evidence from Afar regional state, Ethiopia" World Development Perspectives 15: 100123 (https://doi.org/10.1016/j.wdp.2019.100123)

UNICEF (n.d.a) Situation analysis of children and women: Afar region (www.unicef.org/ethiopia/media/2521/file/Afar%20region%20.pdf)

UNICEF (n.d.b) Situation analysis of children and women: Somali region (www.unicef.org/ethiopia/media/2401/file/Somali%20region%20.pdf)

UNOCHA – United Nations Office for the Coordination of Humanitarian Affairs (2022) "Humanitarian bulletin Ethiopia" (www.unocha.org/publications/report/ethiopia/ethiopia-humanitarian-bulletin-17-january-2022)

USAID – United States Agency for International Development (2021) Women"s empowerment: gender, governance, and land in Afar, Ethiopia. Washington DC: USAID (https://pdf.usaid.gov/pdf_docs/PA00T6CD.pdf)

Wodajo, Y.W. (2014) "Education For All: reaching pastoralist communities in Somali region of Ethiopia: challenges and opportunities". MA thesis, Haramaya University

Woldesenbet, P. (2015) "Provision of and participation in primary education in the pastoralist regions of Afar and Somali of Ethiopia". Thesis, University of Tampere

World Bank (2020) Ethiopia regional poverty report: promoting equitable growth for all regions. Washington DC: World Bank (https://openknowledge.worldbank.org/handle/10986/34805)

World Health Organization (WHO) (2024) Female genital mutilation fact sheet, 5 February (www.who.int/news-room/fact-sheets/detail/female-genital-mutilation)

## ስለ ጌጅ

ሥርዓተ-ፆታ እና ታዳጊዎች፡ ዓለም አቀፍ መረጃ (ጌጅ) ለአስር አመት የሚቆይ (2016-2026 እኤአ) የረጅም ጊዜ የምርምር ፕሮግራም ሲሆን አላማውም በደቡብ የአለም ሀገራት የሚኖሩ ታዳጊ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶችን ሕይወት ለመለወጥ የሚያስችል ጥናታዊ መረጃ ማመንጨት ነው። ለበለጠ መረጃ www.gage.odi.orgን ይጎብኙ።

## ማስተባበያ

ይህ ሰነድ የሥርዓተ-ፆታ እና ታዳጊዎች፡ ዓለም አቀፍ መረጃ (ጌጅ) የስራ ውጤት ሲሆን በዩኬ ኤይድ የገንዘብ ድጋፍ የሚደገፍ በዩናይትድ ኪንግደምና በኢትዮጵያ መንግስት፣ እንዲሁም በአይሪሽ ኤይድ እርዳታ የሚደረግ ፕሮግራም ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት የተገለጹት አመለካከቶችና መረጃዎች የግድ የዩናይትድ ኪንግደምን ወይም የአየርላንድ መንግስትን ይፋዊ ፖሊሲዎች አያንጸባርቅም። የዩናይትድ ኪንግደም መንግሥት ወይም የአየርላንድ መንግሥትም ለእንደነዚህ አይነት እይታዎች እና መረጃዎች ምንም አይነት ሃላፊነት አይወስድም።

## የቅጂ መብት

አንባቢዎች የዚህን ዘገባ ይዘት ለራሳቸውና ለንግድ ላልሆኑ ህትመቶች እንዲጠቀሱና እንዲያባዙ ይበረታታሉ (ማንኛውም የንግድ አላማ ላለው ስራ ግን በመጀመሪያ ከጌጅ ፕሮግራም ጽህፈት ቤት ጋር በgage@odi.org.uk መነጋገርና መስማማት ይኖርበታል)። እንደ የቅጂ መብት ባለቤት፣ ጌጅ ተገቢውን እውቅናና የሕትመት ቅጂ ይጠይቃል። የጌጅ ሕትመትን ሲያጣቅሱ፣ እባክዎን አታሚውን ሥርዓተ-ፆታ እና ታዳጊዎች፡ ዓለም አቀፍ መረጃ (ጌጅ) በማለት ይጻፉ። በኦንላይን ላይ ለመጠቀም ፣ አንባቢዎች ከዋናው ምንጭ ጋር በጌጅ ድህረ ገጽ ላይ www.gage.odi.org እንዲገናኙ እንጠይቃለን።

©ጌጅ 2025. ይህ ስራ በክሬቲቭ ኮመንስ አትሪቢውሽን ንግድ-ነክ ያልሆነ 4.0 ዓለም አቀፍ ፈቃድ (CC BY-NC-SA 4.0) ስር ፍቃድ ተሰጥቶታል።

የፊት ሽፋን፡ በ16 ዓመቷ ትዳር መስርታ አራት ልጆች ያሏት ሴት፤ በአፋር ኢትዮጵያ ቡና የምትሸጥ ሴት ©ናታሊ በርትራምስ/ጌጅ 2024

ጌጅ ፕሮግራም ጽህፈት ቤት
አቨርሲስ ዴቨሎፕመንት ኢንስቲቱት
203 ብላክፍርያርስ መንገድ
ሎንደን SE1 8NJ
ዩናይትድ ኪንግዶም
ኢሜል፡ gage@odi.org
ዌብሳይት፡ www.gage.odi.org

ISBN: 978-1-917476-17-1